# ምዕራፍ አራት
# የመደበኛ ትምህርትጉዞዬ

በዱባንቾ፣ በሐንገጫ በዱራሜ የፊደል ቆጠራና የንባብ ትምህርት ጉዞ አበቃና ለመደበኛው ትምህርት ዕድል ተከፍቶልኝ በአጎቴ ልጅ በአቶ ተሰማ አሩሲ አማካይነት ወደ አሰላ ሄጇ ራስ ዳርጌ ትምህርት ቤት በ1944 ዓ.ም ትምህርት እንደ ጀመርኩ፣ በአመቱ መጨረሻ ወደ 3ኛ ክፍል መዛወሬን ከላይ ገልጫለሁ:: መማር ማለት መለወጥ ነዉና ጋሽ ተሰማ የከፈተልኝ የትምህርት በር ሕይወቴን ቀስ በቀስ እየለወጠ መሆኑ ይሰማኝ ነበር:: ያለ ውስጣዊ ዝግጅትና ሂደት የተለወጠዉ ስሜ እስከአሁን ይገርመኛል:: ነገሩ ይህን ይመስላል:-

ጋሼ ተሰማ፣ ክፍለ ጽዮን ጉግሣ የሚባል ጓደኛ ነበረዉ:: ክፍለጽዮን የራስ ጉግሣ ልጅ ሲሆን ወደ አሰላ የተላከዉ በግዞት ነበር። ጋሼ ተሰማና ክፍለጽዮን በዕድሜ ብቻ ሳይሆን በአስተሳሰብም የሚቀራረቡ ይመስለኛል። በየጊዜው እየተገናኙ ካርታና ዳማ ይጫወቱ ነበር። በወዳጅነቱ ተስቦ ይመስለኛል ጋሽ ተሰማ ትምህርት ቤት ሲያስመዘግበኝ ተስፋዬ የነበረው ስሜን ወደ ተስፋጽዮን ለወጠዉ፤ በዚያው በነካ እጁ የአባቴንም ስም ከዳለሎ ወደ ደለለው ዘወር አድርጎ በስም አማራ አደረገኝና አረፈዉ::

በ1946 ዓ.ም.አራተኛ ክፍል በራስ ዳርጌ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጨርሼ ለክረምቱ እረፍት ወደ ወላጆቼ ቤት ተመልሼ ሳለሁ ጋሼ ተሰማ ከአስተማሪነት ተነሥቶ የአውራጃው ትምህር ቤቶች ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ተሾመና ወደ ሻሸመኔ ተዛወረ።

ዝውውሩ ተፈጽሞ ቤት ተከራይቶ እስከሚወስደኝ ድረስ የ1947 ዓ.ም. አንደኛው ተርም አለቀ፤ ሻሸመኔ አፄ ናዖድ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አምስተኛ ክፍል የገባሁት





በሁለተኛዉ ተርም ነበር:: አሰላ ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ከጋሼ ተሰማ ጋር የጀመርሁት ጣፋጭ ኑሮ ጣዕሙ እንደመጀመሪያው አልቀጠለም:: ትዳር ሲመሰርት የቤቱ አስተዳደር ተቀየረ፤ ተጠሪነቴም ከጋሼ ወደ ባለቤቱ ተዛወረ፤ የቤት ውስጥ ሥራም እየበዛብኝ ለትምህርትና ለጥናት ጊዜ አጣሁ:: ለባል ዘመዶች መግቢያው እየጠበበ ያለመፈለጋችንም ግልጽና ጉልህ መሆን ጀመረ። ይህ ለኔ ብቻ ሳይሆን ለእናቱም ልጅ ለአቶ ዳንኤል አሩሲ በእንግድነቱ እንዳልተመቸው ለእኛ ቀርቶ ለጎረቤትም እየታወቀ ሄደ። የወ/ሮ ሙሉ እህት ልጆች ሁለቱ ለመኖር ሲመጡ መኝታዬ ተነጥቆ ለነርሱ ተሰጠና እኔ መሬት አነጠፍኩ።

ግፊቱ ጠነከረ፤ በዚያው መጠን አጣብቂኙ የማያፈናፍን እየሆነ ሄደ። የምግብ ነገር ይታለፍ። እኔም እንዴት እንዲህ ይሆናል በማለት ጥርሴን ነክሼ በመቻልና ጊዜ ይለውጠዋል በሚል ተስፋ መቀጠል ሞከርኩ። በሥራው ምክንያት ጋሼ ተሰማ በርካታ ቀናትን የሚያሳልፈዉ መስክ ነበር። ያ ጊዜ ደግሞ ፍላፃው ሁሉ የሚወረወርብኝ ወቅት ሆነብኝ።

ሁለታችንም ወንዶች እኔና ታፈሰ ለጥምቀት በዓል ልብሳችንን አጥበን ተኩሰን ግድግዳ ላይ በሁለት መስቀያ ገመድ ሰቅልንና በነገው ወደ ጥምቀት ልንሄድ በተገባልን ተስፋ መሠረት አደርን። ጧት ስንነሣ የኔ ልብስ አንድም ሳይቀር የዚያኛው አንድም ሳይነካበት ተወስዷል። ያለው ለበሰና ወደ ጥምቀተ ባሕር ሄደ፤ እኔም አዝኜና አልቅሼ ለቤቱ ሥራ ቀረሁ። ይኸ ሁሉ ሲሆን ተስፋ አልቆረጥኩም ነበር። አንድ ቀን ግን ህሊናዬ በትእግሥት ያስተናግደዉ ዘንድ የማይችለው ክስ መጣብኝ:: "ወጥ ሰርቀሃል" ተብዬ ስወነጀል ልቤ ተተረተረ:: በዳዊት አገላለጽ ‹አጥንቶቼ› እንክትክት አሉ። ማንነቴ ሟሸሸ። የምለውንና የምሆነውን አጣሁ። ሰብዕናዬ ከሡለ። ጋሼን ላናግር ብሞክር መልስ አልነበረውም። እምነቴም ተሰድቧል ከከእንግዲህ ምን ቀረኝ ብዬ እንደ እብድ ከቤት ወጣሁ። እከሌ ጋ ልሂድ የምልበት የለም ብቻ

ወጣሁ። "የት ትሄዳለህ" ያለኝም አልነበረም። ነገር ግን ያኔ ልብ ባልለውም መገፋቴ ያፈነዳዉ እምባዬ ገደቡን ጥሶ ሳያጥለቀልቀኝ የእንባዬ አባሽ የሆነዉ ጌታ አጠገቤ ኖሯል። እደጅ አላደርኩም፣ ለእለቱም ቢሆን ሆዴ ጠሙን አላደረም። ጌታ በሥርግ ተቀበለኝ።።

የክፍል ጓደኛዬ የወንድሙ ልጅ ታገባ ነበር። መንገድ ላይ አግኝቶኝ ሁኔታዬን ስነግረው "ና አብረን እንሂድ፤ ሥራም ትረዳለህ" ብሎኝ አብሬው ሄድኩና ሁለት ቀን አደርኩ። ቅዳሜና እሁድ አለፈ፣ ሥርጉም ወጥቶ ሰኞ መጣ፤ ጓደኛዬን ተሰናብቼ ወደ ከተማ ሄድኩ። ተመስገን ማዴቦን አገኘሁትና የማያልቀውን ታሪኬን ስነግረው "ከኔ ጋራ እደር" ብሎ ሻሸመኔ ከተማ ውስጥ ወደነበረው SIM ግቢ ወሰደኝ። እርሱ ከወላይታ የመጣ አማኝ ስለነበረ ሚሽኑ ማደሪያ ሰጥቶት እዚያ እያደረ አንድ ትምህርት ቤት (አፄ ናዖድ) እንማር ነበር። በዚያን ዓመት ነበር ከወላይታ የመጡ ወንጌላውያን ጋራ መተዋወቅ የቻልሁት።

በጓደኛዬ በተመስገን ምክንያትና በርሱ ምስክርነትም Neal እና Anderson የሚባሉ የኤስ አይ ኤም ሚስዮናውያን አንድ ሳምንት የተመስገን እንግዳ ሆኜ ቆየሁ።። ብዙም ሳይቆዩ እዚያው ከተመስገን ጋራ እንድቀጥል ፈቀዱልኝ። በሳምንትም የተወሰኑ ሰዓታት በሚስተር Neal ቤት በትንሽ ሳንቲም ተቀጥሬ እሠራላቸው ጀመር።። ቤተ ክርስቲያንም እዚያው በየእሁዱ እንደ ልቤ መከታተል መቻሉ የራሴ ሰው እየሆንኩ እንድሄድ አደረገኝ። በዚያን ጊዜ ነው የወንጌላዊ አባባ ገሎሬ ሕፃን ልጅ አርፋ አስከሬኑን በሰሌን ገንዘን መቃብር ቆፍረን እዚያው ሚሽን ጊቢ ውስጥ ቀብሯ የተፈጸመው። አንድን የ16 ዓመት ልጅ ለዚህ ሁሉ የሕይወት ተሞክሮ ለምን እንደገለጠጠዉ ምስጢሩን የሚያውቀዉ ጌታ እግዚአብሔር ብቻ ነበር ።





# ጥቂት ስለ ተሰማ አሩሲ




አቶ ተሰማ አሩሲ

ቀድመ አያቴ አቶ ድላባ ሁለት ወንዶች ልጆች ወለዱ። እነርሱም ሳካሎ እና ሳንሰሞ ይባሉ ነበር። አባቴና የጋሼ ተሰማ አባት ከነዚህ ሁለቱ ቅርንጫፎች ሲወለዱ የሁለቱም ግንድ ድላባ ነበሩ። ስለዚህ እኔና ጋሼ ተሰማ የቅደመአያት ልጆች ነን ማለቱ ዝርዝሩን ያስቀራል። ያም ሆነ ይህ አንድ ቤተሰብ ነን። በ1944 ዓ.ም ወደ አሰላ ራስ ዳርጌ ትምህርት ቤት የወሰደኝም እርሱ እንደሆነ በሌላው ክፍል ተገልጿል። በዚያን ጊዜ ከእርሱ ጋራ ያስተምሩ የነበሩት ጓደኞቹ አቶ ጥቄሄር ኃይሉ፣ አቶ ጥበበ ሳሳይና አቶ ለማ አዋሰው የሚባሉ ነበሩ።

አቶ ለማና ጋሼ አንድ ላይ ቤት ተከራይተውም አብረው ኖረዋል። እኔ ከጋሼ ጋራ ወደ አሰላ ስሄድ የገባሁትም ሁለቱ ተከራይተው ይኖሩበት በነበረው ቤት ነበር።

ሁለቱ ጓደኛሞች በጣም ይዋደዱ ስለነበረ ቤት ውስጥ ሲሆኑ ያልተወሳሰበ ሰብዕና ያላቸዉ፣ የማይከብዱ፣ የሚቃለዱና የሚሳሳቁ መልካም ምሳሌዎች የሚባሉ ነበሩ። አቶ ተሰማ በቁመናው ረዘም ያለ መልከ መልካም፣ በጣም ተወዳጅና የተከበረ ሰው ነበር። አንድ ቀን የአራተኛ ክፍል መጨረሻ ውጤት ለተማሪዎች እንደተሰጠ

# ጥቂት ስለ ተሰማ አሩሲ



አቶ ተሰማ አሩሲ

ስለሚያውቅ እስቲ ውጤትህን አሳየኝ ብሎኝ ሳሳየው "እንዲያ ነው! በርታ!" ካለ
በኋላ ለአቶ ለማ በእንግሊዝኛ አንድ ነገር አለው። ከዚያ ውስጥ የሰማሁት "ኰሌጅ
የሚለውን ቃል ብቻ ነበር። ሌላውን ንግግር እንዳልረዳ የአራተኛ ክፍል እንግሊዝኛ
ቃላቱ ገና በውስጤ ስላልዳበሩ አምልጦኛል። ቢሆንም አንድ ቀን ጠዋት ለጋሼ
ለማ የፊት ውኃ አቅርቤ ሳስታጥብ በቀደም ስለ እኔ በእንግሊዝኛ ያወራችሁት
ምንድነው? ብዬ ጠየቅሁትና ምንም ሳይቸገርበት "ኰሌጅ ድረስ አስተምረዋለሁ
ነው ያለውና በርትተህ ሥራ።" ብሎ የራሱንም ምክር ጨምሮ ነግሮኝ ነበር። ያን
ምኞት እውን ለማድረግ ግን ከላይ የጠቀስኳቸውና ከትዳር ምሥረታ ጋር የተያያዙ
ጉዳዮች አጨናግፈውታል።

ጋሼ ተሰማ በነበረው መልከ-ግቡነት፣ ከሰው ሁሉ ጋር በነበረው ተወዳጅነትና
ተቀባይነት ወዳጅ ዘመድ ሁሉ "የእከሌን ልጅ" ብሎ ያልተመኘለት፤ ልጃቸውንም
እንዲያገባ አፍ አውጥተው የጠየቁት ከአንድም ሁለት ቤተሰብ አውቃለሁ።
ነገር ግን ያንን ሁሉ መልካም ምኞት ቁም ነገር ሳይል ወ/ሮ ሙሉ ወርቅ አጥናፌ
የተባሉትን ባለ መጠጥ ቤት ወደ ቤቱ አስገባ። "የማንን ቆንጆ ያገባ ይሆን? ምን
ዓይነት ሠርግ ይደገስ ይሆን?" የተባለለት ጎበዝ በሌሎች ዘንድ የተቸረው ግምት
እንደ ገለባ በኖ ቀርቷል።

ስለ ሌሎች ስኬት ሲል የራሱን ምቾት ይሰዋ የነበረው ተሰማ አሩሲ በ1987 ዓ.ም
ሕልፈተ ሕይወቱ ድረስ "ልጅ አልወለድሁም - ወራሽ የለኝም" ሳይል ከእኚህ
ሴት ጋር የሕይወቱን ዘመን አሳልፎአል። አንድ ለብዙ ሰው የማይታወቅ ሚስጢር
ነበረው። ይኸውም ድሮ ጂማ ይማር በነበረ ጊዜ በደረሰበት የመኪና አደጋ ምክንያት
አንድ እግሩ ጉልበቱ ላይ ተመትቶ ስለነበረ ቢድንም ትንሽ ያስነክሰዋል። እርሱ ግ
በአለባበሱም ሆነ በአካሄዱ ቄንጠኛ ስለሚባል የእግሩ ችግር ለብዙዎች የታወቀ
አለነበረም። በዚህም ምክንያት ወደ እስፖርቱ አያደላም ነበር።ይልቁንስ በፔንግ





ፖንግ፣ በዳማ እና ቼዝ በጣም ጐበዝ ነበር። አመጋገቡንም ሆነ አለባበሱን ይጠብቅ ስለ ነበር ሰውነቱ ጥብቅና ጠንካራ እድሜውን ሙሉ በውፋሬ ወይም በእርጅና ሳይርገፈገፍ አልፏል። ለሰላምታም ሲጨብጥ የእጁ ጥንካሬ ለሚጨብጠው ሰው በሚገባ ይሰማዋል። ሰውን ሲያጫውት ለዛ የሞላለትና "ኢታቋርጥ፤ "አትሂድብን" የሚያሰኝ ማግኔት ነበረው። በደርግ ዘመን አቶ ተሰማ ከትምህርት ሚስቴር ወደ አገር አስተዳደር ሚኒስቴር ተዘዋውሮ በአውራጃ አስተዳዳሪነት በጋምቤላ፣ በሚዛን ተፈሪ እና በአጋሮ አውራጃዎች አገሩንና ሕዝቡን ያገለገለ ዝነኛ ኢትዮጵያዊ ነበር። ያስጀመረኝን ትምህርት እንዳሰበው እንዳያስጨርሰኝ የባለቤቱ ጣልቃ ገብነት ቢያጨናግፈውም የትምህርቱን እድል በር የከፈተልኝን ይህንን ታላቅ ባለውለታ ሰው ሳስታውስ ኋላ ላይ ያጐደለብኝ ሳይሆን ታላቅ ባለውለታዬ ነው።

---

ገጠመኝ

---

አንድ ቀን በማለዳ ያልተለመደ ድምጽ ተሰማና ሁላችንም ሮጠን ስንወጣ የአንዷ ሚሲዮናዊት መኖሪያ ሣር ቤት በእሳት ተያይዞ ነበር። በዚያን ዘመን 1946/47 ዓ.ም. የእሳት አደጋ መኪና ያልተሰማ ነገር ነበረና ሁላችንም ሮጠን ደረስን። የቤቱ አሠራር ላዩ ሣር በጉራጌዎች ሙያ የተሠራ/የተከደነ ግድግዳው የጭቃ ልሥንና ወለሉ ጣውላ ነበር። እሳቱን ለማጥፋት በሰው እጅ የተወረወረው ውሀ ከእሳቱ አቅም ጋራ የማይመጣጠን ሆነና ዕቃ ማሸሹ ላይ ተተኮረ። ከላይ ሳሩ ከታች ጣውላው ሲቃጠል በመሐል ግድግዳው ጋለ እንጂ አልተቃጠለም ነበር። ለሚሽኑ ጊቢ ጎረቤትና አንዳንዴም ሥራ ይረዳ የነበረ አቶ ዴአ የሚባል ሁላችንም የምናውቀው ሰውና እኔ በአንድ አቅጣጫ ላዩና ታቹ ተቃጥሎ የቆመውን ግድግዳ ለመጣል ወደፊትና ወደኋላ እያዋዠቅን ስንሞክር ወደፊት የገፋነው አይንደድ እንጂ ከፍተኛ ግለት የነበረው ግድግዳ ወደኛ ተመለሰብን። እኔ ልጅም ስለነበርኩ ሮጬ ሳመልጥ አቶ ዴአ ላይ ወደቀና ከወገቡ በታች ያዘው። የተያዘው እርሱም ያመለጥሁት እኔም ጮህንና እጆቹን በእጆቼ ይዤ ለመጎተት ስታገል ሌሎቹ ደረሱና በትግል ሲወጣ ከወገቡ በታች መቃጠል ብቻ ሳይሆን ተሰብሮ ነበር። በዚያው ሥቃይ በሚሽኑ መኪና ተጫነና ሚስተር እንደርሰን ይዞት የያኔው ልዕልተ ፀሐይ ሆስፒታል ተወሰደ። ይሁን እንጂ በማግሥቱ ወይም በሦስተኛው ቀን አረፈና ያቺው መኪና አስከሬኑን ይዛ ተመልሳ ሻሸመኔ ተቀበረ። እኔ ግን አንዱ ሟች መሆን ስችል እግዚአብሔር ለራሱ ምክንያት አድኖኝ ተርፌ ከብዙ ዓመት ጉዞ በኋላ ታሪኩኝ ከአእምሮ ማስታወሻዬ ፋይል አውጥቼ እነሆ ለመጻፍ በቅቻለሁ።

ከአስከፊ ኑሮ ጋር እየታገልኩ የስድስተኛና ሰባተኛ ክፍል ትምህርቴን ጨረስሁ
በትምህርት ውጤት ግን ከ1ኛ እስከ 3ኛ በታች ወርጄ አላውቅም፡፡ ኑሮው እየመረ
ሲሄድ ከመደበኛ ትምህርት መስመር ዘወር ማለቱን መረጥሁ፡፡ ሰባተኛ ክፍ
ጨርሼ ወደ ስምንተኛ ክፍል እንደተዛወርኩ ሰሞን ጋሼ ሙላቱ ባፋ ለማማከር ወ
ኩየራ ሄድኩ፡፡ ጋሼ ሙላቱ የአክስቴ ልጅ የሆቸው የዓለሜ ባለቤት ሲሆን በዚያ
ወቅት የኤስ አይ ኤም በኩየራ ባቋቋመዉ ሆስፒታል ጤና ረዳቶችን ያሠለጥ
ነበር፡፡ ትምህርት በማቋረጤ ደስ ባይለውም ለከፍተኛ ትምህርት ወደ አሜሪ
ለመሄድ እየተጣደፈ ባለበት አጋጣሚ በጤና ረዳትነት (Dresser) እንድሠለጥ
አመቻቸልኝና ገባሁ።

ሆስፒታሉ የሥጋ ደዌ ሕሙማን የሚታከሙበት ነበር፡፡ እኔ ደግሞ ለሥልጠና
የገባሁት በባዶ እግሬ ነበር። አኔ እንኳን ካለማወቅ የተነሣ ምንም አልመሰለኝም
ነበር። በዚያው ሳምንት ሐኪም ቤት ሸርጤን (Uniform) ለብሼ ለሥራ ወደ
ወዲህ ስል አንዷ የሥጋ ደዌ ሕመምተኛ የነበረች ሴት ጠራችኝ፡፡ ጠጋ ስል ራሷ
አስታዋውቃኝ፤ የሩቅ ዘመዴ ሆና ተገኘች፡፡ "የኔ ይበቃል እዚህ በባዶ እግርህ መሆ
መልካም አይደለምና ጫማ ግዛ ብላ" አሥር ብር አውጥታ ሰጠችኝ፡፡ ሻሸመ
ከተማ ሄጄ ሰባት ብር ጨምሬ ጥቁር የዳርማር ጫማ ገዝቼ እዚያው አድርጌ ወ
ኩየራዬ ተመለስኩ። ያቺ ሴት እርሱሌ ትባል ነበር። የኮሌጅ ትምህርቴን አሜሪ
ጨርሼ ስመለስ በአባቴ በኩል ብፈልግ ባስፈልግ አጣኋት፡፡ መጨረሻ ላይ መሞቷ
ስሰማ እጅግ አዘንኩ።

የመጀመሪያውን ደረጃ የጤና ረዳትነት ትምህርቱን አጠናቅቄ የጤና ጥበቃ ፈተ
በመጠባበቅ ላይ እያለሁ ሕይወቴን በዚህ ልመራ እንደማልፈልግ ወሰንኩ
ተመልሼ 8ኛ ክፍል መጨረስ እንዳለብኝም ቆረጥሁ። ነገር ግን የት የሚለው
ከመወሰኔ አስቀድሞ አቶ ላቀው ሱላሞ የሚባል ወላጆቻችን ወዳጆች የነበሩ በዚያ





ጊዜ በአላባ ማዘጋጃ ቤት ግብር ሰብሳቢ የነበረ ሰው ለሕክምና ሆስፒታላችን መጥቶ ከረዳሁት በኋላ ትምህርት ቤት የመመለስ ፍላጎቴን ሳጫውተው "ለምን አላባ መጥተህ እኔ ቤት እያደርክ አትማርም" ሲለኝ በጣም ደስ ብሎኝ ተቀበልኩ። ታጣፊ አልጋ ስላለኝ ይዤ እመጣለሁ ብዬው በአጭር ጊዜ ውሳኔው ተጠናቅቆ ለአለቆቼ ሚስዮኖች አስታወቅሁ። ሐድሊ ወልዳክ የሚባል የግቢው ኃላፊ አላምንም ብሎ በአውቶቡስ የምሳፈርበት ድረስ ተከትሎኝ መጥቶ እያለ ሐሳቤን ለማስቀየር ሙከራ አድርጎ ነበር ግን አልሆነም።

አላባ አፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ትምህርት ቤት ድሬክተር የነበሩት አቶ አክሊሉ ኪዳነማርያም የሚባሉ ጥሩ ሰው ነበሩ። ሄጄ ስጠይቅ ወዲያው ተቀበሉኝና ትምህርቱ ተጀመረ። ማደሪያዬም አቶ ላቀው ቤት ቀጠለ። ካባለቤቱ ጋራ ከተጋቡ ከአንድ ዓመት ጊዜ ትንሽ ቢበልጥ ነው። ጋብቻዉ የተመሠረተዉ በሁለቱ መፈቃቀድ ሳይሆን በወላጆቻቸዉ ምርጫና ውሳኔ እንደ መሆኑ ገና እስኪሞራረዱ ድረስ ትዳራቸዉ ሰላም አልነበረውም፡፡ ድብድብና ጭቅጭቁ በዚያ ላይ ብዙም ያልደላት ሕፃን ልጃቸዉ ለቅሶ ተደማምሮ ቤቱ የ8ኛ ክፍል ፈተና ለመውሰድ ዝግጅት ምቹ እንዳልሆነ ለመረዳት ጊዜ አልፈጀብኝም። ምን መላ መምታት እንዳለብኝ ቶሎ መመለስ እንዳለብኝ ግልጽ ነው።

አንድ ቀን ወደ ዳይሬክተሩ ቢሮ ጎራ አልኩ፡፡ እንደወትሮው በሩ ክፍት ነበር፤ ጥላዬን አይተው ሊሆን ይችላል፤ ግን አላወቅም "ግባ" ብለው አቶ አክሊሉ በተለመደ

ከአስከፊ ኑሮ ጋር እየታገልኩ የስድስተኛና ሰባተኛ ክፍል ትምህርቴን ጨረስሁ። በትምህርት ውጤት ግን ከ1ኛ እስከ 3ኛ በታች ወርጄ አላውቅም፡፡ ኑሮው እየመረረ ሲሄድ ከመደበኛ ትምህርት መስመር ዘወር ማለቱን መረጥሁ፡፡ ሰባተኛ ክፍል ጨርሼ ወደ ስምንተኛ ክፍል እንደተዛወርኩ ሰሞን ጋሼ ሙላቱ ባፋ ለማማከር ወደ ኩየራ ሄድኩ፡፡ ጋሼ ሙላቱ የአክስቴ ልጅ የሆቸው የዓለሜ ባለቤት ሲሆን በዚያን ወቅት የኤስ አይ ኤም በኩየራ ባቋቋመዉ ሆስፒታል ጤና ረዳቶችን ያሠለጥን ነበር፡፡ ትምህርት በማቋረጤ ደስ ባይለውም ለከፍተኛ ትምህርት ወደ አሜሪካ ለመሄድ እየተጣደፈ ባለበት አጋጣሚ በጤና ረዳትነት (Dresser) እንድሠለጥን አመቻቸልኝና ገባሁ።

ሆስፒታሉ የሥጋ ደዌ ሕሙማን የሚታከሙበት ነበር፡፡ እኔ ደግሞ ለሥልጠና የገባሁት በባዶ እግሬ ነበር። እኔ እንኳን ካለማወቅ የተነሣ ምንም አልመሰለኝም ነበር። በዚያው ሳምንት ሐኪም ቤት ሸርጤን (Uniform) ለብሼ ለሥራ ወደያ ወዲህ ስል አንዷ የሥጋ ደዌ ሕመምተኛ የነበረች ሴት ጠራችኝ፡፡ ጠጋ ስል ራሷን አስታዋውቃኝ፤ የሩቅ ዘመዴ ሆና ተገኘች፡፡ "የኔ ይበቃል እዚህ በባዶ እግርህ መሆን መልካም አይደለምና ጫማ ግዛ ብላ" አሥር ብር አውጥታ ሰጠችኝ፡፡ ሻሸመኔ ከተማ ሄጄ ሰባት ብር ጨምሬ ጥቁር የዳርማር ጫማ ገዝቼ እዚያው አድርጌ ወደ ኩየራዬ ተመለስኩ። ያቺ ሴት እርሱሌ ትባል ነበር። የኮሌጅ ትምህርቴን አሜሪካ ጨርሼ ስመለስ በአባቴ በኩል ብፈልግ ባስፈልግ አጣኋት፡፡ መጨረሻ ላይ መሞቷን ስሰማ እጅግ አዘንኩ።

የመጀመሪያውን ደረጃ የጤና ረዳትነት ትምህርቱን አጠናቅቄ የጤና ጥበቃ ፈተና በመጠባበቅ ላይ እያለሁ ሕይወቴን በዚህ ልመራ እንደማልፈልግ ወሰንኩ። ተመልሼ 8ኛ ክፍል መጨረስ እንዳለብኝም ቆረጥሁ። ነገር ግን የት የሚለውን ከመወሰኔ አስቀድሞ አቶ ላቀው ሱላሞ የሚባል ወላጆቻችን ወዳጆች የነበሩ በዚያን





ጊዜ በአላባ ማዘጋጃ ቤት ግብር ሰብሳቢ የነበረ ሰው ለሕክምና ሆስፒታላችን መጥቶ ከረዳሁት በኋላ ትምህርት ቤት የመመለስ ፍላጎቴን ሳጫውተው "ለምን አላባ መጥተህ እኔ ቤት እያደርክ አትማርም" ሲለኝ በጣም ደስ ብሎኝ ተቀበልኩ። ታጣፊ አልጋ ስላለኝ ይዤ እመጣለሁ ብዬው በአጭር ጊዜ ውሳኔው ተጠናቅቆ ለአለቆቼ ሚሲዮኖች አስታወቅሁ። ሐድሊ ወልዳክ የሚባል የግቢው ኃላፊ አላምንም ብሎ በአውቶቡስ የምሳፈርበት ድረስ ተከትሎኝ መጥቶ እያለ ሐሳቤን ለማስቀየር ሙከራ አድርጎ ነበር ግን አልሆነም።

አላባ አፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ትምህርት ቤት ድሬክተር የነበሩት አቶ አከሊሉ ኪዳነማርያም የሚባሉ ጥሩ ሰው ነበሩ። ሄጄ ስጠይቅ ወዲያው ተቀበሉኝና ትምህርቱ ተጀመረ። ማደሪያዬም አቶ ላቀው ቤት ቀጠለ። ካባለቤቱ ጋራ ከተጋቡ በአንድ ዓመት ጊዜ ትንሽ ቢበልጥ ነው። ጋብቻዉ የተመሠረተዉ በሁለቱ መፈቃቀድ ሳይሆን በወላጆቻቸዉ ምርጫና ውሳኔ እንደ መሆኑ ገና እስኪሞራረዱ ድረስ ትዳራቸዉ ሰላም አልነበረውም፡፡ ድብድብና ጭቅጭቁ በዚያ ላይ ብዙም ያልደላት ሕፃን ልጃቸዉ ለቅሶ ተደማምሮ ቤቱ የ8ኛ ክፍል ፈተና ለመውሰድ ዝግጅት ምቹ እንዳልሆነ ለመረዳት ጊዜ አልፈጀብኝም። ምን መላ መምታት እንዳለብኝ ቶሎ መመለስ እንዳለብኝ ግልጽ ነው።

አንድ ቀን ወደ ዳይሬክተሩ ቢሮ ጎራ አልኩ፡፡ እንደወትሮው በሩ ክፍት ነበር፤ ጥላዬን አይተው ሊሆን ይችላል፤ ግን አላወቅም "ግባ" ብለው አቶ አከሊሉ በተለመደ



ፈገግታቸው ተቀበሉኝ። ያልተለመደ ጥያቄዬን እንዲህ ስል አቀረብኩላቸዉ:- “የማድርበት ቤት ለጥናት ስለማይመች በምንማርበት ክፍል እንዳድር ይፍቀዱልኝ” ብዬ ጠየቅኋቸው፡፡ ብዙም ሳይቸገሩበት “እንዴት ይሆናል?” አሉኝ። እኔም በደንብ አስቤበት ስለነበረ “ሸራ አልጋ አለችኝ፣ ማታ ዘርግቼ እተኛበትና ጧት አጥፌ አነሳለሁ፤ ክፍሉንም በንጽሕና እጠብቃለሁ፡፡ “መልካም” አሉኝና ለዘበኛው ለአቶ አየለ ይኸንኑ ነገሩቸው።

እኔ ሸራ አልጋዬን አስገባሁ። በየማለዳዉ ታጥፎ በአንዱ የግድግዳ ማዕዘን ይቆማል፤ እንደገና ማታ ይዘረጋል። አንዳንድ ቀን አቶ አየለ ከወዳጃቸው (ከካቲካላ) ጋራ ካመሹ “አትገባም” ይሉኛል። አንድ ቀን ሞቅ ብሏቸው ኖሮ ከኋላቸው ስመጣ “የጠቅል አሽከር” ብለው ፎክረው ማታ ማታ የሚይዙትን ጎራዴ መዘዙብኝ። እኔም ፈጥኜ እኔ ነኝ! እኔ ነኝ!! ... ብዬ በመጮኼ ለጥቂት የተረፍኩበትን ምሽት ነበር።

በእንዲህ ዓይነት ስምንተኛን ክፍል በ1951 ዓ.ም ጨረስሁ፡፡ ያኔ የትምህርት






ሚኒስቴር ፈተናዎችን ይሰጥ የነበረው በተወሰኑ ከተሞች ነበር፡፡ ከ20 በላይ ተማሪዎች ለሚኒስትሪ ፈተና ሆሣዕና ሄድን። ትምህርታችንን ለሁለት ሳምንት እየከለስን ቆይተን ፈተናውን ወሰድን። ከአላባ ሆሣዕና ያኔ መንገዱም መኪናውም ስላልነበረ በጋማ ከብት ነበር መጓጓዣው። የአባቴን በቅሎ ወንድሜ ወልዴ አምጥቶልኝ ሆሣዕና ሄደን የቆየንበትን ያህል ጊዜ ዘመድ ቤት ከበቅሎዋ ጋር ቆይቶ ከፈተና በኋላ አላባ መልሶኝ በቅሎዋን ይዞ ወደ ሚሽግዳ ተመለሰ። ስለዚህ የከፈለው መስዋዕትነት ቀላልና የሚረሳ አልነበረም።

## እንደገና አሰላ

በ1952 ዓ.ም መስከረም 18 ቀን ትምህርት ቤት ተከፈተ፡፡ የጠቅላይ ግዛቱ ዋና ከተማ የነበረችውና የራስ ዳርጌ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መገኛ የሆነችው አሰላ ከተማ ሚኒስትሪ ፈተና አልፎ በየአቅጣጫው የጎረፈውን ሁሉ ተማሪ ተቀብላ ማስተናገድ ጀምራ ነበር። ከምሥራቅ ጢቾና ሥሬ፣ ከምዕራብ ሆሣዕና፣ ሻሸመኔ፣ ኮፈሌና ነጌሌ ከሰሜን ዴራ ከደቡብ በቆጂና ከየመኸከሉም ተማሪ በየዓይነቱ ጎረፈ።

የራስ ዳርጌ ትምህርት ቤት ክፍሎቹንና አስተማሪዎቹን ማዘጋጀት እንጂ ከየአቅጣጫው የመጣ ተማሪ የት ያድራል? ምንስ ይበላል? የሚሉ ጥያቄዎች ጉዳዩ አልነበረም። መንግሥት በየወሩ ሃያ ብር እንደሚቆርጥልን ያውቃልና፡፡ ተማሪው ራሱ የሚከራይ ቤት ይፈልጋል፡፡ ሦስትም፣ አምስትም፣ ሰባትም ሆኖ በደቦ ይኖራል፤ አንዳንድ ጊዜ ቤቱ የሚችለው ያህል ሰው በአንድ ክፍል ውስጥ ይጠቀጠቃል፤ ኪራዩን እኩል ይጋራል፡፡ የቦንዳ አልጋ፣ የሣር ፍራሽ ዋና የተማሪ ቁሳቁስ ነበር፡፡ የሽሮና የድንች ወጥ ደግሞ ዋና ምግብ ነበር፡፡ ዋጋቸው ከ10 እና 15 ሣንቲም ዘልሎ አያውቅም፡፡ ከመንግሥት በየወሩ የሚሰጠንን ሃያ (20) ብር አቻችሎ ወር መድረስ ከመደበኛዉ ትምህርት ሌላ ግሩም የሕይወት ልምምድ መድረክ ነበር።



ፈገግታቸው ተቀበሉኝ። ያልተለመደ ጥያቄዬን እንዲህ ስል አቀረብኩላቸዉ፡-

9ኛን ክፍል ትምህርት በእንደዚህ ዓይነት ጀመርንና ጨረስን። ወደ 10ኛ ክፍልም ተዛውሬ ለክረምቱ ትምህርት ቤት ሲዘጋ ወደ ወላጆቼ ቤት በመሄድ ፈንታ ኩየራ ተመልሼ በጤና ረዳትነት ሁለት ወር ሠራሁ። ብዙም ባትሆን ያቺ የሁለት ወር የSIM ደመዎዝ በወር 30 ብር ለመጓጓዣ ጠቀመኝና አዋሳንና ይርጋለምን ጎብኝቼ እዚያ የነበሩትን አስቴር ዋኬሮን፣ ትዕዛዙ መጇን፣ ተሰማ ቀልቦሮና ሌሎችንም አገኘሁዋቸው። ከዚያም ወደ ኩየራ ተመልሼ ለአሰላ የመልስ ጉዞና 10ኛ ክፍል ለመጀመር ሻንጣዬን አዘጋጀሁ። ቀኑ ሲደርስ ኩየራ አብሬአት የቆየሁትን የጋሽ ሙላቱ ባፋን ባለቤት ወ/ሮ ዓለሜንና ልጇን ሚዛንን በታላቅ ናፍቆት ተሰናብቼ ወደ አሰላ አመራሁ::

አዲሶችም የቀድሞ ተማሪዎች በየአቅጣጫው አሰላ መግባት ጀምረዋል። ከአዲሶቹ መጤዎች ሁለት ጓደኞቼ ጴጥሮስ ወንታሞና ሳሙኤል ሄራሞ ነበሩ። ሁለቱም በልጅነታቸው አሰላ ስዊዲሽ ሚሽን ትምህርት ቤት ስለተማሩ አካባቢዉ እጅግም አልተለወጠባቸውም። ሁለቱ 9ኛ ክፍል እኔም 10ኛ ገባንና ትምህርቱ ተጀመረ።



**10ኛ ክፍል፤ ተማሪ 1954 ዓ.ም**

በዚያው ሳምንት ውስጥ ያልጠበቅሁት ስልክ ከይርጋዓለም ተደወለ። የደወለችው ዘመዴ አስቴር ዋኬሮ ከፍ ብዬ የጠቀስኳት ናት። ሌላውን አስተዋውቃኝ ስልኩን አቀበለች። ያ ሰው ቶርሰን የሚባል የኖርዌይ ተወላጅ ነዉ:: በወቅቱ የይርጋዓለም መምሕራን ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር ነበር። ጥያቄው “ለአንድ ዓመት አስተማሪ





እንፈልጋለንና መምጣት ትችላለህ ወይ?” የሚል ነበር:: አጋጣሚውን ያሰላሰልኩት መልሱን በአዎንታ ከሰጠሁ በኋላ ነበር::

ወንድሜ ወልዴ አራተኛ ክፍል መግባት ደርሷል:: የግድ ሊማር ወደሚችልበት አካባቢ መሄድ አለበት:: ያለበለዚያ አቋርጦ ቤት መቀመጥ ግድ ሊሆንበት ነዉ:: ስለሆነም እርሱን መርዳት ይገባኛል:: የስልኩ ጥሪና የአወንታ መልሴ ይህንን ጥያቄ መለሰልኝና 10ኛን ክፍል አንድ ሳምንት ተምሬ አቋረጥሁና ወደ ይርጋዓለም ጉዞ ጀመርኩ። የቦንዳ አልጋዬንና የሣር ፍራሼን እነዚያ ሁለቱ ጓደኞቼ ወረሱኝ:: ወልዴ ደግሞ ዓለሜ ጋ ሻሸመኔ መጥቶ ትምህርቱን ቀጠለ።

## ይርጋ ዓለም

ጊዜዉ 1953 ዓ.ም መጀመሪያ ነበር። ትምህርት ቤቶች ተከፍተው ሥራቸውን ከቀጠሉ የመጀመሪያው አንድ ሳምንት አልዕል። የመስከረም ፀሐይ በማለዳ በለመለሙ ዕፅዋት ላይ የረጨዉ ብርሃን ሌሊቱን ሰፍሮ ያደረውን ጤዛ ወዝ አስመስሎታል። የአየሩ ለብታ ፊት ይዳስሳል። መኪናዉ ከኩየራ - ሻሸመኔ - አዋሳ - አቦስቶ - ብሎም የጊዳቦን ወንዝ ተሻግሮ ያለውን አቀበት ወጣ:: ለመታየት የማትቸኩለዉ ይርጋዓለም ከተማ በዝግታ ብቅ ማለት ስትጀምር የአድራሻዬ መዳረሻ ስለሆነ “ወራጅ አለ” ስል አሽከርካሪው መኪናውን አቆመ:: ሻንጣዬን ተረክቤ ከዋናው መንገድ በስተግራ በኩል ብዙም ሳይርቅ ወደ አለው የኖርዌጂያን ሚሽን ግቢ አመራሁ።

ቀኑ እሁድ ስለነበረ በግቢው ውስጥ ተማሪው፣ አስተማሪው፣ ፈረንጁ፣ አበሻው ተቀላቅሎ ከአምልኮ ሲወጣ ነበር የደረስሁት። ወዲያው በሐሳባቸው ይጠብቁኝ የነበሩ ዘመዶቼ አስቴር ዋኬሮ፣ ተሰማ ቀልቦሮ፣ መሰለችና ማርታ ዋኬሮ በሞቅታ ተቀበሉኝ:: ቀጥሎም ከሚስተር ቶርሰን ጋር አገናኙኝ። “እንኳን በደህና መጣህ” ብለው የተቀበሉኝ ሚስተር ቶርሰን ስለ ሥራዬ ከምሳ በኋላ ለመነጋገር ቀጥረውኝ



10ኛ ክፍል፤ ተማሪ 1954 ዓ.ም

ተለያየን።

ማደሪያዬ ከተሰማ ቀልቦሬና ከትዕዛዙ መጃ ጋር በአንድ ቤት ለሦስት እንደሚሆን ተነግሮኝ ሻንጣዬን ወደዚያ አስገባን። ምሳችንን ከነአስቴር ጋራ በላንና ሰዓቱ ሲደርስ በቀጠሮዬ ከትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር ከሚስተር ቶርሰን ጋራ ተገናኘን። አስቀድሞ የወጣውን የትምህርቱ መርሃ ግብር ተሰጠኝ የማስተምረውም የ8ኛ ክፍል አማርኛ፣ የ7ኛ ክፍል ሂሣብና የ6ኛን ክፍል እንግሊዝኛ እንደሆነ ተነገረኝ። ለዚሁ ሁሉ ሥራ የሚከፈለኝ ደሞዝ 110 (አንድ መቶ አሥር ብር) በስልኩ ጥሪ ተነግሮኝ ስለነበረ ሌላ ድርድር አላስፈለገውም። ሰኞ ሲጠባ ከየክፍሉ ተማሪዎቼ ጋራ ተዋወቅሁና ሥራው ተጀመረ። አንዳንዶቹ ተማሪዎች ከእኔ በዕድሜ የሚበልጡና ትዳር መሥርተዋል ልጅም የወለዱም ነበሩ። ታረቀኝ አዴቦን (አሁን ዶ/ር) በዚያን ወቅት ያገኘሁት የ8ኛ ክፍል ተማሪ ሳለ ነበር::

## 10. አሁንም ትምሕርት

በ1953 ዓ.ም በአስተማሪነት ለመቀጠር ትምህርቴን ባቋርጥም የመማሩ ፍላጎት በወስጤ ሥፍራውን አልለቀቀም። ወደ አሰላ ለሦስተኛ ጊዜ ለመመለስ ግን ነፍሴ እምቢ አለች:: በይርጋዓለም ያሳለፍኩት ጊዜ የጥሩ ምግብ ጣዕም በአፍ ውስጥ እንደሚቀር እንደዚያ የጣመኝ ነበር። በጠቅላላው የነበረኝ ኅብረት (Fellowship) ትውስታ መልካም ነበር። ያንን ዓይነት ኅብረት ተለማምዶ ወደ ምድረ በዳ መመለሱ የጤና አይሆንም የሚል ስሜት በውስጤ ተሰግስጎ ነበር።

ስለዚህ ቢቻል የተሻለ አለዚያም ተመሳሳይ ከባቢ (Environment) መፈለግ ግድ ሆነብኝ። ወደ ትምህርት ቤት መመለሱ ዋነኛው ፍላጎቴ ሆኖ ግን የት የሚለው ጥያቄ ነው ያልተመለሰልኝ። የመጀመሪያው ሙከራ ደብረ ዘይት የነበረው ኢቫንጀሊካል ኮሌጅ (EvangelicaL College) ነው። ማመልከቻዬን ከካርዴ ጋር አስገባሁ።





መልሱ "የሳይንስ ማርክህ በቂ ስላልሆነ አንቀበልህም" ሆነብኝ። እምና አመልክቼ የነበረው የጂማ እርሻ ትምህርት ቤት መከፈቻ አስቀድሞ በነበረው እሁድ ጧት ራስ ተሰማ ሠፈር ወዳለው SIM ለእሁድ አምልኮ ሄድሁና አልቆ ወጥቼ ፈንጠር ብዬ ቆሜ የማውቀው ሰው ብዬ በዓይኔ ስፈልግ Kevin Occoner የሚባል ሻሸመኔ የማውቀው የነበረ ሚስዮናዊ ጋር ከሩቅ ተያየንና ተገናኘን። "ምን አመጣህ" ሲለኝ ትምህርት ቤት የመግባት ፍላጎቴን ነግሬ ጂማ ያመለከትሁት መልስ አልመጣልኝም አልሁት። እርሱም ቶሎ ብሎ "እዚያ አስተማሪ የሆነ ሰው አለ" ብሎ ፈልጎ አገኘውና ይዞት መጣ። ጉዳዬን እንደገና ስነግረው "እኔ ነገ (ሰኞ) እሄዳለሁ። ጠይቄ መልሱን በOcconer በኩል ማክሰኞ ዕለት ደውዬ አሰማሀለሁ። አለኝና አመስግኜ ተለያየን። ማክሰኞ ከሰዓት በኋላ ወደ SIM ተመልሼ ሄጄ የጅማው አስተማሪ ደውሎ እዚያም እንዳልተቀበሉኝ እንደነገረው ነገረኝና "ግን; አለ ሚስተር Occoner "ግን ክርስቲያን ትምህርት ቤት ካገኘ እኔ እከፍልለታለሁ" ብሏል ሲለኝ ልቤ በደስታ ተሞላ:: የቀረውና እኔ የማውቀው ክርስቲያን ትምህርት ቤት ናዝሬት ያለው Bible Academy ብቻ ሳስታውሰዉ "እንግዲያውስ ደብዳቤ ልጻፍላቸው" አለኝ:: በማግሥቱ ሄጄ ደብዳቤውን ተቀብዬ ወደ ናዝሬት አመራሁ።

እዚያ ስደርስ ዳይሬክተሩ ወደ አዲስ አበባ ሄደዋል ተብዬ ዛፍ ጥላ ስር ተቀምጬ ስጠብቅ ዋልሁና ሲቆይብኝ ወደ ናዝሬት ኃይለማርያም ማሞ መታሰቢያ ሆስፒታል የማውቃቸው ሰዎች ስለነበሩ እዚያው አደርኩ። በበነጋው ወደ ሦስት ሰዓት አካባቢ የትምህርት ቤቱን ዳይሬክተር አገኘሁት። "ማመልከቻህንና ያመጣኸውን ደብዳቤ አይተን ተቀብለንሃል" አለኝ። የደስታዬን መጠን ልገልጸው አልችልም። በ1953 ዓ.ም ራስ ዳርጌን ስለቅ መቀየር የጀመረው የሕይወቴ አቅጣጫ በዚህ መልስ ታተመልኝ:: 10ኛንና 11ኛን ክፍሎች ጨርሼ 12ኛን ክፍል በተመላላሽ እየተከታተልኩ በናዝሬት ኃይለማርያም ማሞ መታሰቢያ ሆስፒታል የገንዘብ ተቀባይነት ሥራ ያዝሁ።

ወደ መጽሐፍ ቅዱስ አካዳሚ መምጣት ከነላጵሶ ድሌቦ (ፐሮፌሰር)፣ ደበላ ብሪ (ቄስ/ዶር)፣ ዮሐንስ ለታ (ሌንጮ ለታ) እና ከሌሎችም ጋራ በአንድ ከፍል የትምህርት ገበታ እንድንቋደስ እድል ሰጠን። ሌንጮ ለታ በክፍላችን በዕድሜ ትንሹ ሲሆን በሁለም ትምህርት በጣም ጎበዝ ተማሪ ነበር። አማርኛ ይጥላው አይጥላው፣ ወይም እርሱ አማርኛን ይጥላው አይጥላዉ አላውቅም። በአማርኛ ዝቅተኛ ነጥብ ነበር የሚያገኘዉ:: ታዲያም መከፋትንና ቧልትን በቀላቀለ ቅላጼ "አማርኛ  ሰጊርጌት (Segregate) አረገኝ" እያለ በአማርኛ ያገኘውን ማርክ ይዞ በረንዳ ለበረንዳ ይዞር እንደ ነበረ አስታውሳለሁ። ዘወር ብዬ ሳስብ "ምናልባት ኋላ ላሳየዉ ፖለቲካዊ ዝመት መነሻውን ካደላደሉለት ጉዳዮች አንዱ ይኼዉ ይሆንን እላለሁ?::

## ጃንሆይ በድንገተኛ ጉብኝት

ከነዚህ ቀናት በአንዱ ነበር በአራት ሰዓት ለዕረፍት ወጥተን ሳለ ከፊት ለፊታችን በአለው ወንጂ መንገድ ላይ መብራታቸውን ቦግ - ድርግም እያደረጉ በከፍተኛ ፍጥነት ይሮጡ የነበሩ ሞተረኞችና መኪናዎች አየን:: ወደ መንገዱ ዳር ሮጠን ስንደርስ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ናቸዉ:: የወንጂ ስኳር ፋብሪካን ለመጎብኘት እየሄዱ ነበር:: መኪናቸውን አቁመው "ምንድናችሁ?" ብለው ጠየቁን። በብዙ ድምጽ ተማሪዎች ነን፣ ትምህርት ቤታችንን ይጎብኙልን ብለን ጠየቅናቸዉ:: እሺ ስንመለስ እናይላችኋለን  ብለውን ቀጠሉ:: እኛም ቶሎ ብለን ለዳይሬክተራችን ነግረናቸው እንዲሁም የሚስተካከለውን አስተካከለንና ግቢውን አሳምረን ንጉሠ ነገሥቱን ለመቀበል ተዘጋጀን። ትንሽ እንደ ጠበቅን ተመልሰው መጡ።

ተሰልፈን ተቀበልናቸው:: "በየከፈላችሁ እናያችኋለን" ሲሉን ሁላችንም ወደየከፍላችን ሮጠን በየወንበሮቻችን ተቀመጥን። ወደ እኛ ክፍል እንደገቡ "ትምህርት ቤታችሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ይባላል፤ እንግዲያዉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄ እንጠይቃችኋ?" ሲሉን የሁሉም መልስ "አዎን" ሆነ::





ሁለት ጥያቄዎች ጠየቁን። የመጀመሪያው ከትንቢተ ኢሳይያስ ሁለተኛው ከማቴዎስ ወንጌል ስለጌታ ልደት ጠየቁን። በሽሚያ ከወጡት እጆች መካከል የጌታሁን ድሌቦና የሳሙኤል ሱልጣንን ተመረጡ:: ሁለቱም በትክክል መልሱላቸው:: አመስግነው የቀሩትን ክፍሎችና ምግብ መመገቢያችንን ዞረው ጎበኙ።

በምግብ ቤታችን የነበረውን ፒያኖ ሲመለከቱ "ትዘምራላችሁ?" ብለው ጠየቁ:: አዎንታችንን እንዳረጋገጡ "እስቲ ዘምሩ" አሉ:: ዓለማየሁ ሐብቴ ፒያኖው ላይ ጉብ አለበትና አንጣጣው። አንድ የእንግሊዝኛ መዝሙር Wonderful grace of Jesus የሚል ጣፋጭ ዜማ ያለውና የሚደጋገም Chorus ያለውን በኅብረ ዜማ (በአራት ዓይነት ድምጽ) ዘምረንላቸው:: አመስግነውን "በርትታችሁ ተማሩ" ብለው ሊወጡ ሲሉ ልዑል አልጋወራሽ ወደ ወጥ ቤታችን ዘወር ብለው:-

"የዛሬው ምሳ ምንድን ነው?" ብለው ጠየቁ::

"ልዑል ሆይ ፓስታ ነው" የወጥ ቤቱ ኃላፊ አቶ በላይ ነበር:: "መቅመስ ይቻላል?"

"እዎ!" በፍጥነት በሳህን አምጥቶ ሰጣቸው፤ በሹካ ወስደው እያጣጣሙ

"ሁሌም እንደዚህ ነው የምትመገቡት?"

"አዎ!" ብዙ የተማሪ ድምጾች::

ከአዳራሹ እንደ ወጡ ጃንሆይ ቆም ብለው በግራ በኩል በብሎኬት መሠራት ተጀምሮ የቆመ የሕንፃ ጅምር ተመለከቱ:: ጅምር ሕንፃዉ ምን እንደሆነ ዳይሬክተራችንን ቸስተር ዌንገርን ጠይቁአቸው:: ዶርሚቶሪ ጠቦ ተጨማሪ እየተሠራ መሆኑን፣ ገንዘብ እስኪገኝ የቆየ እንደሆነም አስረዷቸው ግርማዊነታቸውም "ተመልሰን እንጎበኛችኋለን" ብለው አሰናብተውን በመጡበት አኳኋን ተመለሱ። የዚህ ድንገተኛ ወሬ ሳይበርድ በሦስተኛው ቀን አንዲት ውሃ ሰማያዊ አዲስ ፎልስዋገን መኪና ወደ ት/ቤቱ ስትዞር ተማሪው ሁሉ "የማን ዘመድ ወይስ እጮኛ ይሆን?" በሚል የጥያቄ ዓይን ስንከታተል ሰተት ብሎ ወደ ዳይሬክተሩ መኖሪያ ዘበኞች

አመላከተዋቸው ሄደው ምንም ያህል ሳይቆዩ ተመልሰው ሄዱ። በእራታችን ላይ ቸስተር ዌንገር መጡና "ማስታወቂያ አለኝ" በማለት የተማሪውን ጸጥታ ካገኙ በኋላ "ቅድም መጥታ የነበረችው መኪና የጃንሆይን መልእክት እንዳመጣችና መልእክቱም የዶርሚቶሪውን ሕንፃ ማስጨረሻ እንዲሆን አምስት ሺህ (5000) ብር ልከውልናል" ሲሉ ቤቱ በጭብጨባ ተስተጋባ።

ከላይ ከተጠቀሰው አጋጣሚ ሌላ ሁለት ንጉሣዊ ጉብኝት አጋጥሞን ነበር። አንዱ ኬንያ ነፃነትዋን ልታገኝ አንድ ሳምንት ሲቀራት ፕሮዚዳንት ሊሆኑ ያላቸዉ ጆሞ ኬነያታ ኢትዮጵያን በጎበኙበት አጋጣሚ ነበር፡፡ ጃንሆይ ወንጂን ለማስጎብኘት ሲወስዷቸው የመኪኖቹን ብዛትና ሞተረኞቹን ስናይ እንደልማዳችን ሮጠን ወጣን፡፡ መኪናቸውን አቁመዉ እንደ ልማዳቸዉ "ስንመለስ" ብለውን አለፉ።

የጆሞ ኬንያታ ገጽታ አይረሳኝም። የተቆጣጠረው ፂማቸው፣ የያዙት ነጭ ጭራ፣ በዶቃና ጨሌ ያጌጠ አጭር ዱላቸዉ፣ በርበሬ የመሰለ ዓይናቸውና የፈረጠመው ሰውነታቸው ከተርታዉ የአገራቸዉ ሰዉ ልዩ ያደርጋቸዋል፡፡ ከአጃቢዎቹ አንዱ ታዋቂ የነበረው ጋዜጠኛ አሳምነው ገ/ወልድ ነበር። እኔ አሰላ ራስ ዳርጌ 1ኛና 2ኛ ክፍል ስማር እርሱ 5ኛ ወይም 6ኛ ተማሪ ነበር። ሊሄዱ ሲሉ አሳምነው ተማሪዎቹን በዝግታ ድምጽ ወደ መኪናው ለመግባት ሲሄዱ "ኡሁሩ ኬንያ ብላችሁ ጩኹ" ብሎ ነገረን፡፡ ያ ሁሉ ተማሪ እንደተመከረው አንዴ ሲያስተጋባ ጆሞ ኬንያታ በሁለቱም እጃቸው የያዙትን ዱላና ጭራ ወደ ላይ አንስተው "ኡሁራ ኬንያ" በማለት ጮኸ ብለው ተናገሩ፡፡ ቀጥሎም ወደ እኛ ጠጋ ብለዉ እጃቸው ሊያቅፍ የቻለውን ያህል ተማሪዎቹ ትከሻ ላይ አሳርፈው ፎቶግራፍ ተነሡ። ከብዙ ዓመታት በኋላ የወርልድ ቪዥን ብሔራዊ ዳይሬክተር ሆኜ ሳለ ለሥራ ናይሮቢ ሄጄ ነበር፡፡ ታዲያ ትዝታዬን ለአገሩ የሥራ ባልደረቦቼ ሳካፍላቸዉ "ያ ፎቶ በጋዜጣ ወጥቶ አይተነዋል፤ ግን ውሸት ወይም ለፖለቲካ ፕሮፖጋንዳ የተዘጋጀ ነዉ ብለን ነበር"





ያሉኝን አስታውሳለሁ።

ሦስተኛው የዚህ ዓይነት ንጉሣዊ ጉብኝት ጋር የተያያዘዉ ታንዛኒያ ነፃ ከመውጣቷ በፊት እጩ ፕሬዚዳንት የነበሩት ጁሊየስ ኒሬሬ ጋር ነበር። ሁሉም ነገር እንደ አለፉት ጉብኝቶች ሲሆን ጆሞ ግዙፍ ኔሬሬ መጠነኛ ሰውነት ሲኖራቸው ጆሞ ተደሳችና ደስታቸውን ገላጭ፣ ኔሬሬ ደግሞ ጭምት መሆናቸዉ ነበር። ከዚህ ጉብኝት በኋላ ከየረርና ከረዩ አውራጃ ት/ቤቶች ጽ/ቤት ለትምህርት ቤታችን ደብዳቤ ተጽፎ የመጣውን እንግዳ ሁሉ ተማሪው እየወጣ ማስቆም የማይገባ ድርጊት መሆኑ ስለታመነበት ድርጊቱ እንዲቆም ተደረገ።

## የማትሪክ ፈተና

አሥራ አንደኛን ክፍል ከጨረሱኩ በኋላ እንደገና የቤተሰብን ችግር ለመካፈል የሙሉ ጊዜ ተማሪነቴን ማቋረጥ ነበረብኝ። በጊዜዉ በሁለት የክረምት እረፍት በጤና ረዳትነት ለሠራሁበት ለናዝሬት ኃይለማርያም ማሞ መታሰቢያ ሆስፒታል ቤተኛ ነበርኩ፡፡ የገንዘብ ተቀባይነት ሥራ እፈልግ እንደሆነ በአካል ጠርተዉ ያናገሩኝ የሆስፒታሉ አስተዳደር ኃላፊ ዶ/ር ኤሽልማን ነበሩ። አሁንም መልሴ "አዎን" ነበረና ወደ ትምህርት ቤት በመመለስ ፋንታ ወደ ሥራው ዓለም ተሠማራሁ።

ይሁን እንጂ የትምህርቱ ፍላጎት ከስሞ ሳይሆን በሁለንተናዬ በግ ብሎ እየነደደብኝ ግን መልኩን በቀየረ ሁኔታ መቀጠሉን መረጥሁ። ከሥራ አለቆቼና ከአስተማሪዎቼ ጋራ በመስማማት በሳምንት የተወሰኑ ክፍሎችን በተመላላሽነት እከታተል ችል ዘንድ በሥራ ገበታ በማልገኝበት ጊዜ ተከተውኝ የሚሠሩትን ሰዎች ሆስፒታሉ አዘጋጀልኝ፡፡ በቁልፍ የትምህርት ክፍሎች ወደ ትምህርት ቤት የምመላለስባት ብስክሌት በአንድ መቶ ሀያ አምስት /125/ ብር ገዛሁ፡፡ ከሆስፒታሉ እስከ ባይብል አካዳሚ የነበረውን ስድስት ኪሎ ሜትር ደርሶ መልስ በሳምንት ሦስት

ቀን እየተመላለስኩ ትምህርቱንም ሥራውንም ጎን ለጎን ማስኬድ ቻልኩ። ይህም በመሳከቱ ነዉ ወንድሜ ወልዴ ወደ ናዝሬት መጥቶ ትምህርቱን ሊቀጥል የቻለዉ። እዚህ ላይ ቆም ብዬ የወጣትነቴ የሕይወትና የትምህርት "አንጓዎች" ካንባቢ ጋር ብቆጥርሳ!

- ቅድመ መደበኛ ትምህርት፣ አንጋጫ፣ ዱራሜ፣ በቢቶ፣
- አሰላ፣ አላባ፣ እንደገና አሰላ . . .
- ከ7ኛ ክፍል ወጥቶ ጤና ረዳትነት ትምህርት ቤት መግባት፣
- ከ10ኛ ክፍል ወጥቶ አስተማሪ መሆን፣
- 10ኛ ክፍል ተመልሼ ለመቀጠል ዕድሉ መገኘቱ፤
- የማላውቁና የማያውቀኝ ሰዉ ክፍያውን መሸፈኑ፣
- ከ11ኛ ክፍል እንደገና አቋርጦ ሥራ መያዝ፣
- እየሠሩ ትምህርቱን ተከታትሎ ወደታሰበውና የፍጻሜው መጀመሪያ የሆነውን ጫፍ መጨበጥ፤ . . . አቤት!!!

ይህ ሁሉ በኔ ዕቅድ ብቻ ተከናወነ ብል ከማለዳው ጉዞዬ ጀምሮ አብሮነቱን የለገሠኝን ጌታዬንና አዳኜን መርሳት ይሆንብኛል። አንድዬ ይህንን ሁሉ አደረገልኝ ከማለት በተቀር ሌላ ምን እላለሁ!? ክብርና ምስጋና ለእርሱ ይሁን፡፡ ወደ ማትሪክ ፈተና ልመለስ።

ሠራተኛና ተማሪ የሆንኩት 1956 ዓ.ም ነበር። በየዓመቱ የትምህርት መጨረሻ ላይ ነው የማትሪኩ ፈተና የሚወሰደውና በግንቦት ወር ፈተናው መጣና ፈተናውን ወሰድሁ። ፈተናውን እንድወስድ የተመደብሁት ናዝሬት አፄ ገላውዲዎስ ትምህርት ቤት ነበር። ጊዜው መጥቶ አለፈ። አሁን የሚቀረው በትዕግሥት ራስ እያከኩ ውጤቱን መጠበቅ ነበር። እንዴት እንደሆነ አላውቅም እንጂ ያኔ የመደበኛው ተማሪዎች ውጤት በየትምህርት ቤቱ ከታወጀ በኋላ በግል የተፈተኑት ደግሞ





ወደ ትምህርት ሚኒስቴር ሄደው በተፈተኑበት ቁጥር ማለፍ ያለማለፋቸውን ይጠይቃሉ። እኔም በዚሁ መሠረት ሄጄ ቁጥሬን አሳይቼ ከሰርተፊኬቶች ቁልል መሃል የኔ ተመዝዞ ወጣ። ሰውዬው ሳይሰጠኝ በፊት ውጤቱን መልከት አረገና ቀና ብሎ አይቶኝ "ጥሩ ነው" ብሎ ሰጠኝ፡፡ እጅ ነስቼ ተቀበልሁና የረዳኝን አምላኬን እዚህም ያደረሰኝን እያመሰገንሁ ዝለል ዝለል የሚለኝን ስሜቴን በይሉኝታ ልጓም ገትቼ ውስጤ ግን መዝለል ብቻ ሳይሆን እየቦረቀ ወጥቼ ሄድኩ። ወደ ናዝሬትም በደስታ ተመልሼ ሥራዬን ቀጠልሁ።

## ll. ባይብል አካዳሚ - ከትምሕርቱ ሌላ

ወደ ናዝሬት ባይብል አካዳሚ መምጣት የከፈተልኝ ሌላው ዕድል ቀሪውን ዘመኔን ሙሉ ሕይወቴን የቀረጸው የምላው የወንጌል እና የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በር ነው። ትምህርት ቤቱ ለዚህ የተሰጠና የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለማፍራት ታልሞ የተጀመረ ነበር። Evangelism and Personal Development የሚባል ትምህርት በክፍል ሲሰጥ የልምምዱም መስክ ከትምህርት ቤቱ አጥር ውጭ ባሉት አጎራባች መንደሮች ጀምሮ እስከ ወንጂና ሸዋ ስኳር ፋብሪካዎች ድረስ ይወስደን ነበር። በተለይም ወንጂና ሸዋ በኋላም መተሃራ የስኳር ፋብሪካዎች ከተቋቋሙ በኋላ የሰው ኃይል ምንጫቸው ከምባታና ሐዲያ እንዲሁም ከወላይታ ስለሆነና እነዚህ ሁለቱ አውራጃዎች ከኢጣሊያን ወረራ አስቀድሞ በወንጌል የታነጹ ስለነበረ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የሚያመልኩበትን ሥፍራ መርጦ ማመቻቸት ማደራጀትም ሥራችን ነበር።



በዚህምምክንያትበሦስቱምቦታዎች የዚያኑ ያህል ዕድሜ ያስቆጠሩ ቤተ ክርስቲያኖች ተመሥርተው የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አጥቢያዎች ሆነው ይሠራሉ።

ያኔ ስንጀምር በእግር፣ በፈረስ፣ በብስክሌት ብሎም በመኪና እየተጓዝን እናደራጅና እናስተምር ነበር። ለሾንኮራው እርሻ ሠራተኞች የተሠሩአስራሁለትመንደሮችእሁድ እሁድ እየሄድን የምናገለግል አስራ ሁለት የባይብል አካዳሚ ተማሪዎች ነበርን። ላጺሶ ድሌቦ አንዱ ነበር።እነዚህን በመሪነት ሳገለግል በአንዴ አስራ ሦስት ሰው የምትጭን የኃይለ ማርያም ማሞ ሆስፒታል ቫን መኪና ከነሹፌሩ ተውሰን አሥራ አንዱን በየመንደራቸው ካወረድን በኋላ እኔ 12ኛው ሆኜ ወደ አንዱ መንደር እሄዳለሁ። ላጺሶ ቅዳሜውን ሄዶ አድሯል፡፡እኔ ስጨርስ እንደገና ከአስራአንዱም መንደር በመኪናው ዞረን ሰብስበን ወደ ትምህርት ቤታችን እንመለስ ነበር። የጸሎት ቤቶቹ ከተቋቋሙ በኋላ የየራሳቸውን አገልጋዮች ሲያፈሩ በየሳምንቱ መመላለሳችን አብቅቷል። ይህን ርዕሰ ጉዳይ ከመቋጨቴ በፊት በዚያው ሰሞን ስለደረሰብኝ የመኪና አደጋ ጥቂት ልበል፡፡ ከእነዚያ ጉዞዎች በአንዱ እሁድ ማለዳ መኪናውን የሚያሽከረክርልን ቀድሞው የክብር ዘበኛ ጦር ባልደረባ የነበረዉ መቶ አለቃ በቀለ ጭምጭ አይበሉ ይባል ነበር። “የቸገረው እርጉዝ ያገባል” እንደሚባል ሆኖ ነው እንጂ የመንዳቱን ችሎታ ሳንነሳም ገምተነው ነበር።





እንዳይሆን ሆነና ነፍሳችንን በእጃችን ይዘን እንደምንም መንደሮቹን አዳረስን፡፡ አገልጋዮቹን በየምድብ ሥፍራቸዉ ካወረድን በኋላ ወደ እኔ ምድብ መንደር አመራን፡፡ ያለልክ ሲፈጥን እባክህ ዝግ በል መዞሪያችንን እየደረስን ነው ስለው አልሰማኝም፡፡ መጠምዘዣውን ሲቃረብ ጮክ ብዬ “ቀንስ! ፍጥነት ቀንስ!” እያልኩት በመጣበት ፍጥነት ጠመዘዘ፡፡ በሰከንድ ሽራፊ በቀኛችን በኩል ባለው የውሃ መሄጃ ቦይ (አርጂን) ውስጥ መኪናው በአፍንጫዉ ተደፋ፤ ከኋላው ወደ ላይ ተሰቀለ፡፡ እኔና ሹፌሩ ወደፊት ተገልብጠን ሳንሞት ተረፍን። ያኔ የተናጋዉ ወገቤ ለዓመታት ሲያሰቃየኝ ኖሮ ከ25 ዓመት በኋላ ጌታ ፈወሰኝ፡፡የደረሰብንን አደጋ ለእነዚያ አሥራ አንዱ ጓደኞቼ የምናገርበት ምንም የመገናኛ ዘዴ አልነበረንም፡፡ የወንጂ ፀሐይ ሲወቅራቸዉ ውለዉ ተስፋ ሲቆርጡ በእግርና በተገኘው መንገድ ሁሉ ከሾንኮራው እርሻ ወጥተው ወደ ናዝሬት ተመለሱ። እንደ ዛሬው የእጅ ስልክ ቀርቶ የግድግዳውም በውል ያልነበረበት ዘመን ስለነበረ የስሚ ስሚ ነበር ያጋጠመንን አደጋ የተረዱት፡፡ እኔና መቶ አለቃ በቀለን ዶ/ር ኤሽልማን በሌላ መኪና መጥተዉ መለሱን፡፡



# ምዕራፍ አምስት
# ትምህርትና ቤተ ክርስቲያን

## 12. ቀጣይ ትምህርቴና ሜኖ-ናይትነቴ

ያ ጠመዝማዛው ጉዞዬ በአሰላ፣ በሻሸመኔ በአላባ አድርጎ ናዝሬት አደረሰኝ። ዓመተ ምህረቱ 1954 ነው። አሰላ ራስ ዳርጌ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 10ኛ ክፍል ጀምሬ ያቋረጥሁትን ትምህርት ናዝሬት በነበረው ባይብል አካዳሚ መቀጠል ቻልሁ። ይህን ትምህርት ቤት የሚመራው ሜኖናይት የሚሲዮን ተቋም ነበር:: በረፎርሜሽን ዘመን በማርቲን ሉተር የተጀመረውና "ርቆ አልሄድም" በማለት ሜኖ ሳይመንስ (Menno Simons) ኮንራድ ግረብል (Conrad Grebill) እና ሌሎችም የተመሠረተ ነው። ሉተር እንዳለው "ሰው በእምነት ይድናል። የሚለውን እውነት ተቀብለው ከዚያስ በኋላ፡ የሚል ጥያቄ አንሥተው፤ "ወንድምህን እንደራስህ ውደድ" የተባለው ትዕዛዝ በሰው ሕይወት መተግበር ይኖርበታል፤ ስለዚህም "ሰውን መግደል አግባብ አይደለም;። በማለት ካስተማሩት ዶክትሪን የተወለደ ቤተ እምነት (Denomination) ነው። ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 13 ከእራት በኋላ የሐዋርያቱን እግር ያጠበው ሥርዓት፤ ከቅዱስ ቁርባን ሥርዓት በኋላ መደረግ እንዳለበት የሚያምኑና የሚለማመዱም ናቸው። እነዚህን ሜኖናይት የተባሉት እንደ "ሉተራውያን" በራሳቸው ሳይሆን "ሜኖ-ናይት" የሜኖ ተከታዮች ብለው የሰየሙአቸው ተቃዋሚዎቻቸው ነበሩ። "ክርስቲያን" የሚለው ስም የተገኘውም ከተቃዋሚዎች እንደሆነ ሁሉ ማለት ነው።

ወደ ባይብል አካዳሚ ስገባ መንፈሳዊ ሕይወቴ በፍጥነት አላደገም። ይሁን እንጂ መሠረታዊ የሕይወት ዕድገት አስፈላጊውን ሁሉ ንጥረ ነገር አግኝቷል ማለት እችላለሁ። በክፍል ውስጥ ይሰጥ የነበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የበላይ





ክፍል ተማሪዎችና አስተማሪዎች የየቀኑ ቻፕል፣ በዓመት ከአንድም ሁለት ጊዜ የሚደረጉ መነቃቂያ ስብሰባዎች (Conference) ነፍስን የሚመግቡና ሕይወትን የሚያለመልሙ ቅመማ - ቅመማት ነበሩ። ዝማሬዎቹና የምንዘምራቸውም ከውጪ መጥተው የሚዘምሩልን እንደ ወንድም አዲሱ ወርቁ ያሉ ዘማሪዎችን ዜማ ተሰምቶ የሚጠገብ አልነበረም። ለሕይወቴ እርአያነት የሚጠቀሱ ብዙ ናቸው። ከዕለታት አንደ ቀን የቤተ ክርስቲያናችን አባል ወላጅ አባት ሞተው ከቀብሩ ማግሥት ይመስለኛል ልቅሶ ለመድረስ ወደ ናዝሬት ከተማ ሄዱኩና አቶ በየነ ሙላቱና አቶ ገመዳ ባሉበት ሄጄ አጠገባቸው ተቀመጥሁ።

ከእነርሱ ጋር እየተጨዋወትን ትንሽ እንደቆየን የውጭ አገር ዜጋ የሆኑ ሴቶች ልክ እንደ ሐበሻው ነጠላቸውን አዘቅዝቀው ለብሰው ቁርስ በያዙበት ዕቃ ላይ ጀበናቸውን አስቀምጠው ሰተት ብለው ወደ ጓዳ ሄደው ውስጥ ለነበሩት ሴቶች አስረከቡና ወደ ሣሎን ተመልሰው ሐዘንተኛዋ አጠገብ ሄደው አራቱም መሬት ተቀመጡ። ሐዘንተኛዋንም ማጫወት ጀመሩ። ይኸ ትዕይንት በጣም ነካኝ። የሁለቱ ባሎች አስቀድመው መጥተው ልቅሶ ቤት ከሚያውቁአቸው ሰዎች ጋራ ይጫወቱ ነበር። ሁለቱ ሴቶች ባለ ትዳር ሁለቱ ያለገቡ ነበሩ፤ የሁለቱ ባሎች ፖል ጊኝሪክና ፖል ዮዶር ይባላሉ።

ወደ ኋላ ልመለስና ኩየራ የጤና ረዳትነት ትምህርት በምማርበት ጊዜ የግቢውን ኃላፊ ፈልጌ ቤቱ ሄጄ በር ሳንኳኳ ባለቤቱ መጣች። ሚስተር አከሴን (ስሙን ጠርቼ) ፈልጌ ነበር ብዬ ጠየኳት፡ "ጌቶችን ፈልገህ ነው?" ስትለኝ አይ ሚስተር አከሌን ነበር አልኳት። አሁንም "ጌቶችን ፈልገህ ነው?" አለችኝ:: እኔ አስቀድሜ ያልሁትን ለ3ኛ ጊዜ ሚስተር አከሌን ስላት ከፍታ የያዘችውን ውስጠኛ በር ወርውራ ዘጋችብኝ። ንግግራችንን የምንለዋወጠዉ እኔ የውጪኛውን የሽቦ በር ከፍቼ እንደያዝኩ ነበርና እርሷ እንዳረገችው እኔም ወርውሬላት ተመለስኩ። (ኤስ አይ ኤም ከጣሊያን

ወረራ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ዳግም ሲገባ የመጡት አብዛኛዎቹ ሚስዮናውያን በአፍሪካናበሌሎች ቅኝ ተገዥ አገሮች የዚህ አይነት የጌትነት አባዜ ተጠናውቷቸዉ እንደነበር ወንድዬ አሊ በእኩለ ሌሊት ወገግታ በሚገባ ጠቁሞታል)።

ይህንን ዓይነት መደፋፈር ከየራ ተለማምጄ ነበር ናዝሬት የመጣሁት። ሁለቱም የኤስ አይ ኤም ሆነ የሜኖናይት ሚስዮናውያን ብጫጭ ያሉ ነጮች ነበሩ። አንዱ ሥራዬ ብሎ ባሕሉን ተቀብሎ ወንጌልን ሕያው በሆነ መልኩ ያቀርባል፣ ሌላው ጌትነቱን ሊያውጅ ወንጌልን በሁለተኛ ደረጃ ሊያቀርብ ይፈልጋል። እኔም ያኔ በመንፈሳዊ ሕይወቴ አድጌ ቢሆን ኖሮ ኪዘያን ጊዜ የተሻለ መልስ መስጠት እችል ነበር። ይኼ ተግዳሮት ሲያጋጥመኝ ገና 17 ዓመቴ ስለነበር አፍለኛነቴ ተጭኖኝ ኖሮ የሚገባቸውንና ለሌሎቹም የሚያካፍሉት የቃል ውጋት እንደ ሰሪንጅ ሳልተክልባቸዉ ቀረሁ።

ያለአግባቡ ሜኖናይቶችን ማወደስ ዓላማዬ አይደለም፤ የሆነውን በዝምታ ማለፍም ዋሾ ያደርጋል። እውነትን እውነት ብለን መናገር የክርስቲያንም ተግባር ነው። አንድ ጊዜ የኤስ. አይ. ኤም ሰዎች ሜኖናይቶችን አብረው የሚሠሩበትን አንዳንድ ነገር ለመነጋገር ጋብዙአቸው። እሺ ብለው ሜኖናይቶቹ አራት ኢትዮጵያውያንን ጨምረው መሪአቸውን አቶ ሸምሱዲን አብዶን ይዘው ሄዱ። የኤስ.አይ.ኤሞችን አቀባበል ሲገልጹልን ግን በጣም የሚያስቅ የሚያሳዝንም ሁኔታ ነበር። ሲቀበሉአቸው የኢትዮጵያውያንን እጅ ለመጨበጥም አልፈለጉም። ይብሱን ደግሞ ወደ ስብሰባው ክፍል ሲገቡ ኤስ. አይ. ኤሞች የተዘጋጀ መነጋገሪያ መርሃ ግብር አደሉ። ሸምሱዲን "ይህ ምንድነው" ብሎ ሲጠይቃቸው "የውይይት አጀንዳቸው ነው" ብለው መለሱ። ሸምሱዲን አሁንም "የጠራችሁን በጋራ ለመነጋገር ስለሆነ መርሃ ግብሩንም አብረን ነው ማውጣት ያለብን" ብሎ በእጁ የተሰጠውን ወረቀት ቀደደው። ኤስ. አይ.ኤሞች የገጠማቸው ከአቅማቸው በላይ ስለሆነባቸው በዚህ ተቆጥተው ስብሰባው አያስፈልግም ተብሎ ተለያዩ።





ከሜኖናይቶች አንዱ የሚያረካኝ ኢትዮጵያውያንን ለመሪነት ሆን ብለው ያዘጋጁ ነበር። መሪነቱንም ሰጥተው እዳር ቆመው ሲያበላሽ ለመሳቅና ለመሳለቅ ሳይሆን አብረው በመቆም እና አስፈላጊውን ምክርም ትምህርትም በመስጠት ይረዱ ነበር። በኛ ዘመን የነበሩ ሜኖናይት ሚሲዮናውያን ትኅትና ተላብሰው ቀላል ኑሮን የሚለማመዱና በመጠን መኖርን በሕይወታቸው የሚያስተምሩ ነበሩ እንጂ በስብከት የሚጨርሱ አልነበረም። ብዙ ኢትዮጵያውያንን ለተለያየ ትምህርት ስኮላርሽፕ እየፈለጉ ወደ ውጭ በተለይም ወደ አሜሪካ ልከዋል። ከተላኩት ተመልሰው በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የተሰማሩ ግን እጅግ በቁጥር አናሣ ነበሩ። ብዙዎቹ የውሃ ሽታ ሆነው ቀርተዋል።

ከነዚያ ሚሲዮናውያን የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ የደረሰባቸው ጥቂቶቹን ብቻ ለመጥቀስ ያህል ዳንኤል ሰነሰኒግ (Daniel Sensining)፣ ቸስተር ዌንገር (Chester Wenger)፣ ናታን ሔጊ ፖል ጊንግሪክ (Nathan Hege Paul Gingrich)፣ ፖል ዮደር (Paul Yoder)፣ ሮህረር ኤሼልማን (Rohrer Eshleman)፣ ኔቨን ሆርስት (Nevin Horst) እና ቨርነን ክራትዝ (Vernon Kratz) የሚባሉ ነበሩ። ከነዚህ ውስጥ Daniel Sensining እና Nevin Horst ወደ ጌታ ሄደዋል። የቀሩት ወደ አገራቸው ተመልሰው አሁንም በወር አንድ ምሽት እየተሰበሰቡ ለኢትዮጵያ ይጸልያሉ። እኔም MCC በቆየሁባቸዉ ዓመታት የጸሎቱ አባል ነበርኩ።

እነዚህ ሚሲዮናዊያን በሙያቸው አስተማሪዎች፣ ሐኪሞች ነርሶች እና አስተዳዳሪዎች ነበሩ ለአርአያነታቸው ተደጋግመው የሚጠቀሱት በዚህም ቢሆን በዚያ የዚህን ጽሑፍ አዘጋጅ ሕይወት በበጐ ስለነኩ ነው። ይሁን እንጂ ሁሉንም የመላእክት ከምችት ማስመሰል ተገቢ አይደለም። ሰዎች ናቸው፣ ስህተትም ሰርተዋል። ንስሐም ገብተዋል። ለምሳሌ ከነዚህ ከተጠቀሱት አንዱ እኔ በተገኘሁበት ቤተ ክርስቲያን ቆሞ በጥቂት ነገሮች ይቸገር እንደነበረ ተናግሯል። እነዚህም ዘረኝነት፣ የሴቶችን

መሪነት አለመቀበል፣ ግብረ ሰዶማዊነትና የመሳሰሉት ነበሩ።

ይህ ሰው የመጣው ከቨርጂንያ ክፍለ አገር ስለሆነ በዘረኝነት መቸገሩ አያስደንቅም። ከዚህ ሰው ሁለት ሴቶች ልጆች ጋር 10ኛ ክፍል አብረን ተምረናል። ቤተ ክርስቲያናችን ለኮሌጅ ትምህርት ወደ አሜሪካ ልካኝ በዚያው ኢስተርን ሜኖ ናይት (Eastern Mennonite College አሁን ዩኒቨርስቲ ሆኗል) ሲማሩ አገኘኋቸው። ትምህርት ቤትም ሲዘጋ መኖሪያችን አንድ አካባቢ ነበር። ትምህርት ቤታችን በበጋው ወራት ለእረፍት ሲዘጋ እኔም ለአንድ ድልድይ ለሚሠራ ኩባንያ ተቀጥሬ እሠራ ነበር። በአንድ የበጋ ወራት የኮሌጃችን ፕሬዚዳንት የነበሩት ዶ/ር ማይረን አግስ በርገር (Dr. Myron Augsburger የወንጌል ሥርጭት ስብሰባ እዚያው ላንድስ ቪል (Landisville) በሚባል ሠፈር ማታ ማታ የሚካሄድ ለአንድ ሳምንት አዘጋጅተው ነበር። ከእነዚያ ቀናት በአንዱ ምሽት ከሰውዬው ሁለት ሴቶች ታላቋን ደውዬ ወደ ስብሰባው የምትሄድ ከሆነ አብረን እንድንሄድ ጠየቅሁዋት፡፡ ተስማምታ በእኔው መኪና ከቤቷ ወስጂ ስብከቱን ተካፈልን፡፡ ሲያልቅ አንድ ቦታ አቁመን አይስክሬም ጋብዣት ወደ ቤቷ መለስኳት። ሳደርሳት አባትየው መኪናዬን አዙሬ ልሄድ ስል ከቤት ወጥቶ ድምጹን አሰማኝ። እኔ መኪናዬን እንዳቆምኩ በተከፈተው መስኮት በኩል መጣና "ሁለተኛ ይህንን ባትደግም እውዳለሁ" ሲለኝ እሺ ችግር የለም ብዬ መንገዴን ቀጠልሁ። እሱ ዘረኛ እኔም ብሔረተኛ፤ እርሱ ግን የራሱን እንጂ የኔን ብሔረተኝነት ኢየትዮጵያዊ ኩራቴን በፍጹም የሚያውቅ አልመሰለኝም።

## 13. በአባልነት ስለ መጠቃለሌ

እኔ ወደ ባይብል አካዳሚ በ1954 ዓ.ም ስመጣ የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ስያሜን መርጦ ለማጽደቅ ሞቅ ያለ ውይይት እየተካሄደ ነበረ። ከቃለ ሕይወት መሥራች አባቶች አንዱ በሆኑት በአባ ጎሴ ኑነሞ እጅ ብጠመቅም የመሠረተ





ክርስቶስ አባል እንድሆን ከማረኩኝ ነገሮች መካከል ገና አባል ሳልሆን በዚያ ውይይት ላይ እንድሳተፍ መጋበዜ አንዱ ነበር። በዚያን ወቅት ቤተክርስቲያኗ "መሠረተ ክርስቶስ" ተብላ እንድትሰየም ብዙዎች ቢስማሙም ለመመሥረቷ ምክንያት የሆነዉ የ"ሜኖናይት" ሚሽን የሚል እንዲካተት የሚወዱም ጥቂቶች አልነበሩም፡፡ ይልቁንም ክርክሩ "ሜኖናይት" የሚለው ስም ከ"መሠረተ ክርስቶስ" ፊት ወይስ ከኋላ? ወይስ ከመሐል? ይግባ የሚለዉ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ እያደር ሙሉ ኢትዮጵያዊነትን የሚገልጽ ስም ብቻ እንጂ "ሜኖናይት" የሚለው ጉራማይሌ ነገር አያስፈልግም የሚለው አስተያየት አየለ፡፡ በዚሁ ስምምነት ተደረሰ።

በክርክሩ ጊዜ ሚስዮናውያኑም ኢትዮጵያውያኑም እኩል ተሳትፈዋል። አመለካከቶቹ ሁለት ጎራ ፈጥረው እንኳን ቢሆን ፈረንጁ በአንድ በኩል አበሻው በሌላ በኩል ሆኖ አልነበረም፡፡ የአስተያየት እንጂ የዘር ክፍልፍል ያለመኖሩ ሳስብ እስካሁን ያስገርመኛል፡፡ መጨረሻ ላይም "ይሁን አይሁን" የሚለው ውሳኔ ከብዙ ጸሎት በኋላ በድምፅ ብልጫ ሳይሆን በስምምነት መጽናቱን አስታውሳለሁ።

ሌላው ወደ ሜኖናይቶች የተማረኩበት ቁም ነገር አገር በቀል የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለማፍራት የነበራቸዉ ቆራጥነት ነበር። ይህም የቀለም ትምህርት መስፋፋትንና ልቀትን ያጠቃልላል፡፡ ያገሬውን ተወላጅ ከአራተኛ ክፍል በላይ ማስተማር እንደማያስፈልግ የሚያምኑ የሚስዮን ድርጅቶች በነበሩበት በዚያ ወቅት በአገሪቱ አሉ ከሚባሉት የመንግሥትም ሆነ የግል ትምህርት ቤቶች ቢሻል እንጂ የማያንስ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከፍቶ ለአገሪቱም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በማፍራት ላይ ከነበረዉ ሜኖናይት ጋራ መሥራት ለእኔ ከብርም ብርቅም የሆነ ነበር። ወደ ሜኖ ናይት ከመግባቴ በፊት በሁለት ክርስቲያናዊ ሕብረቶች ስገለገል የታዘብኩትን ብጨምር መልካም መስሎ ታየኝ፡፡

አሰላ ራስ ዳርጌ ትምህርት ቤት እንደ ገባሁ በወላጆቼ ቤት ሳለሁ እንደለመድኩት በየሰንበቱ እግዚአብሔር ቤት መገኘት ነፍሴ ተጠማች፡፡ ሊያስተምረኝ የወሰደኝ ጋሽ ተሰማ ወደ እሁድ አምልኮ ባይሄድም እኔ እንድሄድ ፈቀደልኝ፡፡ ዘኬዎስ ኤደሞ የሚባል ሰዉ የስዊድሽ ሚሽን ከሆስፒታል አገልግሎት ጋር አገናኝቶ የከፈተዉን ቤተክርስቲያን አንድ ጊዜ አሳየኝ፡፡ ከዚያ በኋላ የሆነ ነገር አንቆ ካላስቀረኝ በቀር በየእሁዱ እሄድ ነበር። ይኽ ስዊዲሽ ሚሽን ጉለሌ (አርበኞች መንገድ) ካለው ቤተ ክርስቲያን ጋራ አንድ ዓይነት ነው። ከአምልኮ ስንወጣ ብስኩት ይሰጠን ነበር። ብስኩት ለመጀመሪያ ጊዜ የቀመስኩትም እዚያ ነበር፡፡

ሁለተኛውና በጣም ያስደነቀኝ ነገር ሕዝቡ በአዳራሹ ገብቶ የአምልኮ ስነሥርዓት እየተካሄደ ሳለ፡- አንድ ግዙፍ፣ መላጣ ፈረንጅ በሕዝቡ መኻል ተቀምጦ አንድ ወፈር ያለ፣ የካኪ መልክ ባለው ወረቀት የተጠቀለለ ነገር፣ በክብሪት እየለኮሰ፣ ወደ ውስጥ መጥጦ ጪሱን ቡልቅ እያደረገ በአፍንጫውና በአፉ ያወጣ ነበር።[24] ይህ ነገር ጥንባሆ (ሲጋራ) መሆኑን ስረዳ በጣም ገረመኝ፡፡ ክርስቲያን ጥንባሆ ማጨሱን፣ ያውም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ ያውም አንኳር የሆኑ ፕሮግራሞች ስብከትና መዝሙሮች እየተካሄዱ ይህ ይደረጋል ብዬ አልገመትኩም። በኋላ አገሩንና ምዕመኑን በሚገባ ተዋውቄ እንግድነቴ ከአለፈ በኋላ መምህር ዮናስ ዌረቼን ይህ እንዴት ይፈቀዳል ብዬ ጠየቅሁት፡፡ "ባህላቸዉ ቢሆን ነዋ" ሲል ባጭሩ ዘጋኝ።

ጋሼ ተሰማ ወደ ሻሸመኔ ሲቀየር የጸሎት ቤት የሚባል ነገር አልነበረም፤ ከነበረም አይታወቅም። ኤስ. አይ. ኤም ሻሸመኔ ከተማ ጸሎት ቤት እንዳለዉ ያወቅሁት ከጋሼ ተሰማ ቤት ከወጣሁ በኋላ ነበር። የሚሰዮናውያኑ አንድንድ አድራጎት ቢጎፈንነኝም እዚያም ቢሆን የነፍሴን ረሃብ ለማስተገስ ያህል የረባኝን መንፈሳዊ ማዕድ ተካፍያለሁ፡፡ አገልግሎት ምን እንደሆነ ማወቅ የጀመርሁት ኩየራ ለጤና ረዳትነት ከገባሁ በኋላ ነበር። ከዚያ በፊትማ ትግሉ ለመኖር ብቻ ነበር። በዚያ

[24] ቶስካና የሚሉት ሲጃራ መሆኑ ነው (ፊደል ካስትሮ የሚጠጡት አይነት)





ትምህርት ቤት ውስጥ መንፈሳዊው ትምህርት አብሮ ይሰጥ ስለነበረ እንደ አቶ ያዕቆብ ባፋና፣ አቶ ኬዳሞ ሜቻቶ የመሳሰሉ ወንጌላዊያን ስለነበሩ ድባቡ አመቺ ነበር። የመጀመሪያ መልእክቴን በረቡዕ ምሽት የጸሎት ፕሮግራም ላይ በሰው ፊት ቆሜ ያቀረብሁት እዚሁ ኩየራ ነበር። የመልእክቴም ክፍል ፲ኛ ቆሮ 15፥12-19 ሆኖ ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ መነሳት የተናገረውን በመመርኮዝ በእርሱ ስለሚገኝ ዘላለማዊ ሕይወትና ከሞት በኋላም ስላለዉ ሕይወት ሰበክሁ፡፡ ለ17 ዓመት ወጣት በሰው ፊት ቆሞ መናገር የሚያስፈራ ቢሆንም ለአገልግሎቴ ፈር ቀዳጅ መልእክቴን ማቅረብ በመቻሌ ግን ደስ ብሎኛል።

በዚያን ዘመን የአመለካከት አድማሴን ካሰፉልኝ ዕድሎች አንዱ ኤስ.አይ.ኤም በኩየራ ማእከሉ በየአመቱ በጠቅላላ አገሪቱ ላሰማራቸዉ አስተማሪዎች የሚሰጠዉ የክረምት ኮርስ ነበር፡፡ አስተማሪዎቹ ተማሪዎች ሆነው ሲመጡ ሌሎች ደግሞ የነርሱ አስተማሪዎች ሆነው ይመጡ ነበር። እነዚያ የመምህራኑ አስተማሪዎች የሚመጡት ደግሞ ከዩኒቨርስቲ ስለነበረ እነርሱን ማየትና መተዋወቅ ውስጤን ይቀሰቅሰው ነበር። ሁሉን አልፈው እዚህ ደረጃ ላይ የደረሱት ምሁራን አስተማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ሰባኪዎችም ነበሩ። የማስታውሳቸውን ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል አቶ በየነ ጭጭ አይበሉ (በኋላ ዶክተር) አቶ ኃይሌ ወ/ሚካኤል (በኋላ ዶክተር ) አቶ ሚሊዮን በለጠ፣ አቶ ሰይፉ አብዬ . . . ናቸዉ፡፡ እነዚህና ሌሎችም ለሕይወቴ መልካም አርአያዎች ነበሩ፤ ናቸውም። ከዘመን በኋላ ብዙዎቹ በቀደመዉ እምነታው ጸንተዉ እግዚአብሔርን አገልግለዉ ያለፉ ወይንም እያገለገሉ ቢሆንም ጥቂቶች ግን ከጌታ ቤት ተለይተው ሲኖሩ ማየት ልቤን በእጅጉ ያሳዝነዋል፡፡

## 14. ከካሽርነት ወደ ባሕር ዳር ፖሊቴክኒክ ተቋም

የ12ኛን ክፍል በተመላላሽ እየተከታተልኩና በግሌም እያጠናሁ የቤተሰብ ጉዳይ ያመጣውን ጫና ለመወጣት ስል ሥራ ለመያዝ ተገደድሁ። ሥራውም በባይብል

አካዳሚ ገንዘብ ተቀባይነት ነበር፡፡ ለቤተሰቤ ታላቅ እንደመሆኔና የኔም ክፍል ትምህርት ደረጃ ከታናናሾቼ ይበልጥ ስለነበረና ለሥራውም የኔ ዕድሜ የተሻለ ስለነበረ እንደገመድ ጉተታ የገመዱን ጫፍ ይዤ የሌሎቹ (የተናናሾቼን) ጥረት ውጤታማ ለማድረግ መጣር ነበረብኝ። ስለሆነም ከላይ በጠቀስሁት መሠረት የማትሪክን ፈተና በግሌ ለመውሰድ የተቻለኝን ያህል ጥናቱንም ሥራውንም እያደረግሁ ሁለት ስልቻ የተጫነች እንስሳ ጭነቱ መሀል ጀርባዋ ላይ ካልተቀመጠና ካጋደለ ጫኙ እንደገና አስቁሞ አስተካክሎ እስሩን ወጥሮ እንደሚያስተካክል የኔም እረኛ ጭነቴን ማስተካከል ብቻ ሳይሆን ሸክሙንም እየተጋራኝና የከበደውን አንዳንዱም በሙሉ እየተሸከመልኝ ማትሪኩም ታለፈ ሥራውም ተሠራ ታናናሾቼም የትምህርት ዘመናቸው ሳይቋረጥ ጧት ያስጀመረኝ የጉዞዬ ባልደረባ ሳይሰለቸኝ እንደዚህ መራኝ። በማቴ 11÷28-30 ባለው ክፍል እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ . . . ብሎ ጥሪውን ያስተላለፈው የጉዞዬ ባልደረባ ታማኝነቱን የተቀበልሁት እኔ በጧቱ ስለሆነ ቀንበሩም ቢሆን ትከሻ የማይልጥ (የማያቆስል) እንደሆነ ተረድቼአለሁ። በአብዛኛው ጊዜ ሸክም የሆነብኝን ነገር ከመሆኑ እንኳን አስቀድሜ በራሴ መንገድና ቋንቋ ሳወያየው ሳያንገጫግጨኝ ወይም ሳይጎረብጠኝ በፊት ሸህሙን ቀርቶ ቦታውን ያጣሁባቸውን ጊዜያት መቁጠሩ ያዳግተኛል።

ከእስከ የሌለው "ወደ እኔ ጩህ እኔም እመልስልሃለሁ፤ አንተም የማታውቀውን ታላቅና ኃይለኛ ነገርን አሳይሃለሁ" የሚለውን (ኤር.33÷3) የሰጠኝ በናዝሬት ባይብል (መጽሐፍ ቅዱስ) አካዳሚ አስተማሪዬ የነበረ ጋሼ ዳንኤል ለማ (አሁን ዶክተር) ነበር። በወቅቱ ይህንን ጥቅስ እንዲሰጠኝ ያደረገው ሁኔታ በውል ባይታወሰኝም ምርኩዜ ሆኖ በዘመኔ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ታላቅ ጉልበቴ ወይም አቅም ማካበቻዬ ነበር። የካሽርነቱ ሥራ ገንዘብ ቆጥሮ መቀበል፣ ደረሰኝ ለከፋዩ መቁረጥና በቀኑም መጨረሻ ቆጥሮ ማስረከብ ነው። ቆጥሬ ስቀበል ካልተሳሳትኩ በቀር ብዙ የሂሣብ





ጉድለት አይገኝብኝም ነበር።

በናዝሬት ቆይታዬ አየሩም ሕዝቡም ተስማምተውኝ ሳለ ነው አንድ ቀን አቶ ሚሊዮን በለጠ ወደምሰራበት ግርግም የመጣው። ግርግም ያልሁት በቤቱ አዳራሽ መካከል በጡብ የተሰራ አንድ በር ያለው ጉርድ ክፍል ነው። ለረዥሙ ሰው ከወገብ ለአጭሩ ደግሞ ከደረት በታች የሆነዉ ይህ ግርግም መስኮት አልባ ነው። ዙሪያውን ክፍት ስለሆነ የአየር እጥረት አያስቸግርም ። መጪውንም አላፊውንም ስለምናይ ማን መጣ የማይባልበት ሁኔታ ነበርና ጋሼ ሚሊዮንም ሲመጣ እኔ ዘንድ ሳይደርስ ከግርግሜ ወጣ ብዬ ሰላምታ ተለዋወጥን።

በሰላምታ ጊዜ ሳያጠፋ ይዞት ወደመጣው ርእስ አለፈ፤ በዚህን ጊዜ በሌላ ግርግም ውስጥ ካርድ ክፍል ይሰራ የነበረ ወንድም ካሳ አጋፋሪም መጥቶ ሰላም ከተባባሉ በኋላ ነው ጋሼ ሚሊዮን የርእሱን ፈንጂ የአፈነዳብን። ወደ ባሕር ዳር እንድትመጡና እንድትማሩ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ ዓይነት ነገር ሲል ሁለታችንም ጭው አለብን፡፡ እኔ በተለይ ከላይ እንደጠቀስሁት አየሩንም ሕዝቡንም በፍቅር እያጣጣምኩ ስለነበረ ግር ነበር ያለብኝ። ሁለታችንም ተያየንና እናስብበትና እንነግርሃለን ስንለው ብዙ ጊዜ እንደሌለና ባጭር ቀን ውስጥ በሚሰጠው መግቢያ ፈተና መሳተፍ እንዳለብን አውጀብን ወደ ሌላ ዞር አለ። ሁለታችንም ወደ ግርግማችን ተመለስን፡፡ የተባለውንም ፈተና ወሰደን ለተንኮሉ ሁለታችንም **"አልፋችኋል"** ተባልንና ሥራችንን በአጭር ጊዜ አስረክበን ከግርግሞቻችን ወጣን፡፡ ጉዞ ወደ ባሕር ዳር ሆነ። በነገራችን ላይ ካሳ በዚህን ጊዜ ከአስር ዓመት በላይ ናዝሬት ስለኖረ ከእኔ በላይ ታዋቂና ተወዳጅ ነበር።

ዘመኑ 1957 ዓ.ም ነሐሴ ወር ሥራችንን ለቀቅን፤ ሻንጣው ተሸከፈ፤ ስንብቱ ተጠናቀቀ፡፡ ለባሕር ዳሩ ጉዞ በበነጋው ትልቁን የክፍለ አገር አውቶቢስ ለመያዝ በትንሽ አውቶቢስ ከናዝሬት አዲስ አበባ መጥቶ ማደር ግድ ሆነ። በማግስቱ ጧት

12፡00 ሰዓት ትልቁ አውቶቢስ ስለሚለቅ ተዘጋጅቶ ማደር ነበር። እንደማስታውሰው ጓደኛዬ ሙሉነህ ባቾሬ ያኔ ከወ/ሮ ፅዳለ በየነ ጋር ትዳር መስርቶ ስለነበረ እርሱ ዘንድ አደርኩና በማግስቱ በጧት ወደ አውቶቢሱ መናኸሪያ ሸኘኝ። በሆነ ምክንያት ካሳ ቀድሞኝ ነበር የሄደው።

በያኔው ጉዞ አውቶቢሱ ከአዲስ አበባ ተነስቶ ደብረማርቆስ አድሮ በሁለተኛው ቀን ወደ 9 እና 10 ሰዓት ገደማ ባሕር ዳር ደረስን። ይህ ሁሉ ጥረት ከመስከረም 18/1958ዓ.ም. አስቀድሞ ለመድረስ ነው። መስከረም 18 ቀን በመላው ኢትዮጵያ ለክረምቱ የተዘጋው ትምህርት ቤት የሚከፈትበት ስለሆነ የብዙ ሕዝብ መጓጓዣ ጊዜ ነበር። ይሁን እንጂ ከኔ ጋር ወደ አንድ አቅጣጫ የሚጓዙ ብዙ ተማሪዎች አላጋጠሙኝም። ባሕር ዳር ደረስንና ከአውቶቢሱ ወራጅ መንገደኛና ተቀባይ እንዲሁም "እኔ ልሸከም እኔ ላድርስ" የሚል ሕዝብ ግርግር እንደማንኛውም መናኸሪያ ግራ የሚያጋባ ነበር።

ሻንጣዬን ከተረከብኩ በኋላ የምሄደው ወዴት የሚወስደኝ ማን ይሆን? እያልኩ በማላውቀው ሕዝብና ከተማ መንጠራወዝና ማማተር ጀመርኩ። አንድ መለስተኛ ቀይ የጭነት መኪና የያዙ ሰው እንደኔው ሰው ሊቀበሉ እንደመጡና በዓይናቸው እሳቸውም ሲያማትሩ ዓይን ለዓይን ተገጣጠምንና "ፖሊ"፣ ስላቸው አዎን አሉኝ። አቶ ተናኘ ይባሉ ነበር። ሻንጣዬን ከኋላ አስገባሁና እኔ ገቢና ከጎናቸው ተቀምጬ ወደ ከተማ ሳይሆን በኮረኮንች መንገድ ወደ ገጠር የሚሄድ ሲመስለኝ ፖሊ ጫካ ውስጥ ነው እንዴ ያለው? ስላቸው ሳቅ አሉና "ወደ ጊዜያዊ ማደሪያችሁ ነው የምወስድህ" አሉኝና ወደ አዲስ የተሰራ ትምህርት ቤት እንደሆነ አስረዱኝ።

## በየት ልውጣ!?

ምዝገባ ተፈጸመ ትምህርት ተጀመረ። የብርድ ልብሶች፣ የከሰል ካውያ ንብረትም





ሃላፊነት ተሰጠኝ። የሆነ ሁሉ እየሆነ ግን ባሕር ዳርን ወደ ውስጤ የሚያስገባ ናዝሬትን ደግሞ ከውስጤ የሚወስድ ነገርም ሆነ ሰው ጠፋ። የትምህርቱም ነገር ኑሮውም ጨርሶ አልታረቅህ አልጥምህ አለኝ። ያመጣኝ ጋሼ ሚሊዮንን የፖሊ ምክትል ዳይሬክተር ስለ ነበር ምኑም እንዳልጣመኝ አስረድቼ እንዲያሰናብተኝ ሞከርኩ፤ አልሆነልኝም፡፡ ጭራሽ አቶ ይፍሩን እንድጠይቅ መራኝ፡፡ አቶ ይፍሩ ገበየሁ የፖሊ ዋና ዳይሬክተር ነበሩ፡፡ ጉዳዬን በዝርዝር ለአቶ ሚሊዮን እንዳስረዳሁ በማስመዝገብ ልቀቁኝ ብል " በቂ ምክንያት አይደለምና አይቻልም" አሉኝ። በገዛ ፈቃዴ እጄን ስጥቼ ልቀቁኝ እያልኩ መለመን ሞኝነት ሆነብኝ።

## ዋሽሁ!

አድርጌው አላውቅም ሲደረግ ሳይም አድራጊውን ክፉኛ እታዘባለሁ። ጓደኛ አማከርኩና የሚያዋጣህ አለኝ። አሁን አዲስ አበባ ለሚኖረው ጓደኛዬ በቂ ምክንያት ፈጥረህ ከዚህ እንድወጣ አርገኝ ብዬ ጻፍኩለት፡፡ ልክ በሳምንቱ የኤሮግራም ደብዳቤ በት/ቤቱ አድራሻ በኩል ደረሰኝ። የላኪውን አድራሻ ሳይ ገና ሳቅም ጭንቀትም አለኝ፡፡ ደብዳቤው ተከፍቶ ተነበበ እንደገናም አሳቀኝ የደብዳቤው ይዘት ያለው "እናትህ በጠና ታመው ጥሩልኝ ብለዋልና ውለህ ሳታድር እንድትመጣ" ነው። የውሸቱ ፈጠራ ሊያስቀኝ ሲሞከር ይህን ውሸት እውነት አስመስሎ ጋሼ ሚሊዮንን ማሳመኑ ጭንቀት ለቀቀብኝ። የወሰንሁት ጉዳይ ስለሆነ አሁን በነገሩ እንዳዘነ ሰው ፊቴን አስተካክዬ ወደ አቶ ሚሊዮን ቢሮ ደብዳቤውን ይዤ አቀናሁ። በሩን አንኳኩቼ ስከፍት ብቻውን ነበረና ምን ነበር ሲለኝ ፊቱ በነበረው ጠረጴዛ ላይ ደብዳቤውን አስቀመጥሁለትና አንብበው አልሁ። ብድግ አድርጎ አነበበ ራሱን ነቅንቆ "ታዲያ ምንድን ነው የምትለው?" አለኝ፡፡ የውሸቱ ሐዘን ድምጼን ሁሉ ከወትሮ አደልቦት መሄድ አለብኝ አልሁት። "መቼ ትመለሳለህ?" ሲለኝ ምን አውቃለሁ እዚያ ደርሼ ሁኔታውን ሳይ ነው የማውቀው አልሁትና ራሱን እንደገና በመነቅነቅ

ቶሎ እንድትመለስ ብሎ ደብዳቤውን ወደእኔ ገፋው። ከፍ ብዬ እንደጠቀስኩት የብርድ ልብሶች፣ የከሰልና የካውያ ሹም ነበርኩ፡፡ ኃላፊነቴን ገበየሁ ለሚባል ጠና ላለ ተማሪ አስረክቤ ባሕር ዳርን ለቀቅሁ፡፡ በዚህ ጊዜ መስከረምና ጥቅምት አልፎ ህዳርም ተጋምሶ ነበር።

ስንጓዝ ውለን ለአዳር ደብረማርቆስ ደረስን መኝታ ተፈልጎ ተያዘ እራትም ተፈልጎ ተበላና ታደረ። ቀሪው ግማሽ ጉዞ በነጋታው ማለዳ ተጀመረና አዲስ አበባ ወደ አስር ሰዓት አካባቢ ደረስን። ከመርካቶው ግርግር ታክሲ ይዤ ጓደኛዬ ሙሉነህ ወደሚሰራበት ወደ ሜና የመጽሐፍት መደብር ፈጠንኩ፡፡ ደርሼ ስንተያይ ሁለታችንም ከት ብለን ሳቅን፡፡ አዳሬ እርሱ ጋ እንደሚሆን የተረጋገጠ በመሆኑ የቀረውን ጨዋታ ለኋላ ትተን ሥራውን ቀጠለ። አዲስ አበባ ሁለት ቀን ብቻ አድሬ ወደ እናቴ የ360 ኪ.ሜ ጉዞ ጀመርኩ፡፡ ሁለት ሳምንት ሁለቱ ወላጆቼና በሌሎቹም ዘመዶቼ ዘንድ እንደ እረፍትም ሆኖልኝ ቆየሁ። (አሁን ዱራሜ የከምባታና ጠንባሮ ዞን ከተማ ስትሆን ምሽግዳ ደግሞ የአባቴ መኖሪያ እኔም የተወለድሁበት ቀበሌ ቃጨ-ቢራ ደግሞ ወላጆቼ ተለያይተው የእናቴ መኖሪያ ሆኖ ነበር።)

በእንዲህ ሁኔታ እንዳለሁ ከባሕር  ዳር ከለቀቅሁ በኋላ ኃይለማርያም ማሞ መታሰቢያ ይባል በነበረው አሁን የአዳማ ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተር የነበሩት ዶ/ር ሮሀረር ኤሼልማን ከባሕር  ዳር መመለሴን ሰምተው ኖሮ “ወደ ባሕር  ዳር የማትመለስ ከሆነ የሥራ ቦታ ስላለን መምጣት ትችላለህ ወይ?” በማለት ትንሽ በእጅ የተጻፈች ማስታወሻ ላኩልኝ፡፡ “ውሾ አር ረገጥክ ቢሉት የምፈልገው እሱን አይደለም ወይ?” አለ እንዲሉ ማስታወሻዋ ቅዳሜ ደርሳኝ እኔ ሰኞውን ናዝሬት ደረስኩ። እንኳን እኛንና ያለንበትን ቦታም ሆነ ሁኔታ ከማንም በበለጠና በተሻለ የሚያውቅ አምላክ ጥያቄያችንን ሳንጠይቅ አስቀድሞ ያውቃል ይመልሳልም።

ስለዚህ ከባሕር  ዳር ተመልሼ በናዝሬት የጤና ረዳቶች ትምህርት ቤት





ዳይሬክተርና የሆስፒታሉ ረዳት አስተዳዳሪ ሆኜ ተሾምኩ። በተመሳሳይ ጊዜ ነበር አቶ ፍስሐ ወንድም አገኘሁ ዋና አስተዳዳሪ ሆኖ የተሾመዉ፡፡ አዲሱ ሥራ ተጀመረ፤ ፕሮግራሞች ወጡ፣ አስተማሪዎች ተደለደሉ፤ ተማሪዎችም ገብተዋል። ተደላድዬ አዲሱን ሥራዬን በምወደው አካባቢ (environment) ቀጠልሁ፡፡ ያ ወደ ፖሊ ቴክኒክ ትምህርት ቤት እንድሄድ የመለመለኝ ጋሼ ሚሊዮን በዚሁ ዓመት መስከረም ወር የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ መማክርት ጉባዔ ሰብሳቢ ሆኖ ተመርጦ ስለነበረ “ጥር 12 እና 13 ለሚደረገው ስብሰባ ወደ ናዝሬት እንደሚመጣ ነገረኝ፡፡ የውሸቱን ደብዳቤ በመጠቀም ከተለያየን ወዲህ ሁለት ወር ያህል አልፎን ነበር።

**ተናዘዝኩ**

ከላይ ለተጠቀሰው ስብሰባ መጥቶ ጋሼ ሚሊዮን ወደ ሆስፒታላችን ግቢ መጣ። የአታላይ ዓይን አውጣ ከሩቅ እየሁትና እየተጣራሁ ወደ እርሱ ስሮጥ ቆሞ እየኝና እስከደርስ እጁን በአፉ ላይ አድርጎ በመገረም ጠበቀኝ። ናዝሬት መመለሴንም ሥራ መያዜንም አያውቅም ነበር መሰለኝ “አስዋሻችሁኝ” እናቴም አልታመመችም አልለቅ ስትሉኝ የተፈጠረ ዘዴ እንጂ ሌላ የለም ስለው አሁንም አትመለስም ማለት ነው አለኝና ሳቁን ጨመረው ባስብ ኖሮ “የሞተም ዘመድ የለህ” አለው ነበር ይሁን እንጂ ሁለታችንም ይህንን ነገር እያነሳን “አታለልከኝ” “ሰራሁልህ” እየተባባልን በተለያዩ ጊዜያት ስቀናል።

## 15.ለኮሌጅ ትምህርት መመረጥ

ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መጨረሻ ጀምሮ በ1956 ዓ.ም በኃይለማርያም ማሞ መታሰቢያ ሆስፒታል በጤና ረዳትነት፣ የትምህርት ቤት ዳይሬክተርና የሆስፒታሉ ምክትል አስተዳዳሪ በመሆን እየሠራሁ ቆየሁ። እንጀራዬን በዚህ እየበላሁ ቤተ

ክርስቲያኒቱን በሽምግልና በሰብከት በአስተርጓሚነት (ለፈረንጆቹ) እና በተቻለው ሁሉ አገልግሎት እሰጥ ነበር። በናዝሬት መሠረተ ክርስቶስ አጥቢያ በሽምግልና አብረን እናገለግል የነበርን አቶ በየነ ሙላቱ፣ አቶ ገመዳ ባሩዳ፣ አቶ ገ/ሥላሴ ሐብታሙ ለተወሰነ ጊዜ አቶ ፍሰሐ ወ/አገኘሁ እንደነበርን አስታውሳለሁ። ከነዚህ ከታላላቆቼ ጋራ አብሮ መሥራትና ከእነርሱ መማሩ ራሱ ትልቅ ዕድል ነበረ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ወደ ወንጂና ሸዋ ተመላልሶ በምክርም በወንጌል ስብከት ባይብል አካዳሚ ሳለሁ የተጀመረው አገልግሎት እንደቀጠለ ነበር። በ1959 ዓ.ም አጋማሽ አካባቢ የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ (ሥአኮ) ለትምህርት ወደ አሜሪካ እንድሄድ መረጠኝና አስተያየቱን ለጠቅላላ ሽማግሌዎች ጉባዔ (ጠሽጉ) አቀረበ:: ጉባዔው ከአጸደቀዉ በኋላ ነበር ለኔ የተነገረኝ:: እኔም ፈቃደኝነቴን ገልጬ የቤተ ክርሰቲያኑ አመራር ለትምህርት ቤቱና ለሚሽኑ ደብዳቤ ጽፎላቸው ሁለቱም ፈቃደኞች ሆኑ:: ትምህርት ቤቱ ከአሜሪካ ተዘጋጅቶ የሚመጣ የእንግሊዝኛ ፈተና (Tofel) ውጤት እንደሚያስፈልግ ጻፈ:: የቶፌሉን ፈተና ተፈትኜ ውጤቱ በቂ ስለነበረ መቀበላቸውን አረጋገጡልን። የትምህርቱን ክፍያ በተመለከተ በሦስት ተከፍሎ ት/ቤቱ 1/3ኛውን፣ ሚሺኑ 1/3ኛውን እኔ ደግሞ 1/3ኛውን እንድሸፍን ነበረ የተደረገው። ከየት አምጥቼ እከፍላለሁ ብዬ ስጠይቅ "ሥራ ትሠራለህ" ተባልሁ።

በዚያን ጊዜ ወንድሜ ወልዴ ቤናራ 8ኛ ክፍል ጨርሶ ወደ ናዝሬት መጥቶ አፄ ገላውዲዮስ ትምህርት ቤት ይማር ነበር:: ብቸኛ ደጋፊዉ እኔ ስለሆንኩ ትቼዉ መሄድ አይቻለኝም:: እንዴት እንደማደርገዉ ሚሰዮኑን ሳማክር ባይብል አካዳሚ መግባት የሚያስችለዉ ስኮላርሺፕ እንደሚያፈላልግለት በገባልኝ ቃል መሠረት እንዲዚያው ተጠቃለለ። ስለዚህ በ1959 ዓ.ም መስከረም ወር እኔ ወደ አሜሪካ ወልዴም ወደ ባይብል አካዳሚ እኩል ገባን። እርሱ 11ኛ ክፍል ገባ::





## 16.የ"እንዲት ልጅ" ነገር

በኃይለማርያም ማሞ መታሰቢያ ሆስፒታል ስሠራ በየማለዳው እንደምናደርገው የሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ዶ/ር ሮሕረር ኤሽልማን፣ ዋናው አስተዳዳሪ አቶ ፍሰሐ ወንድም አገኘሁና እኔ የጤና ረዳቶች ትምህርት ቤት ዳይሬክተርና የሆስፒታሉ ምክትል አስተዳዳሪ እየተገናኘተን መረጃ እንለዋወጣለን:: በሆስፒታሉ ሌሊቱን ምን አዲስ ነገር እንደተከሰተ፣ በሠራተኛውም ዘንድ ሆነ በሌሎች አካላት መታወቅ ያለባቸውን ጉዳዮችና የመሳሰሉት የየዕለቱ አጀንዳዎቻችን ነበሩ::

አንድ ማለዳ ከዚያ ስብሰባ ወጥቼ ፈንጠር ብሎ ወዳለው ቢሮዬ እያመራሁ ነበር:: በስተቀኝ በኩል ከነበረው የሴቶች ማደሪያ በረንዳ ላይ ከአንዱ ክፍል ወደ ሌላዉ ለመግባት ስትራመድ ከነበረቺቱ እንዲት ተማሪ ጋር በሩቁ ሰላምታ ተለዋውጠን ቢሮዬ ገባሁ። የምሠራውን እየሠራሁ እንዳለሁ ትንሽ ቆይታ ቢሮዬ ብቅ አለች። ከጠረጴዛዬ ፊት ከነበሩት ሁለት ወንበሮች በአንዱ እንድትቀመጥ ጋብዤአት ቁጭ አለች። ወደ ቢሮዬ የመጣችበትን ጉዳይ አሁን ባላስታውስም የነበራትን ጥያቄ መልሼላት ከተነጋገርን በኋላ ከጧቱ የሻይ ዕረፍት በፊት ለመሄድ ተነሳች።

በሩን ከፍቼ ላስወጣት ከወንበሬ ተነሥቼ ጠረጴዛዬን ዞሬ እጇን ስጨብጥ ኃይለኛ ሙቀት ተሰማኝ። እንደዚሁ እንደቆምን ጥቂት ስናወራን በመካከላችን የነበረው ርቀት እየጠበበ ሄደና ከንፈር ለከንፈር ተላተምን። የእርሷን አላውቅም እኔ ግን ለተወሰነ ጊዜ "ምንድነው ያደረግሁ" የሚል ጥያቄ አእምሮዬን ሞላው። ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ስላላየኝ በዚህ ተንፈስ ብዬ ቀናት አለፉና በውስጤ "ማን ያውቃል ዘላቂስ ነገር ከሆነ?" የሚል አሳብ ሽው ይልብኝ ጀመር።

ሁለታችንም ተፋፈርን መሰለኝ ዓይን ለዓይን መተያየቱም ዳገት ሆኖብን ከረመ። አንድ ቀን በሻይ ጊዜ ኩባያችንን እንደያዝን ከሰዎች እይታ ባልራቀ ዛፍ ጥላ

ሥር ቆሜ ጠራኋት፤ እንደመጣች ሰሞኑን ስለሆነው መላተም ምን እንዳሰበች ጠየቅኋት፡፡ "እኔ ምን አውቃለሁ" ስትለኝ እንግዲያውስ በነገሩ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንድንጠይቅ ተስማማን። ጉዳያችንን ለሰው ሳይሆን ለእርሱ ለአንድዬ በመንገሩ ተስማማን። ሁለታችንም ዋለልን። ያለምንም አሳብ ና ዕቅድ የሆነ ነገር ከዚያ በፊት ሆኖ የማያውቅ አሁን ለምን? እንዴት? የሚሉ ጥያቄዎች ተመላለሱብኝ፤ ግን ጌታ ሆይ አንተ ታውቃለህ። አንተን አሳዝኜ ከሆነ ማረኝ ከውስጤም ደምስሰው፣ ይህንን አድርጌ መሸሽ አልፈልግም። በጎው ካንተ ይምጣ ብዬ ጸለይሁ፡፡ ከዛፍ ስር ንግግራችን በኋላ ሁለታችንም ወደ ኖርማል ግንኙነት ተመለስን።

ትንሽ እንደ ቆየን የሜኖናይት ሚሽን ረዳት ዳይሬክተር አድርጎኝ ወደ አዲስ አበባ ተዛወርኩ። ልጅቱ የመጣችው ከጎንደር ሲሆን ፈረንሣይ ለጋሲዮን አካባቢ ዘመዶች አሏት፡፡ እነሱን ጥየቃ በመጣችበት አጋጣሚ ከመኪና ተራ ተቀብዬ ሸኘኋት፡፡ ድንገት በአእምሯችን ሽው ቢል እንኳን የትዳር ጓደኝነት እንደሆነ እንጂ በሁለታችንም በኩል ሌላ አሳብ እንዳልነበረ በግሌ አምናለሁ። በዚህም መካከል ነበረ የአሜሪካው የትምህርት ዕድል የመጣው።

ቢሆንም በሁለታችንም ውስጥ ይኸ አሳብ እያደገ መሆኑ ይሰማኛል፡፡ ወደ አሜሪካ መሄጃዬ እየቀረበ ሄደ። አንድ ቀን ስልክ ደወለችና ልትመጣ እንደሆነ ነገረችኝ፤ ያልታሰበ ዕቅድ ቢሆንም እሺ አልኩ። ለገሃር ወደነበረው የናዝሬት መኪና ተራ ሄጄ ተቀበልኋት። ፈረንሣይ ለጋሲዮን ወዳሉት ዘመዶቿ ልትሄድ መስሎኝ ሳነሳባት እዚያ እንደማትሄድ ነገረችኝ፡፡ ታዲያ የት ታድሪያለሽ ብዬ ስጠይቅ ፍርጥ አድርጋ "ካንተ ጋራ ነዋ!" ስትለኝ ደነገጥሁ፣ ግራገባኝም፡፡ ያለችኝ አንድ ክፍል ቤት ነች፡፡ እስካሁን እንግዳ አስተናግጀባት አላውቅም፡፡ አልጋዬም ሁለት ሰው አታስተኛም፤ ሰዉ የሚያስተኛ ሶፋም ሆነ አግዳሚ ወንበር የለኝም። ይህንኑ ሁሉ ነግሬአት ጓደኛዬ ሙሉነህ ቤት ልወስዳት አሳብ ሳቀርብ "አልሄድም" አለችኝ።





የመጣችው ሌጣዋን ነው። ከእጅ ቦርሣዋ በቀር ሌላ ነገር አልያዘችም። እየመሸ ሲመጣ ለማንኛውም እራት እንብላ ብዬ አራት ኪሎ ቱሪስት ሆቴል አጠገብ በላን፡፡ ቤቴም ኪዘያ አይርቅም ነበር። ወስና የመጣችው ጉዳይ ስለሆነ እኔ ያቀረብሁት አሳብ ሁሉ ውድቅ ሆኗል። ፒጃማ ይዘሻል ወይ ስላትም እንዳልያዘች ተረዳሁ። ሆቴል ልውሰድሽ ብዬም አልሆነም። ይህ እንቆቅልሽ እንዴት ነው የሚፈታው ብዬ ሳወጣ ሳወርድ ቆይቼ፡-

"እሺ አሁን ወዴት እንሂድ?" አልኳት እራት ከበላንበት ሆቴል ስንወጣ፡፡

"የቤትህ ቁልፍ ጠፍቶብሃል እንዴ!?"

"አይ እሱስ አልጠፋብኝም! . . . እንዲያዉ መላው ነው እንጂ የጠፋኝ" ብያአት እሪ በከንቱ አካባቢ ወደ ነበረች ወደ አንዷ ክፍል ቤቴ አመራን። ሰዓቱ ወደ አራት ሰዓት ተጠግቷል። ሁለት ወንበር ነበረና ገብተን ተቀመጥን። ትንሽ እንደ አወራን፡-

"በይ አንቺ አልጋው ላይ ተኚ፤ እኔ ሁለቱን ወንበር ገጥሜ እጋደማለሁ" አልኳት፡፡

"በምንም ዓይነት"

"ታዲያሳ . . . ?"

"ይበቃናል፤ አብረን እዚህ ነው የምንተኛው"

"እሺ የኔን ፒጃማ ልበሺ" ብዬ የታጠበ ፒጃማ አውጥቼ ሰጣኋት፡፡

"አልለብስም እንዲሁ ነው የምተኛው" ስትለኝ በውስጤ ጌታ ሆይ ይህንን እንቆቅልሽ አንተ ብቻ ነህ ልትፈታ የምትችል ብዬ የራሴን ፒጃማ ለበስሁና ተኛን። እስከሚነጋ ድረስ ሳልገላበጥ፣ ሳትገላበጥም ወዲያን ወዲህ ዞረን እንደተኛን ሌሊቱ ነጋ።

ጠዋት ውሃ አቅርቤላት ፊቷን ተጣጥባ ሻይ ቤት ሄደን ቁርስ በላን፡፡ እኔ ወደ ሥራዬ ቢሮአችን ሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ አጠገብ ባለው መስቀለኛ መንገድ ላይ ያለ

(የልዑል ራስ አሥራት ካሣ ሕንፃ) ውስጥ ነበርና ወደዚያ አመራሁ። እሷን በታክሲ
ወደ ናዝሬት መኪና ተራ ሸኘኋት። ቁርስ ስንበላ፡-

"አዳነች ያለችኝ እውነት ሆነ" አለችኝ አግራሞትና ድንጋጤ በተቀላቀለበት
ስሜት "ደግሞ ምን ብላሽ ነበር?"

"ተሰፋጽዮን በእግሮቹ መሐል ብትገቢም አይነካሽም፤ ብላኝ ነበር፤ ይኼው
እውነት ሆነ" አለችኝ፡፡

የእንቆቅልሽ ሁሉ ጌታ ለዚህ ምስክርነት ብቁ ያደረገኝ የወጣትነት ትኩሳቴንና ሥጋዊ
ምኞቴን ቀዝቃዛ ውሃ ደፍቶበት እንጂ በእኔ ጉልበት እንዳልሆነ ተረዳሁ፡፡ አመሰገንሁትም።
በመሠረቱ ያቺ ልጅ ቀዝቀዝ ያለች ሰው ስለነበረች እንዲህ ትጋፋለች የሚል አሳብ
ኖሮኝ አያውቅም። ከበስተጀርባው አብሮ አደጌ አዳነች በፊደል ቆጠራው - ዱባንቾ፤
በጤና ረዳትነት ትምህርት ቤት - ሻሸመኔ (ኩየራ) አብራኝ የነበረች ሰው ነበረች።
ከልጅቱ ጋር አብረን ያዩን ሰዎች ሁሉ "እጮኛሞች" አድርገውናል። እኔም ነገር
ሁሉ ወደዚያው እንደሚያመራ በማመን የመሄጃዬ ቀን መጣና በመሸኛዬ እራት
ፕሮግራም ላይ ተገኝታ ቦሌ ድረስ ሸኝታኝ ተሰነባብተን ተለያየን።

ለመጀመሪያዎቹ ሁለት ወይም ሦስት ወራት ደብዳቤ ስንለዋወጥ ቆይተን ዘግየት
ብሎ የመጣልኝ ደብዳቤዋ ግን ረባሽና ከእሷ የማልጠብቀዉ ሆነብኝ። "አንተ
ፈረንጅ ልታገባ ነው አሉ እኔንም እንጠልፍሻለን እያሉ ያስፈራሩኛል" የሚል
ነበር ደብዳቤው። መልሼ በጻፍሁላት ደብዳቤ እኔ ፈረንጅ ላግባ አላግባ ስመለስ
ይታያል። "ሊጠልፉኝ ያስፈራራሉ" ላልሺው ጠልፈው ከሚያንገላቱሽ አውቀሽ
ብትሄጂ ይሻላል ብዬ ጻፍኩላት፡፡ የኛ ጉዳይ በዚህ ሲያበቃ ከአራት ዓመት በኋላ
ከአሜሪካ ስመለስ እርሷ አግብታ ወንድ ልጅ ወልዳ ቆየችኝ። ያገባችው ሰው ደግሞ
የማውቀውን ሰው ነበር። ልጅቱ በጐንደር ለዘመናት የኖሩት ቤተ-እሥራኤል
ማኅበረሰብ አባል ነበረች፡፡ በ1977 ዓ.ም ከቤተሰቧ ጋራ እንደገና ወደ እሥራኤል





ፈልሳ እዚያዉ ትኖራለች።

በስድስት ዓመቴ ግድም በእውቀት ሳይሆን በልጅነትና የዋህነት "እኔም እቀበላለሁ" ያልሁት ኢየሱስ ዘመኔን በሙሉ ሳይተወኝ እስከአሁን ድረስ መርቶኛል። በልጅነት፣ በወጣትነት፣ በጉርምስና እና አሁን ሽማግሌ በተባልሁበት ዘመን አብሮነቱን ነፍጎኝ አያውቅም። እኔ ታማኝነቴን ላጉድል እንጂ እርሱ ሁሌ ሳይሰለቸኝ ስመቸው በውስጤ ሳልመቸው በአጠገቤ ሆኖ ወደ ቀልቤ እየመለሰኝ ሕሊናዬን እየገራ ቸል እንዳልለው እየመከረኝና እየተንከባከበኝ ለዚህ አድርሶኛል። በምንም የማልመጥነውን "ጸጋዬ ይበቃሀል" ብሎ የመንግሥቱ አካል አድርጎኝ ለሆንኩትና ላደረግሁት ሁሉ ባለቤት ሆኖ ከኃጢአቴ በቀር የሁለንተናው መገለጫ ሆኖ አኑሮኛል። ሙሴ ኢያሱን "በፊትህ የሚሄድ እርሱ እግዚአብሔር ነው፤ ከአንተ ጋር ይሆናል፣ አይጥልህም አይተውህም፣ አትፍራ አትደንግጥም"። (ዘዳግም 31፥8) ብሎ እንዳበረታታው ለኔ ጌታ እንዲሁ ሆኖልኛል።

(የልዑል ራስ እሥራት ካሣ ሕንፃ) ውስጥ ነበርና ወደዚያ አመራሁ። እሷን በታክሲ ወደ ናዝሬት መኪና ተራ ሸኘኋት። ቁርስ ስንበላ፡-

"አዳነች ያለችኝ እውነት ሆነ" አለችኝ አግራሞትና ድንጋጤ በተቀላቀለበት ስሜት "ደግሞ ምን ብላሽ ነበር?"

"ተስፋጽዮን በእግሮቹ መሐል ብትገቢም አይነካሽም፤ ብላኝ ነበር፤ ይኼዉ እውነት ሆነ" አለችኝ፡፡

የእንቆቅልሽ ሁሉ ጌታ ለዚህ ምስክርነት ብቁ ያደረገኝ የወጣትነት ትኩሳቴንና ሥጋዊ ምኞቴን ቀዝቃዛ ውሃ ደፍቶበት እንጂ በእኔ ጉልበት እንዳልሆነ ተረዳሁ፡፡ አመሰገንሁትም። በመሠረቱ ያቺ ልጅ ቀዝቀዝ ያለች ሰው ስለነበረች እንዲህ ትጋፋለች የሚል አሳብ ኖሮኝ አያውቅም። ከበስተጀርባው አብሮ አደጌ አዳነች በፊደል ቆጠራው - ዱባንቾ፣ በጤና ረዳትነት ትምህርት ቤት - ሻሸመኔ (ኩየራ) አብራኝ የነበረች ሰው ነበረች። ከልጅቱ ጋር አብረን ያዩን ሰዎች ሁሉ "እጮኛሞች" አድርገውናል። እኔም ነገር ሁሉ ወደዚያው እንደሚያመራ በማመን የመሄጃዬ ቀን መጣና በመሸኛዬ እራት ፕሮግራም ላይ ተገኝታ በሌ ድረስ ሸኘችኝ ተሰነባብተን ተለያየን።

ለመጀመሪያዎቹ ሁለት ወይም ሦስት ወራት ደብዳቤ ስንለዋወጥ ቆይተን ዘግየት ብሎ የመጣልኝ ደብዳቤዋ ግን ረባሽና ከእሷ የማልጠብቀዉ ሆነብኝ። "አንተ ፈረንጅ ልታገባ ነው አሉ እኔንም እንጠልፍሻለን እያሉ ያስፈራሩኛል" የሚል ነበር ደብዳቤው። መልሼ በጻፍሁላት ደብዳቤ እኔ ፈረንጅ ላግባ አላግባ ስመለስ ይታያል። "ሊጠልፉኝ ያስፈራራሉ" ላልሺው ጠልፈው ከሚያንገላቱሽ አውቀሽ ብትሄጂ ይሻላል ብዬ ጻፍኩላት፡፡ የኛ ጉዳይ በዚህ ሲያበቃ ከአራት ዓመት በኋላ ከአሜሪካ ስመለስ እርሷ አግብታ ወንድ ልጅ ወልዳ ቆየችኝ። ያገባችው ሰው ደግሞ የማውቀውን ሰው ነበር። ልጅቱ በጐንደር ለዘመናት የኖሩት ቤተ-እሥራኤል ማኅበረሰብ አባል ነበረች፡፡ በ1977 ዓ.ም ከቤተሰቧ ጋራ እንደገና ወደ እሥራኤል





ሄልሳ እዚያዉ ትኖራለች።

በስድስት ዓመቴ ግድም በእውቀት ሳይሆን በልጅነትና የዋህነት "እኔም እቀበላለሁ" ያልሁት ኢየሱስ ዘመኔን በሙሉ ሳይተወኝ እስከአሁን ድረስ መርቶኛል። በልጅነት፣ በወጣትነት፣ በጉርምስና እና አሁን ሽማግሌ በተባልሁበት ዘመን አብሮነቱን ነፍጎኝ አያውቅም። እኔ ታማኝነቴን ሳጉድል እንጂ እርሱ ሁሌ ሳይሰለቸኝ ስመቸው በውስጤ ሳልመቸው በአጠገቤ ሆኖ ወደ ቀልቤ እየመለሰኝ ሕሊናዬን እየገራ ቾል እንዳልለው እየመከረኝና እየተንከባከበኝ ለዚህ አድርሶኛል። በምንም የማልመጥነውን "ጺጋዬ ይበቃሀል" ብሎ የመንግሥቱ አካል አድርጎኝ ለሆንኩትና ላደረግሁት ሁሉ ባለቤት ሆኖ ከኃጢአቴ በቀር የሁለንተናው መገለጫ ሆኖ አኑሮኛል። ሙሴ ኢያሱን "በፊትህ የሚሄድ እርሱ እግዚአብሔር ነው፤ ከአንተ ጋር ይሆናል፣ አይጥልህም አይተውህም፣ አትፍራ አትደንግጥም"። (ዘዳግም 31፥8) ብሎ እንዳበረታታው ለኔ ጌታ እንዲሁ ሆኖልኛል።

# ምዕራፍ ስድስት

# አዲስ የሕይወት ምዕራፍ

## 17.ትምህርት በአሜሪካ



ዓመቱ 1959 የነሐሴ ወር ነበር። ወደ አሜሪካ ለመብረር የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዘመድ፣ አዝማድ ጓደኛና ቤተ ክርስቲያን የአየር መንገዱን መሸኛ ሰገነት አጣብበው ሸኙኝ:: አውሮፕላኑ ወደ ፍራንክፈርት ይዞኝ በረረ:: ፍረንክፈርት ላይ ወደ ፓንአም (PAN AM) አይሮፕላን ስንዛወር የጥቁሮች ቁጥር በእጅጉ ቀንሶ የነጮቹ በዝቶ ልብ አልኩ:: አትላንቲክን አቋርጠን ፊላደልፊያ (PHILADELPHIA) ስናርፍ ጥቁር መሆኔ ቦግ ብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ ታወቀኝ።

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያዊነቴን ለማሳወቅ እስከጠየቅ አልጠብቅም ነበር። አብረን የተጓዝን አና ሎወስ ግሬብል ( Anna Louis Giraybill) የምትባል ሜኖናይት ሚሲዮናዊት ነበረች:: የእርሷ ቤተሰቦች ተቀብለውን የአንድ ሰዓት መንገድ






ነድተው ወደ ቤታቸው ወስደውን አሳድረውኝ በማግሥቱ በመኪናቸው ወስደው በሚሽን ቦርዱ እንግዳ ማረፊያ ቤት አሳረፉኝ። እዚያ ስደርስ ናፍታሌ ቢራይ የሚባል ከታንዛኒያ እንደእኔው ለትምህርት የመጣ ሰው አገኘሁ። ሁለት ሳምንት ከእርሱ ጋራ ቆይተን በወሩ (ነሐሴ) መጨረሻ ላይ ለሚከፈተው ትምህርት ቤት ወደ ሐሪሰንበርግ ቨርጂንያ (Harrisonburg, Virginia) ኢስተርን ሜኖናይት ኮሌጅ 250 ማይልስ በመኪና ወሰዱን::

የትምህርት ቤቱ ግቢ ያረፈው ከፍታ ላይ ስለሆነ ሁለት ወይም ሦስት ማይልስ ሲቀረን ደረቱን ገልብጦ ከነሞገሡ ብቅ ይላል። በቀይ ሸክላ የተሠሩት ሕንፃዎች የአስተዳደሩ፣ የመማሪያው፣ የመጻሕፍት ቤቱ አዲስ መጪውን ሁሉ ያስደምማሉ:: የተማሪ አስተናጋጆች አዲስ ደራሾቹን እየተቀበሉ በየመኝታ ቤታቸው የድልድሉን መዘርዘር እያዩ ይመሩና ያደርሱም ነበር። እኔ የተመደብሁት ሜፕል ውድ (Maple Wood) በሚባለው ሕንፃ 16 ቁጥር ክፍል ውስጥ ነበር።

ክፍሉ ሁለት አልጋ ያለበት ነበርና ቀድሜ ስለደረስኩ ከሁለቱ ምርጫ ነበረኝ። በመስኮት ጥግ የነበረውን መረጥኩት:: ከእያንዳንዱ አልጋ ጋር - የግል ቁምሣጥን፣ የጥናት ጠረጴዛና ወንበር ነበር። ትራስና የትራስ ልብስ ከታጠፉ ሁለት አንሶላና ብርድ ልብስ ጋር አልጋው ላይ አገኘሁ:: በጤና ረዳትነት ጊዜ አንዱ ትምህርት አልጋ ማንጠፍ ነበር፤ ጠቀመኝ፤ አልጋዬን በደንብ አነጠፍኩ:: ልብሶቼን ከሻንጣ አውጥቼ በቁም ሳጥኑና በኮመዲኖ መሳቢያዎች ውስጥ ሸሚዞቼን፣ የውስጥ ልብሶቼን ካልሲዎቼን በየዓይነታቸው ደርድሬ ስጨርስ ውጪውን ለመቃኘት ወጣሁ:: ከአንደኛ ፎቅ ወርጄ በመኝታ ቤቶቹ መካከል ለእግር መመላለሻ በድንጋይ ንጣፍ በሲምንቶ በተለሰኑት መንገዶች ላይ እገሬን ካፍታታሁ በኋላ ወደ መኝታ ቤቴ ተመልሼ ገላ መታጠቢያውን ልሞክር የምለውጠውን አዘጋጅቼ ገባሁ። ተማሪው ሁሉ ገና ስላልመጣ ያለሽሚያ ታጥቤ ወጣሁ። ትንሽ እንደቆየሁ 12 ሰዓት ደረሰና ለእራት ወዳመለከቱኝ ምግብ ቤት አመራሁ። የታንዛንያው ጓደኛዬም መጣና



ዓ
ነ
የ
ዘ
ከ
መ
ሽ
ፍ
ፍ
(የ
ስ
በ
አ
ፊ
ስ
ለ

በአንድ ጠረጴዛ ተቀመጥንና ተመገብን። "ከየት አገር ናችሁ" የሚል ልብ አውልቅ ጥያቄ ቢሆንም የማንኛውም ውይይትና ትውውቅ መክፈቻ ነበር። በትምህርት ቤቱ የምንሰየመው የነበረው የተለያዩ የውጭ ሀገራት ተማሪዎች (International Student) በመባል ነበር። ይኸ አካል በማኅበር ተደራጅቶ የተለያዩ ፕሮግራሞች እያዘጋጀ የራሱን አባሎች የሚያበረታታ ነበር። በሁለተኛው ዓመቴ የዚህ ማኅበር ፕሬዝዳንት ሆኜ አገልግያለሁ።

ጠቅላላ ገለጻ ለመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች የውጭ አገሮቹን ጨምሮ በሁለተኛው ቀን ተሰጠን። የትምህርት ክፍሎች፣ ቤተ መጻሕፍት ቻፕል፣ የስፖርት መሥሪያ (ጂምኔዝየም) እና የመሳሰሉት መገልገያዎች ሁሉ የት እንደሆኑ በዝርዝር አስረድተውን የመጀመሪያ ዓመት የኰሌጅ ትምህርት ምዝገባው ተጠናቅቆ ትምህር ተጀመረ። የአንደኛው ዓመት ትምህርት እጅግ ቢጠጥርም በጸሎትና በብርቱ ሥራ ያለማስጠንቀቂያ አለቀ። የመጀመሪያውን ዓመት ኢንተርናሽናል ተማሪዎች በትርፍ ሥራዎች እና እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉ ስለማይደፋፈሩ ፊታችንን በመጻሕፍት ውስጥ ቀብረን (buried in books) የመጀመሪያው ዓመት አለቀ። ውድድሩ ከፍተኛ እንደሆነም ሳይታለም የተፈታ ነበር።



እኔ ለመጀመሪያ ዓመት ኮሌጅ በቤተ ክርስቲያን ስላክ ከእኔ አንድ ዓመት በፊት የተላከው ላጺሶ (ዶ/ር) የመጀመሪያ ዓመት አጠናቅቆ ሁለተኛውን ጀምሮ ነበር። በዚያው መሠረት ተከታትለን እርሱ ሲጨርስ እኔ አራተኛ ዓመት ጨርሼ በባችለር ዲግሪ ስመረቅ መጥቶ አስመርቆኛል። የተማርሁት



ከሚሸግዳ እስከ ዓለም ዳርቻ

ታሪክና መጽሐፍ ቅዱስ ነበር። የተዘጋጀሁትም ወደ ኢትዮጵያ ተመልሼ እነዚህን ሁለት ትምህርቶች በባይብል አካዳሚ ወደ አገሩ የሚመለሰውን ዶ/ር ካልቭን ሽንከን ተክቼ እንዳስተምር ተወስኖ ነበር።አራቱ የኮሌጅ ዓመቶቼ መንፈሣዊውና ሥጋዊው ሕይወቴ ያደገባቸው ዓመታት ነበሩ። በኮሌጁም ተማሪና መምህራን ዘንድ ከፍተኛ አክብሮት አትርፌ በተማሪዎችም ሕይወት ጥሩ ሚና ተጫውቼ ያሳለፍሁበት ዘመን ነበር። የሥነ ሥርዓት ኮሚቴ አባል፣ የዋይ ፒሲኤ (Young Peoples Christian Association) አባልና (Student Government Association (SGA) Senator) በመሆን ክፍሌን ወክዬ ተመርጬ ነበር። ለዚህ ምርጫ ተማሪዎች እንዲወዳደሩ በካምፓስ ሬድዮ ሲነገር ሰምቼ አብሮኝ አንድ የመኝታ ክፍል ለምንጋራዉ ሪቻርድ በውማን (Richard Bowman) ለሚባል ሰው ስነግረው ከት ብሎ ሣቀብኝና "ማን ይመርጥሃል?" ሲለኝ ምንም ሳልመልስለት ሄጄ ተመዘገብሁ። ለምን መመረጥ እንደምፈልግም በተሰጠው መድረክ ቆሜ "የተማሪ ጓደኞቼ ድምጽ በመሆን በአስተዳደሩና በተማሪው መሃል የበለጠ መግባባት እንዲኖር ጥረት ለማድረግ ነው" ብዬ ሐሳቤን ገለጽሁ፡፡ በምርጫው ዕለት ሁለተኛ ከፍተኛ ድምፅ በማግኘት ስመረጥ ያ ሰው ፊቱ ቲማቲም መስሎ ደስ ሳይለው "Congratulations" አለኝ፤ Thank you ብዬ ብቻ ተውሁት።

ይህ ሰዉ ትምህርቱን ጨርሶ ለአገልግሎት ወደ ኮስታሪካ ሄደ፤ እኔ ወደ አገሬ ተመልሼ በባይብል አካዳሚ ሳስተምር አንድ ቀን በስሜ የተላከ ልዩ የውጭ አገር ፖስታ ደረሰኝ፡፡ ስከፍተው ላኪው Richard Bowman ይላል፡፡ ሳነበው "ስላንተ ዝቅተኛ አስተሳሰብ ስለነበረኝ ነው እንደዚያ የሳቅሁብህ፤ ትክክልም እንዳልሆንሁ አሁን ስለተረዳሁ ነው ይህንን ዳብዳቤ ልጽፍልህና ይቅርታ ልጠይቅህ የተገደድሁ" ይላል፡፡ ይህንን አንብቤ ስስቅ "ምን የሚያስቅ ነገር አገኘህ?" ብለው የሥራ ባልደረቦቼ ሲጠይቁኝ አነበብሁላቸው፤ እነርሱም ተገረሙ።



በኮሌጅ ያሳለፍኩት ልምድ በሁሉም አቅጣጫ ደስ የምሰኝበት ነዉ:: ወደ ኋላ መለስ ብዬ ሳስብ አሁንም ፈገግ ከሚያደርጉኝ አንድ ሌላ ገጠመኝን ልጨምር። ስሙ ቦብ (Bob) ይባላል። ከዕለታት አንድ ቀን እኔ ከክፍል ወጥቼ ወደ ዶርሚቶሪዬ ስሄድ ከኋላዬ ፈጠን ፈጠን ብሎ አለፈኝ። የመኝታ ቤቶቻችን ፊት ለፊት በትይዩ ነበሩ። ካላይ ስንመጣ እርሱ በስተግራ የእኔ ደግሞ በስተቀኝ ነበር። ስለቀደመኝ እርሱ ዞሮ ገብቷል። እኔም ወደ መኝታ ቤታችን ሕንፃ ዞርኩ። ከኋላዬ የተወረወረ ፖም (Apple) ሽው ብሎ እኔን ስቶ ከፊቴ ባለው ግድግዳ ላይ አረፈ። እኔም ቶሎ ብዬ ወደ ኋላ ዞር ብዬ ሳይ በጨረፍታ አንድ ሰው ፈጥኖ ሲገባ አየሁና እየቀለደ "አስደነገጥሁህ አይደል!" ይለኛል ብዬ ቆሜ ባይ ባይ ብቅ አልል አለኝ።

ምናልባት ስልክ እየደወለልኝ ይሆናል ብዬ ወደ ክፍሌ ገብቼ ጠበቅሁት:: እንኳን ሊደውል ደብዛውም የለም። ሳላገኘው ቀናት በተቆጠሩ መጠን ነገሩ እየከነከነኝ ሄደ:: በሦስተኛው ቀን ከክፍል ወጥቼ ወደ ላይብራሪ ስሄድ ቁጭ ብሎ ሲያነብ አየሁት፤ ቶሎ መጻሕፍቴን አስቀምጬ ወደ ተቀመጠበት አዘገምኩ:: ውጪ ላናግርህ እፈልጋለሁ ስለው እሺ ብሎ ወደ መተላለፊያው (Corider) ወጣን::

እንደቆምን በቀደም አፕሉን የወረወርከብኝ አንተ ነበርክ አይደለም? ስለው ፊቱ ሳምባ መስሎ "አዎን" አለኝ:: እየተጫወትክ ነው ብዬ ቆሜ ብጠብቅህ ጠፋህ። ስልክ ትደውላለህ ብዬ ገምቼ ነበር፤ አልደወልክም፤ ምነው? አልሁት:: እርሱም "ከአንተ ጋራ ችግር ስላለብኝ ነው የወረወርሁብህ" ብሎ እቅጩን ነገረኝ:: ዘረኝነቱ ገባኝና አንተ በሽተኛ ሰው ነህና እኔ ደግሞ ለበሽተኛ ሰው መጸለይ እንጂ ሌላ የሚደረግ ነገር አላውቅም፤ ብዬው ወደ ላይብራሪ ተመለስኩ። እርሱ የአራተኛ ዓመት ተማሪ እኔ ደግሞ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ ነበርኩ። የትምህርት ዓመቱ አልቆ በምረቃው ቀን ጋዎኑንና ቆቡን እንዳረገ እኔን እየፈለገ መጣና:- "በአንተ ምክንያት ይህንን ትምህርት ቤት ግቢ (Campus) ጥሩ ሰው ሆኜ እየለቀቅሁ ነኝ"





ብሎ አቀፈኝ፤ አመሰገነኝ።

ያንን ሰው ፓርትላንድ ኦሪገን (Portland, Oregon) ከ25 ዓመት በኋላ በሰሜን አሜሪካ ሜኖናይት ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ጉባዔ ላይ አገኘሁት:: ሰላምታ ሰጠኝ እኔ ግን ረስቼው ሲያስታወሰኝ "በአንተ ምክንያት አፍሪካ ሄጄ ታንዛኒያ 3 ዓመት አስተምሬ ብዙ ቦታ ዞሬ አይቼ ተመለስኩ፤ እንዴት ረሳኸኝ" ሲለኝ በተራዬ ይቅርታ ጠይቄው አውርተን ተለያየን።

## የኮሌጅ ዕዳዬ

የኮሌጁን ክፍያ 3ኛውን እጅ (1/3) የምከፍለው እኔው እንደሆንኩ ቀደም ብሎ ተገልጿል። ይህንን ለማድረግ ደግሞ መሥራት ነበረብኝ። ሥራው በሚሽን ቦርድ በኩል ተጠይቆልኝ "በመጣ ጊዜ ሊጀምር ይችላል" የሚል መልስ ተሰጥቶአቸው ኖሮ እኔም ተነግሮኛል። እዚያ ትምህርት ቤት የሚዘጋው ከግንቦት ሦስተኛ ሳምንት ጀምሮ ነበር። ት/ቤቱ ያለው 250 ማይልስ ርቀት ላይ በቨርጂንያ ክፍለ አገር ነበር። ይህ ክፍለ አገር የሚገኘው ከፔንስልቫኒያ በስተደቡብ ነው አስተናጋጆቼ (Host family) የነበሩት ላንካስተር ከተማ ስለነበረ በዝጉ ጊዜ ሁሉ ወደዚያ መመለስ ነበረብኝ። በዝጉ የምቀይባቸው አስተናጋጆቼ Paul እና ማርታ (Martha) ብሩቤከር (Brubaker) ይባሉ ነበር። የላንዲስ ቫሊ (Landis Valley) ሜኖናይት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባሎች ነበሩ። በአራቱ ዓመት የአሜሪካ ቆይታዬ እዚህ (ኢትዮጵያ) ክረምት እዚያ (አሜሪካ) በጋና የገና ወይም የፋሲካ ዕረፍት ሲሆን ወደ ላንካስተር ሄጄ እቆይ ነበር።

ለመጀመሪያው በጋ ትምህርት ቤት ሲዘጋ ወደ ላንካስተር መጥቼ ሥራ ወደ ተገኘልኝ መሥሪያ ቤት (ኩባንያ) ወሰዱኝና ከኃላፊው ከዴል ሃይ (Dale High) ጋራ አስተዋወቁኝና በደስታ ተቀበሎኝ "እንግዳ እሰፋውን ታውቃለህ?" ብሎ

ሲጠይቀኝ 10ኛ ክፍል የባዮሎጂ (Biology) አስተማሪዬ እንደነበረ ነገርሁት። እርሱም ተማሪ በነበረ ጊዜ እነርሱ ጋ ሠርቶ እንደነበረና ጥሩም ሠራተኛ እንደሆነ ተነገረኝ። እኔንም በርትተህ ሥራ ማለትህ ነው ብዬ በውስጤ አሰብሁና ሳልናገረው አስቀረሁ። ኩባንያው የሚሠራው ትላልቅ የብረት ድልድዮችን ነበር። የብየዳ፣ የማጓጓዣ፣ የቀለም፣ የመቁረጫ፣ የመብሻ፣ የመሳሰሉት ክፍሎች ነበሩት። የኔ የመጀመሪያ ሥራ የሰጡኝ የብረቱን ዝገት በግራይንደር ማስለቀቅ ነበር። አንዴ አሳይተውኝ ግራይንደሩን በእጄ ለቀቁት።

እኔም ይህቺስ ቀላል ናት ብዬ እስነሣሁትና ብረቱ ላይ ሳስኬደው በኤሌክትሪኩ ጉልበት ተሽከርክሮ የለበስሁትን ሡሪ ከቅልጥሜ በታች ሸረከተልኝ። በዚሁ እለፈኝ ብዬ ጠበቅ አድርጌ ይዤ ሳስሄደው የተሻለ ታዘዘኝና ዋልሁበት።

አንድ ሁለት ቀን ይህንን ከሠራሁ በኋላ ወደ ቀለም ክፍል አዘዋወሩኝና ስቀባ ለራሴም ትንሽ ትንሽ እያስነካሁ እየተፈናጠቀብኝ በሳምንቱ ውስጥ የልብሴ መልክ እንደቀለሙ ቀይ (Orange) እየመሰለ ሄደ።



ወደ ትምሕርት ቤቱ እስከምመለስበት ሁለት ወር ተኩል ጊዜ ውስጥ አብዛኛውን ሥራ ተለማምጄ ነበር። መንጃ ፈቃድ ስላላወጣሁ የቀረኝ ሹፍርና ብቻ ነበር። ለመጀመሪያው ዓመት ይከፈለኝ የነበረው በሰዓት ሁለት ከሃምሣ (2.50) የአገሩን ብር (USD) ነበር። ከዚህ ገንዘብ ምንም ሳይቀንስ ተጠራቅሞ ወደ ሚሽኑ ይላከና





እነርሱም በስሜ ሂሣብ ከፍተው እያጠራቀሙ ለኮሌጁ ይልካሉ። በዚህ ዓይነት በአራተኛው በጋ ትምህርቴን ጨርሼ ተመርቄ ወደ ላንካስተር ስመለስ የነበረብኝ ዕዳ አንድ መቶ (100) ዶላር ብቻ ነበር። እሱንም አንድ ሰው የምረቃ ስጦታ ሰጥቶኝ ከት/ቤቱ ግቢ እግሬ ሳይወጣ ከዕዳ ነፃ ሆኜ ድግሪዬን ይዤ ወጣሁ። በነገራችን ላይ ይከፈለኝ የነበረውም የቀን ክፍያው በየዓመቱ እየተጨመረ በአራተኛው ዓመት ወደ አምስት (5.00) ዶላር ደርሶ ነበር። በግንቦት መጨረሻ ከኮሌጁ ተመርቄ ጥቂት ለመሥራት ወደ ላንካስተር ተመለስኩና ሥራውን ጀምሬ ለሁለት ወር ያህል ሠርቼ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ተዘጋጀሁ፤ ቲኬቱም ተገዛ። ወደ አገሬ ስመለስ በእግረ መንገድ የሆኑልኝ መልካም ነገሮች ደግሞ ቀጥዬ ልንገራችሁ፡፡

## 18.ወደ አገሬ

ጂ.አይ.ሌመን (G.I Lehman) የሚባሉ የኮሌጃችን የብሉይ ኪዳን መምህር በየዓመቱ የጉዞ ቡድን አሰባስበው የመካከለኛውን ምሥራቅ አገሮች ያስጎበኙ ነበር። እኔንም በስብሰባቸዉ እንዲያካትቱኝ ስጠይቃቸው "በአጋጣሚ የአንድ ሰው ቦታ ቀርቷል፣ አብረኸን ትችላለህ" በማለት ፈቃዳቸውን ገለጹልኝ፡፡ ለ1971 (እኤአ) መርሐ ግብር ጉዟቸዉ የሚፈለገውን ክፍያ ፈጽሜ ተመዘገብኩ። ጉዞው የሚሸፍነው ግሪክንና መካከለኛውን ምሥራቅ ነበር፡፡ እኔና ሮን ዳንሊንገር የሚባል የኮሌጅ ጓደኛዬ ቀደም ብለን ባወጣነዉ እቅድ መሠረት ስዊትዘርላንድን፣ ጀርመንን፣ አስትሪያን፣ ኢጣሊያንንና በመጨረሻም ፈረንሳይን ጎብኝተን ስንጨርስ እኔ ወደ አቴንስ በረርኩ። የሰሜን አሜሪካው የጉዞ ቡድን ከፕሮፌሰሬ ጋራ አቴንስ የገቡ ዕለት ነበረና ከአየር ማረፊያው በታክሲ ወደ ሆቴላቸው ሄጄ ተቀላቀልሁ።

በመጀመሪያው ቀን በአቴንስ ከተማ ያሉትን ታሪካዊ ሥፍራዎች እንደ አክሮፖሊስና ሌሎችንም በአውቶቡስ ዞረን ጎበኘን፡፡ በማግሥቱ በሌላ አውቶቡስ ተሣፍረን ተሰሎንቄና፣ ቆሮንቶስን ተዘዋውረን አየን፡፡ አቴንስ አድረን ወደ ካይሮ ግብፅ በረርን።



ለመጀመሪያው ዓመት ይከፈለኝ የነበረው በሰዓት ሁለት

ካይሮ ያሳለፍነው ሦስት ቀን ሲሆን ዋናው ትኩረታችን ማርያምና ዮሴፍ ሕፃኑን ጌታ ኢሱስን ይዘው በተሰደዱበት ወቅት የቆዩበትን ሥፍራ ማየት ነበር፡፡ በተጨማሪም አሮጌና አዲሱ ካይሮን፣ ፒራሚዶቹን፣ የገማል አብዱል ናስርን መቃብር ሌሎችንም ታሪካዊ በታዎች እንደ ሽቶ ፈብሪካ አሳዩን።

የግብጹን ጉብኝታችንን ከጨረስን በኋላ ከካይሮ ወደ አማን ዮርዳኖስ ነበር የበረርን። ያ በረራ ከቶ የሚረሳኝ አልነበረም። አጫጫኑ ራሱ የድሮውን የድሬዳዋ ባቡር አይነት ይመስላል፡፡ ልጅ የያዙ እናቶች፣ ወጣቶች፣ ሽማግሌዎች . . . በጠቅላላ ከሃምሳ የምንበልጥ ሰዎች ወደ አይሮፕላኑ ውስጥ ገባን፡፡ መቀመጫም ሆነ መታጠቂያ አልነበረውም፡፡ ዳሩ መታጠቂያ የሚኖረዉ አስቀድሞ ወንበር ሲሠራለት ነዉ፡፡ ከሰዉ ሌላ ክፍት ቦታዎች ሁሉ ዕቃ ተጠቅጥቆበት ሲነሣ ማጓራት ጀመረ፡፡ አይሮፕላኑ ራሺያ ሰራሹ ኢሉሺን ነዉ፡፡ ተንቀጥቅጦ እና ተርገብግቦ ተነስቶ ከአሥር እና ከአሥራ አንድ ሺህ ጫማ በማይበልጥ ከፍታ በርሮ አማን ደረሰ፡፡ እስከ አረፈበት ጊዜ ድረስ ከቀጠለው መርገብገብ ከፍና ዝቅ እያለ ከመናጡ ሌላ አየር ማቀዝቀዣው አይሠራም ነበር፡፡ በሙቀትና በላባችን ንፍሮ ልንሆን ጥቂት ሲቀረን ነበረ አማን ያረፈው። ካረፈም በኋላ የአማን ከተማ ሙቀት በወናፍ እንደሚነፋ ምድጃ እሳት እንፋሎቱ ይጋረፍ ነበር። እኛ ስንደርስ ዮርዳኖስ በሌላ ግለት መንደድ ጀምራ ገና አልበረደላትም ነበር። ይኸውም በዚያች አገር ለረዥም ጊዜ የኖሩ ፍልስጥኤማውያን የንጉሥ ሑሴንን መንግሥት ለመገልበጥ ውጊያ ከፍተው ለቀናት ከፍተኛ ጦርነት ያካሄዱበት ሰሞን ነበር፡፡ ዐመፁን የዮርዳኖስ ወታደሮች ቢደመስሱትም አልፎ አልፎ የተለያየ መሣሪያ ተኩስ ይሰማ ነበር፡፡ በየመንገዱ ማቋረጫ የነበረውን ከፍተኛ ፍተሻ ዳግም ያየሁት በደርጉ ዘመን ብቻ ነበር።

ሁኔታው በዮርዳኖስ ብዙም ስላልተመቸን ፔትራ በሚባል ቦታ የነበረውን





የሮማውያንን ኮለሲየም ጎብኝተን አንዱን ቀን ዝምብለን አሳለፍነዉ፡፡ በሦስተኛው ቀን ወደ ሦርያ ዋና ከተማ ወደ ደማስቆ በመኪናዎች ተጓዝን። እዚያም እንደዚሁ ጉብኝት ስናደርግ ለዚህ ጸሐፊ አእምሮ ተመችቶት የነበረዉና ሁሌም የማይረሳው “የደማስቆ መንገድ” ጉብኝት ነዉ፡፡ ያም የሳውል መንገዱም፣ ሕይወቱም ተልእኮውም እስከወዲያኛዉ የተለወጠበት ሥፍራ መሆኑ ይታወቃል፤ (የሐዋ ሥራ 9፥4)፡፡ በሦሪያ ሌሎችንም የታሪክ ሥፍራዎች ጎብኝተናል። ይኸኛው ግን በአእምሮዬ ውስጥ በጹኑ ተሰግስጐ ቀርቷል። ምንአልባትም የጳውሎስን ታሪክ አስቀድሞም እወድደው ስለነበረና ከዚያ ግንኙነትና መገለጥ በኋላ ጳውሎስ ለጌታ ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ ስለምደነቅበትም ሊሆን ይችላል።

የደማስቆን ጉብኝታችንን አብቅተን ወደ ሊባኖስ ዋና ከተማ ቤሩት አሁንም በመኪና ተጓዝን። በዚያ “የሊባኖስ ዝግባ” (1ኛ ነገ. 4፥33) የተባለውንና የሰዶም መንደር ተብላ ታሪኳ ከመጽሐፍ ቅዱስ “ሰዶምና ገሞራ” ጋር ይያያዛል የተባለውን ደቡባዊ ሊባኖስን ጎብኝተን ነበር። የሊባኖስ በተለይም የቤሩት ከተማ ባሕልና ሥልጣኔ ከአረቦቹ ይልቅ ከፈረንሳይ ጋራ የሚወዳደር እንደነበረ አስታውሳለሁ። ይሁን እንጂ ከብዙ ጦርነቶች መፈራረቅ በኋላ ያቺ ከፓሪስ ጋራ ትወዳደር የነበረችው ውቧ ቤሩት በ1990ዎቹ አውሮፓውያን አቆጣጠር ተመልሼ ስሄድ እጅግ የምታሳዝን ከተማ ሆና ነበር። በመድፍ ጥይት የተቦዳደሱ ሕንፃዎች አንገታቸውን ደፍተዉ፣ መንገዶቹም ተቆፋፍረዉ ነበር።

ውቧን ቤይሩት ጉብኝት ጨርሰን በመርሐ ግብራችን መሠረት የምንበርረው ወደ እሥራኤል ሲሆን ከ1967ቱ (እ.ኤ.አ) ጦርነት ጊዜ ጀምሮ ወደ እሥራኤል በቀጥታ ከአረብ አገሮች ተጉዞ የነርሱ ቪዛ በታተመበት ፓስፖርት መግባት አይቻልም ነበር። የእሥራኤልም ቪዛ የተሰጠን በነጭ ወረቀት ታትሞ ነበር እንጂ በፓስፖርታችን አልነበረም። ምክንያቱም አረቦችም ወደ እሥራኤል የሚሄደውንም

ሆነ የሚመለሰውን ወደ ድንበራቸው አያስገቡም ነበር። ስለዚህ የነበረው ምርጫ ወደ ቆጵሮስ ደሴት መብረርና ከዚያ ወደ እሥራኤል መቀጠል ነበር። ያኔም ሆነ ከዚያ በኋላ ሦስት ጊዜ ተመላልሼ ወደ እሥራኤል ሄጃለሁ። አንዱና አንዱ በጣም የሚያስጠላው እና ለምን መጣሁ የሚያሰኘዉ ሲወጣም ሆነ ሲገባ ያለው ፍተሻና በጸጥታ ሠራተኞች የሚቀርቡ የምርመራ ጥያቄዎች ናቸው። ለምሳሌ አንዱን የደቡብ አፍሪካ ዜጋ የሆነውን ጓደኛዬን ቺካጐ ላይ ምርመራውን አልጨርስ ብለው ሊበርበት የነበረው አይሮፕላን ትቶት ሄደ። እኔ ገብቼ አንድ ቀን ሙሉ ያንን ጓደኛዬን ጠብቄ ከሀያ አራት ሰዓት በኋላ በሌላ በረራ መጥቶ በመልሱም ጉዞ ልክ በዚሁ ምክንያት በረራው አመለጠውና 24 ሰዓት መጠበቅ ነበረበት። የእርሱን ያህል የጠበቀ ባይሆንም በእኔም ላይ ያደረጉት ነው። ቢሆንም ይህ ሁሉ የሚሆነው በክበባቸው የጠላት ብዛት ስለሆነ በትዕግሥት ከመቀበል ሌላ አማራጭ የለውም።

ለማንኛውም ወደ ኒቆሲያ ልመለስና አየር ማረፊያው ውስን ዕቃችንን አብጠርጥረው የ32 ሰው ሻንጣ ፈትሸው ሲያበቁ በአይሮፕላናቸው አስገቡንና በርረን ቴሊአቪቭ አረፍን፡፡ የኢምግሬሽን ጣጣ ጨርሰን በአውቶብስ ወደ ኢየሩስአሌም አመራንና ማረፊያችን ወደ ሆነው ወደ ኪንግ ዴቪድ (King David) ሆቴል ደርሰን ክፍሎቻችንን ያዝን።

በማግሥቱ የአሥር ቀን ጉብኝታችንን ከቤተልሔም ጀመርን፡፡ ከልደቱ እስከ ሞቱ ከዚያም እስከ ትንሣኤውና እስከ ዕርገቱ ያለውን የጌታችንን የየሱስ ክርስቶስን ታሪክ ማስተማር ከጀመረበት፣ ደቀመዛሙርቱን የመለመለባቸውን ሥፍራዎች፣ ድንቅንና ተአምራት የፈጸመባቸውን ቦታዎች፣ ከናዝሬት እስከ ገሊላ ባሕር፣ ቀጥሎም እስከሙት (Dead sea) ባሕር የዳዊት በሮች የሚባሉት ያሉበትን የኢየሱሳሌምን ግንብ የአብረሃምን መቃብር የያዕቆብ ጉድጓድና ሌሎቹንም ሁሉ በአሥሩ ቀን ጉብኝት ልናይ ችለናል። ነገሮች የተፈጸሙባቸውን ሥፍራዎች ብቻ





ሳይሆን በሕይወት ላይ የተለየ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ልዩ ጉብኝት ሆኖልን አሥሩ ቀን ጭልጥ ብሎ አለቀ። በዚህኛው የጉዞአችን ክፍል በየማታው እየተገናኘን ከፕሮፌሰራችን ጋራ ውይይት/ ጥያቄና መልስ ጊዜ ነበረንና ትምህርታዊና ወደር ያልነበረው ሆኖልናል።

## አዲስ አበባ

እንደማንኛውም መልካም ነገር ሁሉ ይህም ጉዞ ጣፋጭነቱ እንዳጓጓን አበቃ፡፡ ሰላሳ አንዱ የቡድኑ አባሎች ወደ ሰሜን አዙረው ቱርክ (ኢስታምቡል) በረሩ፡፡ እኔ ደግሞ ወደ ደቡብ (ኢትዮጵያ) ለመብረር አንድ ቀንና ሌሊት በእዚያው ኪንግ ዴቪድ ሆቴል ማሳለፍ ነበረብኝ፡፡ አጋጣሚውን ወደ ኋላ መለስ ብዬ ባለፉት አራት አመታት በትምህርት ገበታም ሆነ ከማሕበራዊ ሕይወት ተሳትፎ በእሥራዔልም ጉብኝት የተቋደስኳቸውን ትርፍና ኪሣራ ለማስላሰል ጊዜ አገኘሁ፤ እንኳሮቹንም ወደ ማስታወሻዬ ውስጥ አስገባሁ።

በማግሥቱ ከአራት ዓመት በፊት ለቅቄ ወደ ሄድሁባት አዲስ አበባ በክረምት እንደ ሄድኩ በክረምት ተመለስሁ። በረራዬ ከቴላቪቭ ከሌሊቱ በዘጠኝ ሰዓት ተነስቶ አዲስ አበባ የደረሰው ከንጋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ነበረ። የመመለሻዬን ቀን ለዘመድ አዝማድ፣ ለወዳጅ ለጓደኛም አልተናገርኩም ነበር። ስሄድ የቦሌን አይሮፕላን ማረፊያ አጣቦ የነበረው ሸኚ ስመለስ ሁሉም በየቤቱ ነበር የጠበቀኝ።

በመድረሻ ያለውን የአየር ጣቢያ ጣጣ (ኢሚግሬሽንና ጉምሩክ) ጨርሼ እዚያው ካለው ባንክ ምንዛሬ ለውጬ ሻንጣዬን ገፍቼ ወጣሁና አንድ ታክሲ ይዤ ወደማውቀው ካሣንቺስ ወደነበረው ሜኖናይት እንግዳ ማረፊያ (Mennonite guestshouse) እስከፍቼ ገባሁ። እሥራኤል በከባድ ሙቀት ሸኘችኝ፣ አዲስ አበባ በብርድና በዝናብ ተቀበለችኝ። የእንግዳ ማረፊያው አስተዳዳሪ ሣራ ራሽ

(Sara Rush) ትባል ነበረና ክፍል ሰጥታኝ ለመተኛት ሞከርኩ፤ ግን እንቅልፍ በዓይኔ ውልብ አልል አለኝ፡፡ ለቁርስ ተነስቼ ከነበሩት እንግዶችና ከአስተዳዳሪዋ ጋራ እየተጫወትን ቁርስ ተበላ። ከዚያም የብዙ ሰዎች መገናኛ ወደ ነበረው ሜኖ መጻሕፍት መደብር (Menno Book store) ቸርቺል ጎዳና ጫፍ ሄድሁ፡፡ ብዙ ወደጆቼንም እዚያዉ አገኘኋቸዉ፡፡ "ለምን አልነገርከንም" እያሉ የተቆጡም ነበሩ።

## የኮሌጅ ጓደኞቼ በአገር ቤት

እሁድ መጣና ለአምልኮ ወደ አሁኑ ሰሜን መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን (ያኔ ብቸኛዋ) ሄጄ አምልከን ከሕዝቡ ጋራ ስወጣ ሁለት ወጣት ፈረንጆች የኮሌጅ ጓደኞቼ ጂንና ማርጋሬት የአጥሩን በር መግቢያ ይዘው ቆመዋል። (Gene and Maragret) ምንም ሳያወሩ ድንገት ስለአየሁዋቸው ድንግጥም ድንቅም አልሁ። ይጠብቁኝም የነበሩት የሚያውቁኝም እኔኑ ስለሆነ እንግዶቼ ሆኑ። ጂን ወደ ደቡብ አፍሪካ ማርጋሬት ደግሞ ቦትስዋና (Botswana) ለማስተማር ይሄዱ ነበር። ማርጋሪት እዚሁ ቅሪ እንድላት ፍላጎቷ እንደነበረ ምን አልሺኝ? በማያሰኝ ቋንቋ ነግራኝ ነበር። ነገር ግን አልመጣልኝም። ሁለቱ ጓደኞቼ ለሳምንት ያህል ጉብኝታቸውን ጨርሰው ወደ ሥራ ምድባቸው ሄዱ፡፡ በመሰረቱ በውስጤ ፈረንጅ የማግባት አሳብ ከዚያም አስቀድሞ ያኔም አልነበረብኝም፡፡ ፈረንጅ ያገቡ ጓደኞቼ ምንም ለውጥ ሳያመጡ ጓደኞቼ እንደሆኑ ኖረዋል፡፡ አሁንም አሉ። እውዳቸዋለሁ አከብራቸዋለሁ ሚስቶቻቸውንም ጭምር።

## እዚህም እዚያም

ለቤተ ክርስቲያኔ የገባሁትን ቃል ጠብቄ ወደ አገር ስመለስ በሠለጠንኩበት ሙያ ናዝሬት ባይብል አካዳሚ ለማስተማር ነበር። የዓመቱ የትምህርት መርሐ ግብር እስቲጀመር ሁለት ሳምንት ያህል የጊዜ ክፍተት ስለነበረኝ እዚህም እዚያም እያልኩ





ዘመዶቼንና ወዳጆቼ ስጠይቅ ከረምኩ፡፡ በመጀመሪያ የሄድኩት ወደ ወላጆቼ ነበር፡፡ በሕዝብ መጓጓዣ ሻሸመኔ ከዚያም ወደ ዱራሜ ተሣፍሬ ደረስኩ፡፡ አቶ ጌታቸው ሻንቆ (የአጎቴን ልጅ) አገኘሁና በቅሎውን ከሚመልስ ልጅ ጋራ ሰጠኝና እተወለድሁባት ፍልቅልቅ መንደር ሚሽግዳ አመራሁ።

ልክ ወደ ሰፈራችን ስጠመዘዝ ከማውቀው ዘመድ ቤት ነጠላ የለበሱ ሴት በርቀት ብቅ አሉና ወደኔ እያዩ ቆሙ፡፡ እኔም በውስጤ እማማ ይሆኑ ይሆንን እያልኩ ተጠጋኋቸዉ፡፡ እውነትም ያለምንም ቅድሚያ ቀጠሮ የጠበቁኝ እናቴ ነበሩ። ከበቅሎው ወርጄ፣ ተከትሎኝ የመጣው ልጅ አመስግኜ ተሰናበትኩት፡፡ ከእማማ ጋር ረዥም የናፍቆት ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ እየተጫወትን ወደ አባቴ ቤት ሄድን፡፡ አባባ ጋቢአቸውን እንዳጣፉ ደጅ ቆመው አላፊ አግዳሚውን እያዩ በደቀያ ሜዳ የጧቱን አየር እየሳቡ በሩቁ ትኩር ብለው ሲያዩን ማንነታችን ለይተዉ ነበር፡፡ "የት ተገናኝታችሁ ነው?" እያሉ ሰላምታ ተለዋውጠን ወደ ቤት ገባን።

ቁርስ ቀረበና ቡና ደርሶ ጠጣን። ሌሎችም ዘመዶችና ጎረቤቶች መምጣቴን ሰምተው ይሆን እግር ጥሎአቸው አላውቅም ብቻ መጥተው ቡና ጠጥተው ተጫውተን እንዳመጣጣቸዉ ሄዱ። እማማ በጠዋት ከቤት ወጥተዉ ያገኘኋቸው ጎረቤት መንደር የታመመ ሰው ለመጠየቅ ነበር። ከአባታችን ከተለያዩ አሥራ ሰባት ዓመት ሆኖአቸዋል። የሚኖሩትም በተወለዱበት ቀበሌ ቃጨቢራ ከወንድሞቻቸው መሬት ወስደው፣ ቤት አሰርተው፣ እንስሳትና የጓሮ አትክልትም እያለሙ ነበር። ነገ እመጣለሁ ብዬ ሸኘኋቸውና ቀኑን ከአባባ ጋራ በአካባቢው ያሉትን ዘመዶችና የምናውቃቸውን ጎረቤቶች ስንጠያይቅ ቆይተን ውዬ አደርኩ።

በማግሥቱ ረፋዱ ላይ በእግር የጨሜን ተራራ አቋርጬ ወደ እናቴ ቤት ቃጨቢራ ሄድሁ። ስደርስ ቤቱ በነደደው እሳት በሚሠራው ምግብና በሚፈላው ቡና ሞቆአል። አንድ ሁለት አጎቶቼ (የእናቴ ወንድሞች) መጥተው ቤቱን የበለጠ

አሟሙቀውታል። ምግቡ እየተበላና ቡናው እየተጠጣ ጨዋታው ደርቶ ዋልን። እዚያው መጠየቅ የነበረባቸውን የአጎቶቼን ቤተሰቦች እየዞርኩ ጠየቅሁና በአመሻሹ ላይ ወደ እናቴ ቤት ከቀሩት እሁቴ ዘነበችና ወንድሜ ታደሰ ጋራ ስንጫወት አምሽተን እዚያው አደርን። በሁለቱም ወላጆቼ ቤቶች እየተመላለስሁ አንድ ሳምንት ያህል ቆይቼ ወደ ናዝሬት ሄድኩ። ከወላጆቼ አገር ይልቅ ብዙ ወዳጅና ዘመድ፣ የሥራዬም ዕድል ፈንታ እዚያ ተቋጥሮ እንደ ነበረ አንባቢ አይዘነጋውም፡፡ ወደ ቤተሰብ ነገር ልመልሳችሁ፡፡

## 19.እማማና 17ቱ ዓመታት

ይህንን ክፍል እመለስበታለሁ ብዬ ነበር እነሆ አሁን ተመልሻለሁ። በ1947 ዓ.ም እማማ **እሁቴን ዘነበችን** አስከትለው የመጨረሻ **ወንድማችንን ታደሰን** አዝለው ሰባታችንም የተወለድንበትን ቤታቸውን ትተው ወደ ተወለዱበት ቃጨቢራ ሲመለሱ ከዓይኔ እስኪጠፉ ቆሜ ሳያቸው ከነበረበት ከአንቅልፋ እንደነቃ ሰው ሆኜ ጐረቤቴና ጓደኛዬ ወደሆነው ዮሐንስ ምርከኖ ቤት ጐራ እንዳልኩ አንባብዬን ላስታውስ።

እንግዲህ መታወስ ያለበት ጉዳይ ሰባት ልጆች የወለደች እናት የለማና የዳበረ ትዳርዋን ጥላ ቀድሞ ስታገባ ወደነበረችበት ኑሮ መመለስ ማለት ምን እንደሆነ አንባቢዎቼ ልብ በሉ። እናትም እንኳን ብትሆን ያንን ሁሉ ዘመን በቤትዋ የኖረች ያፈራችና ያስተናገደች ሰው ግማሽ ዕድሜዋን ካሳለፈችበት ተፈናቅላ ስትመጣባት የምትቀበላት እሰዮ ብላ አይደለም። ተጠልታ ተንቃ በጥቅሉ ከሥራ የመጣችውን ልጅና እህት ወንድሞችም ሆነ ሚስቶቻቸው መሳቂያ መሳለቂያ ያደርጓታል እንጂ አቅፎ - ስሞ "እንኳን መጣሽልን" የሚላት የለም። የኔንም እናት የጠበቃቸው ተመሳሳይ ችግር እንጂ ተድላ አልነበረም። ሁለት ልጅ ይዘው መሄዳቸዉ ደግሞ አቀባበሉንም ኋላም ኑሯቸውን የባሰ አድርጐት ነበር።





እማማ በባሕርያቸዉ ማሸነፍን እንጂ መሸነፍን አያስተናግዱም። ሁኔታዎች በከፋ መጠን ጭራሽ አቅም እያበጁ እየጠነከሩ መጡ፡፡ በትዳራቸዉ መፍረስ ያጡት ንብረት ብቻ ሳይሆን ክብርና ማዕረግ ቅስማቸውን ሰብሮ እጅ አላሰጣቸውም። "ቀን እስኪወጣልህ የአባትህ ባሪያ ይግዛህ" እንደሚሉት ሲመች በመልካም ጠባይ ሳይመችም ደግሞ በአቅማቸዉ ሁሉ እውነትን አንግበዉ ይጋፈጣሉ፤ ይህን ጠባያቸውን እንኳን ከማሕፀናቸው የወጣን ልጆቻቸዉ ቀርቶ ጐረቤትና የአካባቢያቸዉ ማኅበረሰብ አባላት ሁሉ የሚያውቀው የእማማ ባሕርይ ነው።

እማማ በመጀመሪያ ያረፉትበት የእናታቸው ቤት ብዙ ለመቆየት የማይቻላቸዉ እንደሆነ ከሁሉም አግጣጫ ግልጽ ሲሆንላቸው ሚስቱ ሞታበት ባዶውን (ወንቱ) የነበረ የወንድማቸውን ቤት አስፈቅደዉ የነበረቻቸውን አንድ ላምና ጥጃ ከሁለቱ ልጆቻቸው ጋር ይዘው ገቡ። ያም ቢሆን የራሳቸዉ ንብረት ስላልሆነ ሰላም አሳጣቸዉ፡፡ ስለሆነም ከልማዱ ያፈነገጠ ቢሆንም የራሳቸዉ ጎጆና ማሣ እንዲኖራቸዉ አጥብቀዉ ጥረት ማድረግ ጀመሩ፡፡ ጥረታቸው በቅርብ ቤተሰቦቻቸዉ ዘንድ የተነወረ ሆነ፡፡

"ትውከት ከመጣ ጥርስ አይከለክልም" እንደሚባለው ታላቅ ወንድማቸውና ሚስቶቻዉ የፈሩት አልቀረላቸውምና እማማ ቤት መሥሪያ ቦታ ብቻ ሳይሆን ለእርሻም ጭምር የሚሆን መሬት እንዲሰጣቸው ታላቅ ወንድማቸውን ለመጠየቅና ለማስጠየቅ ቆረጡ። እንደዚህ ዓይነት ርስት የመካፈልን ያህል ከባድ ጥያቄ "ሴት ልጅ ማቅረብ አትችልም" የሚል አመለካከት በብርቱ በሰረፀበት ማኅበረሰብ ውስጥ መሬት መጠየቅ 'ሳይነሱ መሸነፍ' ነበር። እማማ ግን ያንን ብርቱ ልማድ ጥሰዉ ትግላቸውን ጀመሩ። ታላቅ ወንድማቸዉ ሁነኛ መልስ እንደማይሰጥ አስቀድመው የተረዱት እማማ ከአባትም ከእናትም ወገን አሉ የሚባሉትን ሽማግሌዎች ዞረው ጠርተው በቀጠሮ ቀን ለተሰበሰቡት ጉዳያቸውን አቀረቡና እንደ ሬትም ቢመር ቤት

መሥሪያው ብቻ ሳይሆን የእርሻውም መሬት ጭምር እንዲያካፍላቸዉ አደረጉ።

ይሁን እንጂ በዚህም በዚያም ቂም ተይዞ ወንድም ሚስቶቹና ልጆቹ ዝምድናውን ሁሉ ረስተውት በእናቴና በልጆቻቸዉ ላይ ይህ ነው የማይባል ፍላጻ ከየአቅጣጫው ይወረውሩ ጀመር። ከእማማ ጋራ ከአባታቸው ቤት ተፈናቅለው የሄዱት ዘነበችና ታደሰ ያንን ወቅት ሲገልጹ "ስደተኞች ይመስል ብቸኝነት ያጠቃን ነበር" ይላሉ።

ታላቅ ወንድማቸውና ቤተሰቡ ወከባ ባበዙባቸው መጠን የእማማ ብርታት እየጨመረ ሄደ:: መሬቱም ለማ ሕፃናት ልጆቻቸውም በአካልና በአእምሮ እየጎለበቱ ሸክማቸውን መጋራት ጀመሩ። ወንድሜ ታደሰ በበኩሉ:-

> "እኔን ወደ ኃላፊነት ፊጥኜ እንድገባ ያደረገኝ የየእማማ ልፋትና ትጋት ነዉ፤ እማማ ለማሠውም ሆነ ለጓሮው ሥራ ወይንም ውኃ ከወንዝ ለመቅዳት ማልደዉ ወፍ ሳይንጫጭ ነበር የሚነሱት፤ እላቸዉ እንዲያ ሲታትሩ እያየሁ መኝታዬ ላይ ተጋድሞ ለመቆዬት አይቻለኝም:: ስለሆነም ለወዲያዉ ተከትዬ ተነስቼ በእርሻውንም ሆነ በጓሮዉ ሥራ እሰማራ ነበር" ይላል።

በተጨማሪም እማማ ኑሯቸን ለማሸነፍ ብሎም ልጆቻቸውን ለማስተማር በቂ ገቢ ለማግኘት ሲሉ አረቂ (ካቲካላ) ማውጣት ጀመሩ:: ይህም ሙያ ሆኖ - በአካባቢው ካሉት ተመሳሳይ ምርቶች ተመራጭ ሆነላቸዉ እንደነበረ የሚመሰክርላቸዉ ደግሞ ሌላው ወንድሜ ወልዴ ነዉ።

እንግዲህ እንባበቢ "በነዚያ አስራ ሰባቱ ዓመታት የት ነበርክ?" ማለቱ አይቀርም። ወላጆቼ ሲለያዩ እኔ ገና አምስተኛ ክፍል የምጀምርበት ዓመት ነበር። ከዚያ ተነሥቼ በ17ቱ ዓመት ውስጥ እስከ ኰሌጅ ያለውን ትምህርት አጠናቀቅሁ። በየ መካከሉ ከሰባተኛ፣ ከዘጠነኛ እና ከአስራ አንደኛ ክፍሎች አቋርጬ ጤና ረዳት አስተማሪና ካሽር ሆኜ እንደነበረ በቀደሙት ክፍሎች ዘግቤአለሁ። በእነዚያ ትምህርት





ባቋረጥኩባቸው ዓመታት የተገኙት ሳንቲሞች የሚውሉት ለራሴና ለወንድሞቼ ትምህርት ብቻ ሳይሆን ለእናቴም ኑሮ መደጎሚያ ጭምር ነበር። የማገኛቸዉ ብጥስጣሽ ከሥሩት ቁምነገር መካከል እናቴ ደጋግመዉ የሚያነሷት፣ የማይረሷትም አጋጣሚ አለች:: እንደሚከተለዉ ልግለጸዉ::

በአንድ ክረምት እናቴን ለመጠየቅ ወደ ቤት ሄጄ ነበር:: ያኔ ሁላችንም የሌሊት ልብስ የሚባል ቅልጣን አናውቅም:: እኔ ራሴ ቀን ለብሼዉ በዋልኩት ነበር ሌሊቱንም ተኝቼበት የማድረዉ:: የዚያን ዕለት ግን የሌሊቱ ቅዝቃዜ አላስተኛኝ አለ። እንቅልፍ አጥቼ ስገላበጥ ሳለሁ እናቴ የሆነ ነገር ሲያጉመተምቱ ድምፃቸውን ሰማሁ:: የበለጠ ጆሮዬን አቁሜ የሚሉትን አጣርቼ ማዳመጥ ጀመርኩ፤

> "እትትትትት!! ... እትትትትት!!" ይላሉ፤ ከደቂቃዎች ዝምታ በኋላም
>
> "እትትትትት!! ... እትትትትት!!" . . . ይቀጥላል::ይህ ብቻ አልነበረም፤

በግራና

ቀኝ ጎናቸዉ የተኙትን ዘነበችንና ታደሰን ተጣርተዉ:-

> "ልጆች! ጠጋ ብላችሁ እቀፉኝ፤ ረ በረደኝ . . . እዎ እንደሱ . . .":።

ከራሷ ተርፋ ስንቱን የቤተሰብ አባላት ስታለብስ የነበረች እናት ግማሽ ዕድሜዋን ያህል ለፍታ ካፈራችዉ ቤት ንብረት ተገድዳ የፈለሰችን እናት ራቁትነት ለመግለጽ ከዚህ በላይ ምን አለ? እማማ በኋላ ቀር ልማድና ለሴቶች ደንታ በሌለዉ ማኅበረሰብ ውስጥ የትዳር መፍረስ የሚያስከትለዉ የጨርቅ ብቻ ሳይሆን የህሊናም ራቁትነት ማሳያ ናቸዉ ብል ማጋነን አይሆንም:: ያ በዚያች ደረቅ ሌሊት የሰማሁት የእማማ "እትትትትት!! ... !!" ድምፅ ለረዥምም ጊዜ ከአእምሮዬ አልወጣ ብሎ እንዲያውም እንደ ማለዳ ውርጭ ተጋግሮብኝ ከረመ::



ከግራ ወደቀኝ አቶ ታደሰ ፣ ወ/ሮ ዜና፣ ወ/ሮ ዘነበች፣ አቶ ወልዴ፣ ወ/ሮ ዘውዱ፣ ወ/ሮ ስናይት፣ ደራሲው አቶ ሱጋም

ማስከረምጠባ፤ትምህርቴንአቋርጬደርጋሚምአስተማሪነትተቀጠርሁ። ከመጀመሪያው ወር ደመወዜ ብርድ ልብስ እንዲገዙ ፍራንክ ላኩላቸው፡፡ የፍራንኩ መጠን ሃያ ብር (ብር 20) ይመስለኛል፡፡ ታናሽ ወንድማቸውን ሱጌቦን ይዘው ሺንሺቾ ገበያ ሄደው እኔ ነኝ ያለ (አሥመራ የሚባለዉ ብርድ ልብስ ሳይሆን አይቀርም) ብርድ ልብስ በአስራ ስድስት ብር ገዙ፡፡ ያኔ ሰፊዉ ሕዝብ የሚደርበዉ ጋቢና ቡልኮ እንጂ ብርድ ልብስ ብርቅና ዘመናይ ሐብታሞች ነበሩ የሚጠቀሙበት፡፡ እናም እማማ ከብርዱ ከመገላገላቸዉ ብቻ ሳይሆን ኩራትም እንደሆነላቸው በተደጋጋሚ አውርተውልኛል፡፡ በመሠረቱ በሁለት እግር ሳይቆሙ ለሌላዉ መድረስን የተማርኩት ከራሳቸው ከእማማ ነዉ። እንዲያ በመከራ የዘሩትን ደግነት እንዴት በደስታ እንዳጨዱ ለመዘርዘር ጊዜም ቦታም የለኝም፡፡

በእንዲህ ዓይነት መደጋገፍ በእግዚአብሔር እርዳታ አስራ ሰባቱን ዓመታት በጭንበት ማግሥት እኔ በአሜሪካ የኮሌጅ ትምህርቴን ጨርሼ ተመለስኩ። ወላጆቼ እንደዚያው እንደተለያዩ ነበሩ። ከአሜሪካ እንደተመለስኩ ወላጆቼን ለመጠየቅ ስሄድ መጀመሪያ ያገኘሁዋቸው እማማን ነበር፡፡ በዚሁ





ጉብኝት ላይ እንዳለሁ ነበር ለእናቴ አንድ ጥያቄ ያቀረብኩት። ጥያቄውም፡-

"በአባታችን ግቢ ውስጥ ቤት ብሠራለዎት ወደ ዚያ ይመለሳሉን?" የሚል ነበር። መልሳቸው እጅግ ያስደነቀኝና ከዚያ ሁሉ ዓመታት በኋላ ያልጠበቅሁት ምላሽ ሆነብኝ፡፡

"አግኝቼው ነው ወይ? "ደዕቅንዶ" ነበር ያሉኝ፡፡

የእማማን ምላሽ በልቤ ይዤ አባቴን ለመጎብኘት ሄድኩ። አንድ ቀን አመሻሹ ላይ ሁለታችንም ደጅ ቆመን የደቀያን ሜዳ እያየን፡-

"እዚህ ግቢ ውስጥ ቤት ሠርቼ እማማን ማምጣት ፈልጋለሁ"፤

አልኳቸዉ፡፡

የአባባም መልስ እንዲሁ አስገራሚ ነበር፡-

"ገንዘቡን አምጣ እንጂ ቤቱን እኔው እሰራለሁ፡፡"

በዚሁ መሰረት ቤቱ ተሠርቶ አለቀና እማማ በ1964 ዓ.ም በተለያዩ በአስራ ሰባት ዓመታቸው ወደ ሚሽግዳ ተመለሱ። አስራ ሰባት ዓመት የአለሙትን መሬት ትተዉ ለምን ተመለሱ? ስለምንስ መመለስ ፈለጉ? በሕይወታቸዉ ላይስ ምን ፋይዳ ይጨምርላቸዋል? ተመልሰውስ ከቀድሞ ባለቤታቸዉ ጋር እንደ ባልና ሚስት ቀጥለዉ ነበር? . . . ወዘተርፈ ጥያቄዎች መነሳታቸዉ አይቀርም፡፡ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት በቀድሞው የከምባታ ማኅበረሰብ ልማድ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ሴት ልጅ ከወለደችበት፣ ከከበረችበት ቤት መፍለስ ወደ ድህነት አዘቅት የመወርወር ያህል ከባድ ነዉ፡፡ እሱንስ እማማ በብርታታቸዉ አሸነፉት፤ ልጆቻቸውም ደረስንላቸዉ፡፡ነገርን ከመፈናቀል በኋላ የፍቺዉ ዋነኛ ሰለባ ራሷ ሴቷ ሆና ሳለች የማኅበረሰቡ አባላት በተለይም በቅርብ ዘመዶቿ የሚደርስባት ነቀፌታ፣ ትችት፣ የአንደበት ጅራፍ ስነ ልቡናዊ ውርደቶች ቀላል አልነበሩም፡፡



ከግራ ወደቀኝ አቶ ታደሰ ፣ ወ/ሮ ዜና፣ ወ/ሮ ዘነበች፣ አቶ ወልዴ፣ ወ/ሮ ዘውዴ፣ ወ/ሮ ሰናይት፣ ደራሲው አቶ ሱጋሞ



እናት 2007

እማማም የዚያ ሰለባ ሆነው ማሳለፋቸዉ ውስጣቸዉ የማይሽር ጠባሳ ጥሎባቸዉ ነበር፡፡ እኔም ከትምህርት ቤት ቋጥሬ ባመጣኋት ሳንቲም አባቴ ግቢ ውስጥ ቤት ሠርቼ እወስዳቸዉ ዘንድ በጠየቅኋቸዉ ጊዜ ያለ ማመንታት "አግኝቼው ነው ወይ? **"ደዕቅንዶ"** ሲሉ የመለሱት ያ ልማዱ፣ ወጉ፣ ያጠለሻባቸውን ከብር እንደ ገና ለመላበስ የነበራቸዉን ብርቱ ምኞት ያንጸባረቀ ነበር፡፡ ከተመለሱ በኋላ ግን ከቀድሞ ባለቤታቸዉ ጋር እንደ ባልና ሚስት አልሆኑም፡፡ እንዲያውም ወደ ግቢያቸዉ

ሲመለሱ ያገኟት የአባባ ሚስት ማርታ ጋር እንደ ታላቅና ታናሽ እህትማማች ተሰባስበዉ ነበር ያሳለፉት፡፡ ማርታ ተፈታች፣ ምን ያህል ትዳር እንዳስመረራት የተገነዘብኩት መንኩሳ ገዳም መግባቷን የሰማሁ ቀን ነበር፡፡ ከማርታ በኋላ አባባ አራት ሚስቶችን በየተራ አግብተዋል፡፡ ከፊሎቹ እማማን የከፉ ጣውን ፅዋ እንዳጠጧቸውና አንዳንዴም "ምነዉ ወደ እዚህ ግቢ ባልተመለስኩ?" እስከ ማለት እንደ ደረሱ ይናገራሉ፡፡ ለማንኛውም በጨቅላ ዕድሜዬ ሁለት ልጆቻቸውን ይዘው





ዓይኖቼ እስኪዝሉና እስኪሰወሩብኝ ድረስ ሲሄዱ ያየሁዋቸው እማማ ተመልሰው በቀድሞው ግቢአቸው በራሳቸው ቤት ተመቻችተዉ ሲኖሩ ማየት ለኔ ኩራት ከመሆኑም ሌላ የያኔውን ቁስሌን ሽሮልኛል።

ያ ቤት ከተሠራ አርባ ሁለት ዓመት ሆነዉ፤ አሁንም በጥሩ ሁኔታ አለ። አሁን ዘጠናዎቹን የአጋመሱት እማማ የቅርብ ክትትልና እንክብካቤ ስለ ሚያስፈልጋቸዉ አርባ ሁለት ዓመት የኖሩበትን ቤትና ቀዬቸውን ትተው በአዲስ አበባ ከእህታችን ወ/ሮ ዘነበችና ከባለቤትዋ ከአቶ ሣህለማርያም መናሞ ጋራ ይኖራሉ፡፡ አእምሯቸውም ሆነ ልቡናቸዉ ቁልጭ እንዳለ አለ። የሚወዱትን ቤታቸውንና አካባቢውን ለመተው የተገደዱት አብሮአቸው ሆኖ የሚረዳቸው ሰው በመታጣቱ ብቻ ነው። ይረዱአቸዋል ብለን ያዘጋጀንላቸውም ሰዎች የልብ አላደርስ እያሉ ጉዳት ላይ እንዳይወድቁብን ፈርተን ይኸኛውን አማራጭ ወሰድን።

በዚህ አጋጣሚ እማማን የመንከባከብ ኃላፊነት የተረከቡትን ዘነበችንና ሣህለማርያምን በሁላችንም ስም ጌታ ይባርካችሁ እላለሁ።



**አቶ ሣህለ ማርያም** **ወ/ሮ ዘነበች**



እናት 2007

ሣህለማርያምን በሁለቱ ጎኖ[illegible] ፊት ይገረሙም አላለሁ።



አቶ ሣህለ ማርያም ወ/ሮ ዘነበች

## 20. አዲሱ የሥራ ዓለም

ኮሌጅ በአሜሪካ ጨርሼ ወደ ኢትዮጵያ የተመለስሁት በ1963 ዓ.ም ክረምት በነሐሴ ወር መጨረሻ ላይ ነበረ። የ1964 ዓ.ም መስከረም ሲጠባ ትምህርት ቤት ተከፈተ። ለምዝገባ በተያዘው ቀን ቀጠሮ ልጆቻቸውን ከተለያዩቱ ጠቅላይ ግዛቶች ይዘው የመጡ ወላጆችና ተማሪዎች ግቢውን ሞልተው ገበያ ይመስል የነበረውን ጫጫታቸውን አስታውሳለሁ። ምዝገባው አብቅቶ አዲሶቹም ነባሮቹም ተማሪዎች ትምህርት ሲጀምሩ ግቢው ሕይወት ዘራ። ከአስተማሪዎቹ መካከል አዲስ መጤ እኔ ብቻ ነበርኩ። ትንሽ ዘግይቶ አቶ ዓለሙ ቸኮል በሲራኪውስ (Syracuse) ዩኒቨርስቲ ኤም ኤውን ተምሮ ተመለሰ።

የትምህር ቤቱ ዳይሬክተር የነበረው አቶ ነጋሽ ከበደ ከ10ኛ ክፍል ጀምሮ ጓደኛዬ ነበር። በሠራተኞች ማረፊያ ቤት ለጊዜው አብረን እንድንኖር ሲወሰን ደስ ብሎኝ ነበር። ነገር ግን ብዙም አልዘለቀም፤ እያመሸ መምጣት ጀመረ። ይህ ደግሞ በውጭ አገር ቆይቼ ለተመለስሁት ብቸኝነቴን አጎላው። እያደር ሲገለጥልኝ ለካስ ነጋሽ ያመሸ የነበረው ሁለት ዓመት አስቀድማ ከኮሌጃችን ለማስተማር ከመጣችው ከጃነት ሸርትዘር (Janet Shirtzer) ጋራ ቁም ነገር ማውራት ጀምረው ኖሮአል። ቀኑ ሲደርስ አብሮ የመኖሩ ነገር አበቃ፤ የጋብቻ ስነሥርዓት በዓላቸዉ ሲወሰን፤ እኔ ወጣሁ እርሷ ገባች። ባልና ሚስት ሆነው እየኖሩ ነው።

### አስተማሪና የተማሪዎች ዲን

ብዙም ሳልቆይ ሹመት ተሰጠኝ፤ አስተማሪና የተማሪዎች ዲን (Student dean) ተብዬ ሥራዬን ቀጠልሁ። ተማሪዎቹን በሚያስፈልገው የመምከርና ሲያስፈልግም የስነሥርዓት እርምጃ (Discipline ማድረግ) ይጠበቅብኛል፡፡ ስለሆነም ከሌሎቹ መምህራን ጋራ እየተማከርኩ ልጆች እንዳይጣመሙና የተቃና ዕድገት እንዲኖራቸው





መንከባከብ ትኩረቴን ወሰደዉ፡፡ በተጨማሪም የዓለም ታሪክ፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ ጂኦግራፊ አስተምራለሁ፡፡ በቆይታዬ ከሚያስደስቱኝ ነገሮች መካከል በየዕለቱ ከጠዋቱ አራት ሰዓት ተኩል ገደማ የሻይ እረፍት ስናደርግ ሁላችንም መምህራንና አመራር ሰብሰብ ብለን ቀልዱንም ቁም ነገሩንም እየተጫወትን ዘና የምንልበት ጊዜ አንዱ ነበር። በተጨማሪም ከአሥር ሰዓት በኋላ ደግሞ በተለያዩ ስፖርቶች የተለያየ ውድድር እያደረግን በተማሪውና በአስተማሪው መኻል ጥሩ መግባባት እንዲኖር እንተጋ ነበር። በዚህ ሁኔታ በባይብል አካዳሚ ያሳለፍኩት ሦስት ዓመት ጣፋጭ ነበር፤ በዚያም መቀጠል እንጂ ለጊዜዉ ሌላ አሳብ ም አልነበረኝም።

### ባይብል አካዳሚ

የናዝሬት ባይብል አካዳሚ የተመሠረተው በ1952ዓ.ም ነዉ፡፡ የተቋቋበትን ዓላማና ግቦች መሥራቹ የሆኑት ቸስተር ዌንገር ሚያዚያ 3 ቀን 2006 ዓ.ም በላኩልኝ ኢ-ሜል አስረድተውኛል። እነዚህም ግቦችና ተደራሽ የማኅበረሰቡ ክፍሎች የሚከተለው ናቸው።

- ✓ በሐረርጌ ክፍለ አገር በወበራ አውራጃ በደደር ከተማና በጋራ ሙለታ አውራጃ በበደኖ ከተማ የሚኖናይት ሚሽን ትምህርት ቤቶች የ8ኛን ክፍል የጨረሱ ተማሪዎች በዚያው ዓይነት ትምህርታቸውን በሁለተኛም ደረጃ ተምረው በመንፈሳዊውም ትምህርት እንዲያድጉ የሚያስችላቸውን ዕድል መከፈት፣
- ✓ ላኪው ሚሽን ቦርድም በቅላ በማደግ ላይ ላለችው መሰረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ከተማረው ኃይል መምረጥ እንዲችል ለዚያም ብቁ የሆኑ ሰዎችን ማዘጋጀት፣

- ✓ የኢትዮጵያ መንግሥት የትምህርት ሚኒስቴር ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በቀር ለሌላው ሚሽን በተከለከለው በሸዋ ክፍለ አገር በየረርና ከረዩ አውራጃ ናዝሬት ከተማ (አሁን አዳማ) ይህ አዲስ የሚከፈተው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወደ ዩኑቨርሲቲ ለመግባት ብቁ የሆኑ ተማሪዎችን እንዲያፈራ የመንግሥት ፍላጎት ስለሆነ፣
- ✓ እንደ ሜኖናይት ልምምድ መጽሐፍ ቅዱስን ተምረው ተማሪዎቹ እምነታቸውን በሕይወታቸው እየገለጹ በኅብረተሰቡ መሃል እንዲኖሩና፤
- ✓ በመጨረሻም የሚስተር ዌንገር የራሳቸው ግብ ያሉት በባይብል አካዳሚ ተምረው የሚመረቁ ሰዎች በማንም ሳይመኩ ራሳቸውን ችለው እንደ ቅዱስ ጳውሎስ "የገዛ ዱንኳናቸውን እየሰፉ" ለክርስቶስ ምስክሮች ሆነው ኑሮአቸውን እንዲገፉ"[25] የሚሉ ነበሩ።

ከፍ ብሎ እንደተገለጸው በትምህርት ቤቱ የመማሩንም ሆነ የማስተማሩን ዕድል ያገኘሁት እኔ ወደ ኋላ መለስ ብዬ ሳስብ እነዚህ አምስት ሰፋፊ ግቦች በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ተሳክተውለታል፡፡ ከዚያ ትምህርት ቤት የተመረቁ ሐኪሞች፤ ነርሶች፤ መሃንዲሶች፤ ምሁራን ተመራማሪዎች፤ የቢዝነስ ባለቤቶች፤ የድርጅት መሪዎች ኢኮኖሚስቶችና የፖለቲካም ተሳታፊዎች ነበሩ፤ አሁንም አሉ፡፡ በአገርና በዓለም ዙሪያ ሁሉ ተዘርተው በሙያቸው እያገለገሉ ያሉ እነዚህ የባይብል አካዳሚ ውጤቶች ትምህርት ቤቱ ለስኬታቸዉ ያደረገላቸውን መልካም አስተዋጽኦ ይመሰክራሉ።

ከነዚህ አብረን ከተማርን ጓደኞቼ አንዱ አቶ መና ተዋኸደ ለብዙ ዓመታት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ባልደረባ ሆኖ የኢትዮጵያን ሕዝብ ያገለገለና አሁን በውጭ አገር የሚኖር የተዋጣለት የቢዝነስ ሰው ሽብቶና ገዝፎ ከሃምሣ ዓመት በኋላ

[25] ቸስተር ዌንገር፤ ኢሜል፣ ሚያዚያ 3/2006 ዓ.ም.





ተገናኝተን የተጫወትነው እነዚያ አስተማሪዎቻችን የከፈሉት ዋጋና የሰጡን ምክር ለዛሬ ማንነታችን እንዳበቃን በታላቅ አድናቆት ነበር የተጨዋወትነው። ከእርሱ ሌላ ከባይብል አካዳሚ ምሩቃን የማልረሳቸውን ጥቂቶቹን ብቻ ልጥቀስ፡-

- አቶ ሌንጮ ለታ (ያኔ ዮሐንስ ለታ) በሙያው ኬሚካል መሃንዲስ
- ዶ/ር ነጋሦ ጊዳዳ - የኢፌድሪ ፕሬዝዳንት
- ፕሮፌሰር ላጲሶ ዲሌቦ - የታሪክ ተመራማሪ
- አቶ ነጋሽ ከበደ - የተቋም መሪ
- ቄስ ዶ/ር ደበላ ብሪ - የሥነ መለኮት ምሑር
- ወ/ሮ ብዙአየሁ ሾኔ - የቢዝነስ ሰው
- ወ/ሮ ሚሚ ታረቀኝ- የኢንሹራንስ ባለሙያ
- ዶ/ር ተናሲ ኒኮላ - በናታል ዩኒቨርሲቲ ደቡብ አፍሪካ የኢኮኖሚክስ ፕሮፌሰር
- ድምትሪ ኒኮላ - በካናዳ አየር መንገድ ፓይለት
- ነብዩ ሸኔ - በኡጋንዳ የበልጂግ የቴክኒክ ድርጅት ተጠሪ (Technical Corp Reperesentative)
- እሥራኤል ከተማ - UNDP Southern Africa
- ሉሌነሽ ከተማ - ሜዲካል ዶ/ር
- ሐና እስክንድር - ሜዲካል ዶ/ር
- የምሥራች ኃይለ መስቀል - ሜዲካል ዶ/ር
- መታሰቢያ አየለ - ነርስ
- በዕደ ለማ - ሜዲካል ዶር፤

# ምዕራፍ ሰባት

## ትዳር

ቀጥሎ የማካፍላችሁ የሕይወቴ ገጽታ ከኮሌጅ መልስ ካለፍኩባቸዉና ከላይ "አዲስ የሕይወት ምዕራፍ" ብዬ የከፈትኩት ትረካዎች አካል ነዉ፡፡ አዲስ ምዕራፍ የከፈትኩለት በረዥሙ ገጾች ለማተት ሳይሆን፣ ትዳር በራሱ ትልቅ ዓለም እንደ መሆኑ አስሼ ባልጨርሰውም ተገቢውን ማዕረግ (ፕሮቶኮል) ለመስጠት ያህል ነዉ፡፡

በ1953 ዓ.ም ግርማዊነታቸው ብራዚልን ለመጐብኘት ሄደው ሳለ ጄኔራል መንግሥቱ ነዋይና ወንድማቸው ገርማሜ ነዋይ ቅንጅት በጐደለው መልኩ በጥድፊያ የሞከሩት የመፈንቅለ መንግሥት ከሽፎ እነርሱም የእሳት እራት ሆኑ፡፡ ያን ጊዜ የሃያ አንድ ዓመት ወጣት ሳለሁ ሬድዮኔን አንግቤ በሰማሁት ሁሉ ሳጨበጭብ ነበር፡፡ ያ ንቅናቄ በእውነቱ እንደ ማንኛውም የዘመኑ ወጣት የግሌም ሆነ የቤተሰቤ ሕይወት አልፎም የማኅበረሰቤን መለወጥ አስመልክቶ አመለካከቴንና ስነ ልቡናዬን ያነቃነቀ ነበር፡፡ በ1966ቱ ንቅናቄ ጊዜ ደግሞ የሠላሳ አራት ዓመት ጎልማሳ ነበርኩ፡፡ የለውጥን ነገር ከቤተክርስቲያን እውነት አንፃር ማመዛዘንና ማገናዘብ የጀመርኩበት ጊዜ ነበር፤ ወጣትነቴ በሁለቱ አመፆች ጥላ ስር ማለፉ ይገርመኛል፡፡ ወደ ትዳሩ ዓለም ለመግባት የተንደረደርኩት በዚሁ ለውጥ ሰሞን ነበር፡፡ እያንዳንዱ እርምጃዬ ግን እንዳሰብኩት ቀላል አልነበረም፡፡

የኰሌጅ ትምህርቴን ጨርሼ ስመለስ ማሕበራዊ ትስስሬ ድሩ፣ ማጉ፣ ተበጥሶ ውሉ እንደጠፋበት ሸማኔ ወዳጆቼ የት? ወዴት? እና እንዴት? ብዬ ማፈላለጉ ከባድ የቤት ሥራዬ ነበር፤ አንድ፡፡ በሁለተኛ ደረጃም ከዕድሜዬ መብሰል በተጨማሪ ብቸኝነቱ ከብዶኝ ስለ ነበር ከኮሌጅ መልስ ቶሎ ትዳር ብመሠረት በወደድሁ ግና





የማውቃቸው አማኝ ሴቶች አግብተው ወይም ተይዘው ስለቆዩኝ ከአንድና ከሁለት ሙከራ በኋላ ደፍሮ ለመጠየቅም ተሰቀቅሁ።

ለምሳሌ አንዷን የማውቃትን ምራቄን ዋጥ አድርጌ ደፈር ብዬ አንድ ቀን ቢሮዋ ስሄድ በጨዋ ደንብ በጥሩ ተቀብላኝ ሰላምታ ተለዋውጠን ቆንጆ ማኪያቶ ተጋብዤ ልወጣ ስል "ከተመቸሽ ከሰሞኑ አንዱን ምሽት እራት ብጋብዝሽስ?" ስላት ፈገግታዋን ሳትነፍገኝ "እኔ እኮ እጮኛ አለኝ፤" ስትለኝ እንደ ደነገጠ ውሻ የሌለኝን ጭራዬን በሁለት እግሮቼ መካከል ሸግቤ ለመሮጥ ከቢሮዋ ለመውጣት መውጫው በሩ እንዴት እንደራቀኝ አይረሳኝም።

ሦስተኛዉ የምርጫ ጉዳይ ነዉ፡፡ ከዕድሜ ጋር የተያያዙት ጉዳዮች ብቻ በራሳቸዉ አዎንታዊና አሉታዊ ጐኖች አሉት። ቢቻል በሁለትና ሦስት ዓመት ልዩነት ዕድሜ ውስጥ ለትዳር ተፈላጊዎች ቢገኙ መልካም ሲሆን በአገራችን ነባሩ ሁኔታ ወንዱ ታላቅ ደግሞ ሴት ታናሽ ብትሆን በተለምዶ ይመረጣል። ይህንን ብለን ሳይሆን ለምሳሌ እኔ ባለቤቴን በስምንት ዓመት ስበልጣት የራሱ የሆኑ የተለየዩ ጐኖች ሲኖሩት ከዚህም የበለጠ የዕድሜ ልዩነት ሲኖር የመግባባት ችግር እንደሚከሰት ለመገመት ይቻላል። ከዕድሜአችን ጋራ አስተሳሰባችንም ስለሚለያይ በተቻለ መጠን የዕድሜን ክፍተት ለማጥበብና ለማቀራረብ መሞከር የሚመከር ነው። ሌላው ደግሞ "ዕድሜው /ዕድሜዋ ለጋብቻ ደርሶአል" በማለት ከቤተሰብ፣ ቤተ ዘመድ ከጓደኛም ጭምር ግፊት ሲጨመርበት በወንዱም ሆነ በሴቷ ላይ ቀላል ነው የማይባል ጫና ያሳድራል። በግፊትም የሆነ ነገር በተለይም የትዳር ቋጠሮው እያደር ይላላና መፈታቱ አይቀሬ ይሆናል። ስለዚህ ጋብቻን ዓላማቸው የሚያደርጉ ወጣቶች ለሚኖርባቸው ውጫዊ ግፊትም ይሁን ውስጣዊውን የስሜት ፈረስ ሉጋሙን ጠበቅ አድርገው ቢይዙት ለቁም ነገር መድረሳቸው አስተማማኝ ይሆንላቸዋል።

አራተኛዉ አቀራረብ ነዉ፡፡ መቼም መምረጥ በወንዱም ሆነ በሴቷ ያለ ነገር ነው።

አንድ የትምህርት ቤት ጓደኛዬ ከዚያው ትምሕርት ቤት ለምናውቃት ለአንዷን "ወደድኩሽ" ብሎ ማስታወሻ ጻፈላት። እርሷም እንደማይሆንላት ምክንያቷን ደርድራ መለሰችለት፡፡ በደብዳቤዋ ያለችውን ካለች በኋላ "ያንተው" ብላ ፈርማበት ነበር። ይህ አባባል ለጓደኛዬ አልተመቸውም፡፡ እንዴት "አይሆንም" ካለች በኋላ "ያንተው" ብላ ፈርማ ትላለች በማለት በልቡ ተነዋወጠ፡፡ ቀላል የማይባል ችግር ተፈጥሮበት እንደነበረና ለሳምንታት "ሰውም፣ እህልም አላይም" ብሎ አስቸግሮን ነበር። "ያንተው/ያንቺው" ብሎ መፈረም ቃል መገቢያ ሳይሆን የደብዳቤው መዝጊያ ከፈረንጆች "Yours" የመጣ ነው። አሁን እንኳን የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች ስለበዙ ደብዳቤው የሚጽፍም ያለ አይመስለኝም። እንዲህ እንዲህ ሆነና እንደ ይስሐቅ ብልሐተኛ አማጭ እስከማገኝ ወራትን በብቸኝነት አሳለፍኩ፡፡

በብቸኝነት ጊዜ ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለብዙ ላጤዎች የኋላውን መከለስ የወደፊቱንም በምኞት ማስመር የተለመደ ነዉ፡፡ ራሴን ስከልስ የአሥረኛ ክፍል ተማሪ ሆኜ እንደ ቀን ቅዥት (Day dream) ውስጥ ሆኜ ስለ ትዳርና ልጆች ማሰቤን አስታውሳለሁ፡፡ መጥቶልኝ የነበረው አሳብ እንደ ጣፋጭ ምግብ ጣዕም በውስጤ አሁንም አለ፡፡ ትዝ ይለኛል፤ ያኔ በሃያ አንድ ዓመቴ፡-

> "የማገባት ነርስ ብትሆን እወዳለሁ፡፡ መጀመሪያ ሁለት ወንዶች ቀጥሎም አንድ ሴት ልጅ እንወልዳለን" ስል ተመኝቼ ነበር፡፡

ነርስ ስለማግባቱ በጊዜው ልቤ ያመነበት ምክንያት ደግሞ፡-

> "በፊቱ የቆመውን ሁሉ የሚጠራርገው የአብዮቱ ነርፍ በአንድ ወይ በሌላ መልክ ቢደርስብኝ (ብሞት ወይም አንድ ነገር ብሆን)፣ የልጆቼ እናት ነርስ ከሆነች ሥራ አታጣም፤ ልጆቻችንንም በሚገባ ታሳድጋለች" የሚል ነበር፡፡

እዚያው - በዚያው ቀን ነበር ለሦስቱም ልጆቼ ስም ያወጣሁላቸዉ፡፡







ቤተሰባችን በኒውዘርላንድ ( 1976)


የመጀመሪያው ወንድ ልጅ የአያቴን ስም እወድ ስለነበረ "ዋቤቶ" እንዲሆን መረጥኩ፤ ትርጉሙ "የእግዚአብሔር ልጅ" ማለት ነዉ፡፡ ሁለተኛው ወንድ ልጅ "መና" እንዲባል ተመኘሁ፡፡ ትርጉሙ በከምባትኛ "ሰው" ማለት ነዉ፡፡ ለእሥራኤላውያን እግዚአብሔር ከሰማይ ያወረደላቸው ምግብ መና ነበር፡፡ በተጨማሪ ደግሞ የከፍል ጓደኛዬና የምወደው መና የሚባል ልጅ ነበር፡፡ ይህ ሁሉ ተደምሮ የሁለተኛው ልጃችን ስም መና እንዲሆን ወሰንኩ፡፡ እናቱ እርሱን እርግዝ ሳለች ብዙ ጊዜ ትታመም ነበር፡፡ የስምንት ወር እርጉዝ ሆና ቀበሌ "መጽሐፍ ቅዱስ አድለሻል" ብሎ ለአስር ቀናት አሰራት፡፡ በዚህ እንግልት መካከል ፅንሱ ጤነኛ ሆኖ ከተወለደ ስሙ እውነትም መና እንለዋለን ስንል ቆይተን ፍጹም ጤነኛ የሆነ ልጅ ተወለደልን፤ በዚያዉ አጸናነው፡፡

ሦስተኛዋ ልጅ ማኅሌት እንድትባል ነበር በዚያዉ በቀን ህልሜ ያወጣሁላት



ቤተሰባችን በኒውዚርላንድ ( 1976)

ስም፡፡ ልጃችን ተረገዘችና "ወንድስ ብትሆን?" የሚል አሳብ አልፎ-አልፎ ውርር እያደረገኝም ቢሆን "ማኅሌት" እንደምትሰኝ ከባለቤቴ ጋራ ስነጋገር ዘጠነኛው ወር መጣና ምጥ ይዞአት ሆስፒታል ገባች፡፡



በመጀመሪያው ቀን ምጡ ጠናባት፡፡ በሁለተኛም ቀን እንዲሁ ስታምጥ ውላ አደረች፡፡ እትብቱ በሕፃኑ አንገት ተጠምጥሞ ማመጥ እንጂ መውለድ እንደማትችል የተገነዘበችዉ ሐኪም በእጇዋ እትብቱን አላቅቃ አገላገለቻት። በተመኘሁላት ስም ማህሌት ተባለች፡፡አምሳለ ገብረ ማርያም ትባላለች፡፡ በሙያዋ ነርስ፣ የምትሠራውም በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ነበር፡፡ በሆስፒታሉ ግቢ ውስጥ ለነርሶች መኖሪያ በተዘጋጁ ቤቶች ውስጥ ትኖር ነበር፡፡ እንደ እኔ በዕድሜዋ ጠና ባትልም ሁለ ነገሯ ትዳር ለመመሥረት የተዘጋጀ ነበር፡፡ ሁለታችንም አስቀድሞ ተያይተን እናውቅም፡፡

ስለሁለታችን የሚጨነቁ የሁለታችንም ወዳጆች የነበሩ፣ ራሳቸውም ጓደኛሞች የነበሩ ሰዎች መከሩብን፡፡ ሊያስተዋውቁን ወሰኑ፡፡ እኔ በወቅቱ የምኖረው ናዝሬት በማስተምርበት መጽሐፍ ቅዱስ አካዳሚ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግቢ







የ አለቃ ገ/ማርያም የባለቤቴ አባት ( የኮሪያና የኮንጎ ዘማች)

ውስጥ ነበር፡፡ ሊያገናኙን በተስማሙት መሠረት በአንዱ ዓርብ ከሰዓት በኋላ ከእኔ ጋር ሆነን በቮልስ ዋገን መኪናዬ ከናዝሬት ወደ አዲስ አበባ ተጉዘን ወደ ጳውሎስ ሆስፒታል አመራን፡፡

ስንደርስ የገባነው ጓደኛዋ ቤት ነበር፤ ሻይ እየተፈላ ተጠርታ መጣችና ተዋወቅን፡፡ ፈረንጆች "THE REST IS HISTORY" እንደሚሉት እንደ ታሪክ ሆኖ ተመልሶ ይወራል፡፡ በጣም ጥቂቱን ኋላ ላይ እመለስበታለሁ፡፡

ባለቤቴ ወይዘሮ አምሳለ ገ/ማርያም በ1942 ዓ.ም ፊት በር ተብሎ በሚጠራው ሠፈር ተወለደች። አባቷ የመቶ አለቃ ገ/ማርያም ፈዬ፤ እናቷ ወ/ሮ ወርቅነሽ ብሩ ይባላሉ። አባቷ በደቡብ ሸዋ ከምባታና ሐዲያ አውራጃ በአንገጫ ወረዳ ልዩ ስሙ ገርምባ በሚባል ቀበሌ ተወልደው አደጉ፡፡ በጐልማሳነት ዕድሜአቸው ወደ አዲስ አበባ መጥተው በክብር ዘበኛ ጦር ክፍል ተቀጠሩ፡፡ የክብር ዘበኛም አባል ሳሉ በመጀመሪያ ኮሪያ ቀጥሎም ኰንጐ በመዝመት የተዋጉና አገራቸውን በጥሩ ስም ካስጠሩ ተዋጊዎች አንዱ ነበሩ። ከአገልግሎታቸዉ ስኬት የተነሳም የመቶ አልቅና ማዕረግ ደረሱ፡፡





የ አለቃ ገ/ማርያም የባለቤቴ አባት ( የኮሪያና የኮንጎ ዘማች)

በ1953 ዓ.ም መንግሥቱና ገርማሜ ነዋይ መርተውት በነበረው የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ በመሳተፍ ተጠርጥረዉ ታሰሩ፡፡ ከሞት፣ ከረዥም እስርና ከግዞት የተረፉት



ባለቤቴ ወ/ሮ አምሳል ፣ እህቷ ወ/ሮ አሥረበ ፣ እናቷ ወ/ሮ ወርቅነሽ እና እህቷ ወ/ሮ ወይኗቱ

የክብር ዘቡ አባላት ወደ ሌላ የጦር ክፍል ሲበትኑ የመቶ አለቃ ገ/ማርያም ወደ ምድር ጦር ተመድበው ወደ ነጌሌ ቦረና ተላኩ። ባለቤታቸውን ወ/ሮ ወርቅነሽ ብሩ ያገኙአቸው እዚሁ አዲስ አበባ የክብር ዘበኛ አባል ሳሉ ነበር።

የአምሳለ እናት ወ/ሮ ወርቅነሽ ወላጆቻቸውን ከ1928 - 1933 ዓ.ም አገራችንን ወሮ የነበረዉ ጣሊያን ሲገድልባቸዉ ከተወለዱበት ከሐረርጌ በርግገው እንደ ወጡ አዲስ አበባ ይኖሩ ነበር፡፡ አገር ሲረጋጋ ያኔ ገና ተራ ወታደር ከነበሩት ከገ/ማርያም ጋራ ትዳር መሠረቱ፡፡ በልጅነት ከመሠረቱት ትዳራቸው መጀመሪያ አምሳለን፣ ቀጥሎ ወይኒቱን ከዚያም አስረስን አፍርተዋል።





አምሳለ ዕድሜዋ ለትምህርት ሲደርስ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አንደኛ ደረጃና በዳግማዊ ምኒልክ ትምሕርት ቤት 10ኛን ክፍል ካጠናቀቀች በኋላ በኢትዮጵያ ቀይ መስቀል የነርሶች ትምህርት ቤት ተምራ ዲፕሎማ አግኝታለች። በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል በነርስነት ሙያዋም ስትሠራ ማታ ማታ በመማር የ12ኛን ትምህርት እየተማረች ሳለ ነበር ከእኔ ጋራ የተገናኘነው። በዚያዉ ሰሞን የተሻለ ደመወዝና የኑሮ ለውጥ ፍለጋ የአመለከተችበት የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ሆስፒታል ተቀብሎአት ወደ ወንጂ መጣች፡፡ መኖሪያዋና ሥራዋ እሠራበት ለነበረው ለናዝሬት በጣም የቀረበ ነበር። በምክንያትም ያለ ምክንያትም ጎራ እያልኩ ለመጎብኘት ተመቸኝ፡፡ ያስተዋወቁን ወዳጆቻችን ወደ አንድነት እንድንመጣ ማበረታታቸውን ቀጠሉ፡፡ ይሁን እንጂ እንደተዋወቅን ወዲያዉ ወደ ትዳር ዓለም መጓዝ አልጀመርንም።

የየግላችንን "በእውነት የኔ ነው/ናት? ወይስ ... አይደለም?" የሚሉትን ጥያቄዎች በቅጡ ለመመለስ ሁለታችንም እንደ ክርስቲያን በጸሎት፣ እንደ ባለአእምሮም ከተለያዩ ሰዎች ሰዎች ጋር ለመመካርና አስተያየቻቸውንም ለመመዘን በቀጥታም በተዘዋዋሪም መኳተነን ነበረብን። በእኔ በኩል በዚያን ጊዜ ዕድሜዬ ሠላሳ ሁለት ዓመት ስላስቆጠረ ትዳር እንድመሠርት የነበረዉ የወዳጅና ዘመድ ግፊት ብዙ ነበር። ስለሆነም በባዶ ሜዳ ስለ ትዳር አጋሬ የደረደርኳቸውን አንዳንዳንድ መመዘኛዎች ቀስ በቀስ እያላላሁ መምጣቴ አሌ የማይባል ነበር - ከእምነት አንድነት በስተቀር።

ወ/ሮ አምሳል ከእኔ ይልቅ በብዙ ነገር ጠንቃቃ ናት። ስለሆነችም በችኩላ የመወሰን ችግር በትዳራችን አሁንም እንኳን አያጠቃንም። ይኸንን እናድርግ ብዬ ኃሳብ ሳቀርብ "ለምን?" "እንዴት?" ብላ ስለምትጠይቅ በጥድፊያ ውሳኔ ውስጥ ገብተን የተቆጨንበትና የማስታውሰው ነገር የለም። ስንገናኝም በመጀመሪያ እይታዋ "አበበ ቢቂላን ይመስላል" ከማለቷ በቀር ሙሉ ማንነቴን ለመቀበል ረዘም ያሉ ወራት ፈጅቶባት ነበር፡፡ ወደ ትዳርም ለመግባት ከተስማማን በኋላ የአባቷ ከዚህ ዓለም



በሞት መለየት ምክንያት ሠርጋችን ለአንድ ዓመት ጊዜ ተራዝሞ ነበር። ለአባቷም ስታለቅስ "ሚስጢር ነበረኝ" እያለች ሰውን ሁሉ ማስለቀሷን አስታውሳለሁ፤ ለማግባት መወሰኗን አልነገረቻቸውም ኖሯል::

በተዋወቅንበት ሰሞን በሁለታችንም በኩል ሌሎች በአሳባችን የምናስላስላቸዉ ሰዎች (የልባችን ምልምሎች) ነበሩን ብላችሁ አትገረሙ፤ ትዳር የመላእክት ጉባዔ ውሳኔ አይደለምና መመዘን መመዛዘን የነበረም ያለ ነዉ። ለምሣሌ አንድ እርሷን ለትዳር አጥብቆ ሲፈልጋት የነበረ ሰው አዲስ አበባ እያለች ብቻ ሳይሆብ ወንጂም በሥራ ከተዘዋወረች በኋላ እየተመላለሰ ይጠይቃት እንደነበረ አስታውሳለሁ። እኔም ብሆን እንዲሁ ከሌላ ልጅ ጋር የተጀመረ ነገር ነበረኝ። የአምሳልን ልተወውና የኔኑ ጅምር ላውራችሁ::

የኔ የቀድሞ ጅምሬ እምነቷ ወደ ጂሆቫ ያዘነበል እንደነበረ የተረዳሁት ሽማግሌ ልኬ ወላጆችዋም ተቀብለው የሠርጉ ቀን ከተወሰነ በኋላ ነበር። "ነገር ፈረሰ ዳቦ ተቆረሰ" እንደሚባለው ሆኖ ቀርቶአል። እንዲያውም የሚመስላትን ስታገኝ ቀድማኝ አገባች። ተጠባባቂ (ታሳቢ) ነበርኩ ማለት ነዉ:: ያኔ ዋናዉ ጉዳይ መቅደም ወይንም መቀደም የመሰላቸዉ ብዙ ወዳጆቼ ነበሩ:: በመቀደሜም "ከርፋፋ" የሆንኩ ሳይመስላቸዉ አልቀረም፤ ለእኔ ግን በእምነት የመለያየታችን ነገር ለድርድር ማቅረቡ ሕይወቴን በዘላቂነት የሚያወላግድብኝ ጉዳይ እንደሚሆን ስለ ተረዳሁ ቅርም አላለኝ ነበር:: ለትዳር በሚተሳሰቡ ሰዎች ዘንድ በሕይወታቸዉ ዋጋ የሚሰጧቸው ነገሮች ሁሉ በምርጫ ውስጥ አስፈላጊ ቅመሞች ናቸዉ:: ቸል ቢባሉ ትዳሩን እንደ ጫማ ውስጥ ጠጠር እቆረቆሩ ምቾት ይነሱታል፤ እረፍትና ሰላም ያሳጡታል፤ አብሮ ለመኖር እጅግ አስቸጋሪ ያደርጉታል። ጠጠሩ እንኳን ጫማውን አውልቆ ማራገፍ ይቻላል። በእምነት ከማይመስሉ ወይም ከማይመስሏት ጋር መጣመር ትዳርን ግን እንደ ጫማ አውልቆ ማራገፍ እንዲህ ዋዛ አይደለም፤





እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ካዘጋጃቸዉ መልካም ነገሮች ዋነኛ የሆነውን የጋብቻን ዋጋም ማቃለል ይሆናል።

አብሮነታችን ወልቆ ቀሪ ሕይወታችንም እንዳይወላላቅ ነበር እስከ መጨረሻዋ የውሳኔ ቀን ድረስ በጥንቃቄ ለመራመድ የሞከርነዉ:: ይህን ሁሉ ማመንታትና የአሳብ ውጣ ውረድ ካለፍን በኋላ ነበር በ1966 ዓ.ም ሚያዚያ . . . . ቀን በዕለተ ፋሲካ የተጋባነዉ::

## 21. የአርባ ዓመት ትዳር

የሃያ ስድስት እና የሠላሣ አራት ዓመት ወጣቶች ሳለን በ1966 ዓ.ም የፋሲካ እለት



የጋብቻ ሥነ ሥርዓታችን ዕለት ሚያዚያ 6 / 1966 ዓ.ም
(አሁን በሁሉም ወንጌላዊያን አብያተክርስቲያናት እንደ ባህል የተለመደው ሻማ ማብራት ሥነ ሥርዓት በኢትዮጵያ የተጀመረው በእኛ ሠርግ ዕለት ነው።)

የጀመርነው ትዳር በሚያስደንቅ መቆየት እስከዛሬ ዘልቆልናል:: የዚህ መጽሐፍ ይህን አሁን የምታነቡትን ምዕራፍ ስጽፍ፣ ስሰርዝ፣ ስደልዝ እንደገናም በድልዙ ላይ

የሃያ ስድስት እና የሠላሣ አራት ዓመት ወጣቶች ሳለን በ1966 ዓ.ም የፋሲካ እለት



የጋብቻሥነሥርዓታችን ዕለት ሚያዚያ 6 / 1966 ዓ.ም

(አሁን በሁሉም ወንጌላዊያን አብያተክርስቲያናት እንደ ባህል የተለመደው ሻማ ማብራት ሥነሥርዓት በኢትዮጵያ የተጀመረው በእኛ ሠርግ ዕለት ነው።)

ስከትብ ባለቤቴን ወ/ሮ አምሳለን አንድ ጥያቄ ጠየቅኋት፡፡ "አርባ ዓመት ሙሉ እንዲህ በአብሮነት ያቆየን ምስጢር ምንድነዉ?" ብዬ፡፡ ፈጥና የወረወረችልኝ ምላሽ "እግዚአብሔር ነዋ" የሚል ነበር።



እኔና ባለቤቴ

ከእውነቱ ያልራቀና ያለ እግዚአብሔር እንኳን አርባ ዓመት ቀርቶ አራት ቀኑም እንደሚከብድ እናምናለን። ወደ ኋላ ተቆጥሮ እማንኛውም የቆይታ አኋዝ ላይ ለመቆም የመድረሻዉ መንገድ "ሁሉም በጽጌረዳ አበባ ፍራሽ ነበረ፤" ቢባል





ያስተዛዝባል እንጂ የሚታመን አይሆንም። የሚያስፈሩ፣ የሚያንገጫግጩ ኮሮኮንች ጉዞዎችም ነበሩበት። እንዲያውም የእግዚአብሔርን ታላቅ የጸጋ ምርኩዝነት የምንገነዘበው የትዳር ጉዞ ወዲያ ወዲህ ከሚያላትም ሁኔታ ውስጥ ወጥቶ ወዲያ ማዶ የሚሰፍነውንና ከቶም በቃላት የማይገለውን ሰላም ማጣጣም ሲቻል ነዉ፡፡

ሁለት ተቃራኒ ፆታዎች ተዋድደውና ተፈላልገው ትዳራቸውን ከመሠረቱ በኋላ እንደዚያው ተዋድደውና ተፈላልገው ዘመናቸውን ይጨርሳሉ ማለት ግብዝነት አለዚያም ተምኔታዊነት ነው፡፡ ከቶም ሰዉ መሆናችን ብቻ አያስችለንም፡፡ የሚቻለው ግን መቻቻል ራሱ ነው፡፡ ለመቻቻል አቅም ያነሣቸው እንደማይዘልቁትም በየጊዜው ይታያል፡፡ ማንኛውም ወንድ ወይም ሴት "እኔ ብቁ ነኝ" ብሎ መናገር አይቻልም፡፡ እንደልማዳዊ አባባል ሦስት ጉልቻ መሆንና መሸካከም የቀረውን ሸክም ሦስተኛው ጉልቻ ለሆነው እግዚአብሔር መተውና በርሱም መደገፍ ነው፡፡ ከዚህ ጋራ ደግሞ የልጆች መወለድና እነርሱን በኃላፊነት አሳድጎ መሆን የሚችሉትን ሁሉ ሆነው አድገው ጥሩ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ የማድረግ ፍላጐት ለባልና ሚስትም አብሮ መኖር አቅም ይሰጣቸዋል ብዬ አምናለሁ፡፡ ያ ማለት ደግሞ ግጭት፣ ንትርክና ብስጭት አይኖርም ማለት አይደለም፡፡ የሚያነታርከውን ነገር እንደ አደጉ አዋቂ ሰዎች ተነጋግረው መፍታት መቻል የትዳርን ኑሮ ከሚያቀልሉ ነገሮች አንዱ ነው። ለአንዳንድ የትዳር ባልደረባ ደግሞ መነጋገር ማለት እርሱ ወይም እርሷ ብቻ ይሆኑና መነጋገር የተባለው ድምጥማጡ ጠፍቶ መጯጯህ ይሆናል፡፡

መንፈሳዊና ሥጋዊ ፍላጐቶችና ስሜቶች አንዳንድ ጊዜ እንደማይጣጣሙ እንደሚቃረኑና እንደሚፈታተኑ ሁሉ ባልና ሚስትም እንደዚሁ ናቸው፡፡ በየግል ፍላጐቶቻቸው የተነሣ ይወዛገባሉ፣ ይጋጫሉ ወደ ከባዱ ሁኔታ መለያየትም ይደርሳሉ፡፡[26] የግል ፍላጐት የተባለው ከትዳር ባልደረባም አልፎ ልጆችንም ዘልሎ ለብቻው "የእኔ ብቻ" ይሆንና የአገር ሽማግሌም ተሰብስቦ የማይፈታው

[26] ማሞ ውድነህ፤ የደረስኩበት - ግለ ታሪክ ትዝታዎች፣ 1997 ዓ.ም ገጽ 18።



እኔና ባለቤቴ

ችግር ይሆናል፡፡ እኔና ወይዘሮ አምሳለም አልተጨቃጨቅንም፣ አልተኳረፍንም ብለን አንዋሽም፡፡ ይሁን እንጂ ሁለታችንም በተለያየ ሁለት ሰብእና ተከርክመን እንደማደጋችን መጠን ሁለቱችንም ደካማ ጐን እንዳለን ሁሉ ብርቱ ጐንም ነበረን፤ አለንም፡፡ ስለሆነም ትዳራችን ከእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ በተጨማሪ የየራሳችን ምርጫና ውሳኔ ነዉ ለማለት እደፍራለሁ፡፡

አንዱ የእግዚአብሔር ጸጋ መከሰቻው በልጆች ነው። ትዳር መስርቶ ልጆች ወልዶ አሳድጐ መልካም ዜጋ ሆነው ማየት ከራሳችን አስወጥቶ ትኩረታችንን በእነርሱ ላይ ማድረጋችን የትዳርን ውጣ ውረድ ማሸነፊያ ታላቁ መሣሪያ ሆኖልናል። ቀደም ሲል እንደገለጽኩት ከቀን ሕልሜ ሰነቃ የማገባትን ሚስትና የምንወልዳቸውን ልጆች ከነስማቸው መጻፌ ይታወሳል። ቀልድ የሚወድ አምላክ በዚያው በአለምሁት ቅደም ተከተል ልጆቹን ሲሰጠን እናም ስንሰይማቸው ባለቤቴ ያለአንዳች ተቃውሞ ነበር የተስማማችኝ። በዚህም አድናቆቴ ብዙ ነዉ።


ሌላው የኢትዮጵያ መሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ዋና ጸሐፊ ሆኜ የተመረጥኩት ተጋብተን ብዙም ሳንቆይ ነበር፡፡ ስድስት ወር ሳንቆይ ከናዝሬት ድንኳናችንን ነቅለን በመስከረም ወር 1967 ዓ.ም አዲስ አበባ ገባን፡፡ በአዲስ አበባ ቆይታችን ለሥራ ቦታ ቅርበትም ሆነ ምቹ አካባቢ ለመፈለግ ሦስትና ቤቶችን ቀያየርን፡፡ ከዚያ ደግሞ ቤት ሰርተን መካኒሳ ወረድን።ድንኳን መትከል፣ ድንኳን መንቀል የኑሯችን አካል ሆነ፡፡ በተንቀሳቀስን ቁጥር የቤት ቁሳቁስ ማሰባሰቡና ማስጫኑ" ማውረዱና ማስተካከሉ በአብዛኛውን ሴቶች ላይ የሚወድቅ ኃላፊነት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ወ/ሮ አምሳለ ያለችግር ተወጥታዋለች።

ይህን ሁሉ የምዘረዝረው እግዚአብሔር ሕይወታችንን ተንቀሳቃሽ ሊያደረግ ሲያለማምደን እንደሆነ ለመጠቆም ጭምር ነዉ፡፡ ከፍ ብሎ የተዘረዘረው የአገር ውስጥ ድንኳን እየነቀሉ መትከል ለዓለም አቀፉ ተከላና ነቀላ ሲያዘጋጀን ነበር ለማለት






ይቻላል። በዚህ ሁኔታ መጀመሪያ ከኢትዮጵያ የተዛወርነው ወደ ኒውዚላንድ ሲሆን በቁስአቁስ ደረጃ አፍርሶ መገንባት ነበረብን። ለሠርጋችን የተሰጡንና የሚያስጐመጁ እቃዎች ሁሉን ማስጫን ስለማይቻል ማራገፍ ወይንም መስጠት ነበረብን። የእቃው ብዙም አላስቸገረንም ነበር። የመጀመሪያ ቤታችን ይሸጥ ብለን የወሰንን እለት



ልጆቻችን ዋብቶ መና ማህሌት (1992 ዓ.ም.)

ውስጣችንን አስለቅሷል። የእኛን ብቻ ሳይሆን የልጆቻችንንም ጭምር። በዚያን ቀውጢ ዘመን በነፃም እንዲኖሩበት የጠየቅናቸው ዘመዶቻችን የተለያየ ምክንያት በመስጠት ሊኖረበትና ሊያቆዩልን አልቻሉም ነበር። ውክልና ብለን የሰጠነውም ወደጃችን በግማሽ ዓመት ጊዜ ውክልናውን ማውረድ ስለፈለገ የነበረን አማራጭ መሸጥ ነበር። ያ ለእኛ በጣም ከባድ ነበር። የዋጋው መሰበርና ቤቱንም ማጣት።

ወደ ድንኳናችን ነቅሎ መትከል ልመለስና በጠቅላላው ስምንት ጊዜ ቆጠርኩ የተነቃቀልነው። ለዚህ ሁሉ መንቀሳቀስ አራት ቤታችንን ሸጠን እቃችንን ሰጥተን ያደረግነው መዘዋወር በኢኮኖሚአችን ላይ ብቻ ሳይሆን ጫናዉ በሰውነታችንም ከፍ ያለ ነበር። ይሁን እንጂ እንደቤተሰብ ትኩረታችን መደረግ ባለበት ነገር ላይ ስለሆነ መደጋገፍና መተሳሰብን ይፈጥራል። አንድ ጊዜ አስታውሳለሁ ካሊፎርኒያ ስኖር እኔ በወርልድ ቪዠን ሥራ ወደ አፍሪካ ጉዞ ላይ ሆኜ የነበርንበትን የኪራይ



ልጆቻችን ዋብቶ መና ማህሌት (1992 ዓ.ም.)

ቤት መቀየር እንዳለብን ተስማምተን ስለነበረ እኔ ከጉዞዬ ስመለስ ቤታችን ተቀይሮ እናትና ልጆች ሁሉን ጨርሰው በተስተካከለ ቤት ተመልሻለሁ። መደረግ አለበት በምትለው ነገር ላይ መጐተትን የምትጸየፍ ባለቤቴ እንዲህም አድርጋለች።

ልጆቻችን እያደጉ ሲሄዱ ሙሉ በሙሉ በምናደርጋቸው ውይይቶችና ብሎም ውሳኔዎች መሳተፍ ብቻ ሳይሆን የሚበጀውን መርምረው በአጽንኦት ተናግረው ይረዱን ነበር። ይህም የሰው ሥራ ሳይሆን የማይመረመር አምላካችን ከሰጠን ስጦታዎች አንዱ ነው። ዛሬ እነርሱ የራሳቸው ሰዎች ሆነው በሚኖሩበት ሕብረተሰብ ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ ያሉ ሰዎች ሲሆኑ በደወሉልን ቁጥር መልካም ሐሳባቸውን ከመግለጽ አልፈው ለወላጆቻቸው በጐ ከማሰብና ከማድረግ ያልተቆጠቡ ናቸው። ስለልጆቻችን ካወራሁ በአንድ ኀጠመኝ ልደምድም። ሦስቱም ወደ ትምህርት ቤታቸው ሄደው እኔ አሁን በማላስታውሰው ምክንያት ቤት ውዬ ነበር።

ያ ማለት እኔና ባለቤቴ ብቻ ነበርን። እስካሁን ሁሉ መልካም ነው። በር ተንኳኳና ስንከፍትለት አዲስ ዓይነት የቤት መጥረጊያ (Vacuum cleaner) አስተዋዋቂ ሰው ነበር። ማድረግ የምንችለውን ሳናደርግ ስለቀረን ያም ከበር መመለስ ገብቶ ሳሎናችን እቃውን ዘረጋግቶ በሰዓት ቁና ቃላት እየተናገረ ስለእቃው ያስረዳን ጀመረ። አብዝቶ በተናገረ ቁጥር የባለቤቴ ልብ ወደ እቃው እየተሳበ እኔ ደግሞ ጥያቄ በመጠየቅና ፊት በመንሣት ስናወጋ ቆይተን "ያንን ያህል ከፈለግሺው ይሁን እንግዛው" ሳልል ግን ወደዚያው አዘንብዬ ሳለሁ ሦስቱም ልጆቻችን ሰዓታቸው ደርሶ በቁልፋቸው የቤቱን በር ሲከፍቱ እና ሲገቡ ሻጩ ያወርድብን የነበረው የንግግር ጐርፍ ገታ አደረገዉ። ወዲያውኑ መኻከለኛው ልጃችን መና ሳሎኑን ሞልቶት የነበረውን እቃና የተፋጠጥነውን ሦስታችንን እያየ "ይኼ ሁሉ ምንድነው?" ብሎ ሲጠይቅ ያ ሻጭ በአጭሩ በጣም ልዩ ቫኪዩም ክሊነር እንደሆነ ሲያስረዳው " ይኸማ አለን አይደል





እንዴ?" ሲል ብቻ እኔ ከምርኮ ወይም ከአደጋ የሚያድኑን (rescue mission) እንደመጣለት ሰው ተንፈስ አልኩ። ሻጩም አየሩ እንደወጣበት ኳስ ሲተነፍስ ባለቤቴ እንዴት እንደተነፈሰች አላስታውስም። በደረሰልኝ ፈጣን እርዳታ አቅም አገኘሁና በል እናመሰግናለን እቃህን ሰብስበህ ሂድልን ብሎ ማስናበት ቻልን። ሻጩ ያመጣው እቃ አቧራውን ፍጹም በመምጠጥ ኗሪዎቹን ከብዙ በሽታ የሚታደግ አድርጐ ስላቀረበ የባለቤቴን ልብ እጅጉን ማርኮብኝ ነበረና እንኳም እንዳላስከፋት ብዬ ስንታገል የደረሱት ልጆቻችን ነፃ አውጥተውኛል። የቀሩት ሁለቱ ልጆቻችን ዋቤቶና ማሕሌት ነገሩን እንደመናቅ ብለው የሚበሉትን ፍለጋ ወደ ወጥቤት ገቡ።

ከሁሉም በላይ እስከዛሬ በትዳር ጸንተን ያቆየን የምለው ትልቁ ቁም ነገር ሁለታችንም የሁሉ መሠረት በሆነዉ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመሥርተን ማደጋችን ቤተክርስቲያንንም እንደ አቅማችን መጠን ለማገልገል በመታደላችን ነዉ፡፡ እኔ መቼም ትዳር ከመሠረትን በኋላ ከቤተክርሲቲያን አመራር ጠፍቼ አላውቅም፤ ያም ለሁለታችንም ቢሆን የኃላፊነት ስሜት አስርፆብን ነበር፤ ስለሆነም ለራሳችንም ሆነ ለመንጋዉ ጭምር መጠንቀቅ ተገባን፡፡ ስለሆነም በትዳር ጉዳይ ጫፍ የረገጡ አስተያየቶችንም እርምጃዎችን ከመውሰድ በመቆጠባችን ለትዳራችን እድሜና ጸጋ እንደለገሠው አምናለሁ። የምናነበውም ሕያው ቃል መሠረታችንን እያጸናልን የመንገዳችን ካርታ ሆኖ አኑሮናል። አብሮ መጸለዩም ይኸን ያህል ሠልጥነንበታል ባልልም ሌላው የትዳር አውታራችን ነበር፡፡ ስናከር እያረገበን፣ ስንላላም እያጠነከረን ግንኙነታችንን ከአምላካችን ጋር እያስተሳሰረን አቆራኝቶን እዚህ ደርሰናል፤ አርባ ዓመት፡፡ ክብር ሁሉ ለእርሱ ይሁን! መጽሐፉ የኔና የእምሣለ የትዳር ማኑዋል ስላልሆነ ባጭሩ መግታት እንዳለብኝ ይሰማኛል፡፡ በትዳር ሕይወታችን ከተግባቦትና ከሰዎች ጣልቃ ገብነት የተያየዘ ያንድ አጋጣሚ ትዝታዬን ልተርክላችሁ፡፡ አንድ ጊዜ የቤተሰብ ጉዳይ ለመፈጸም ከ400ኪ.ሜ በላይ ተጉዤ ቦታው ደረስኩ፡፡ የሚሠራ ነገር ስለነበረ የሚያስፈልገው ሁሉ ከዚሁ ከአዲስ

አበባ ተገዝቶ የሚሠራው ሠራተኛም ተቀጥሮ በመኪና ተጭኖ የተባለውን ርቀት ማጓጓዝና ሥራውን ማሠራት ነበረብኝ።

በዚህ ላይ ባለቤቴ ለእናቴ ስጥ ያለችኝ ገንዘብ ነበር። እስከዚህ ድረስ ምንም ችግር አልነበረም እኔ ሥራውን ለማሠራት አንድ ሳምንት ቀድሜ ከላይ የተጠቀሱትን ዕቃዎችና ሠራተኛ በአውቶብስ አስጭኜ መንገድ አድሬ በማግሥቱ ከቦታው ደረስኩ። እዚያም ለሥራው የሚያስፈልጉ ከአዲስ አበባ የማይጫኑ እንደ ድንጋይ፣ አሸዋና ውሃ የመሳሰሉትን የማቀርብበትን መንገድ አጥንቼ እንደሚቻል አደረግሁና ሥራው ተጀምሮ በፕሮግራሙ መሰረት ተጠናቀቀ፡፡ ባለቤቴ በሳምንቱ ለፕሮግራሙ ደረሰችና እየተጠናቀቀ ያለውን አሳይቻት ሁለታችንም ደስ ብሎን አደርንና በጧት ተነሥቼ ሥራውን ለማስጨረስ ሄድኩ። ወደ ረፋዱ ላይ ባለቤቴ ከእህቷ ጋራ ወደ ሥራው ቦታ መጡና የማይሆን ነገር መሆንና ማድረግ ጀመረች። የሥራው ባለቤት መሆንና ሠራተኛውን እንዲህ አድርግ ያንን ጨምር ማለት ስትጀምር ግራ ገብቶኝ ዝም ብዬ ማየት ጀመርኩ።

ሥራው ተጠናቅቆ የማጸዳዳት ነገር ነበር የቀረውን ጨራርሰን ሠራተኛውን አስናብቼ አድሮ በማግሥቱ እንዲሣፈር አድርጌ ወደ ቤት ተመለስኩ። በዚህ ጊዜ ሁሉ በእኔና በእርሷ መካከል ንግግር ተቋርጧል። የቀረነው እናቷም እህቷም እኔን ለማስተናገድ አዲስም አማች ስለሆንኩ ሁሉ ነገር አምሯል ሞቅአልም። ባለቤቴ ብቻ ከበረዶ ቀዝቅዛለች። ሆን ብዬ እርሷን አንድ ነገር ስጠይቅ እናቷ ወይም እህቷ ይመልሱልኛል። እንዳይታደር የለም አደርኩ።

የታቀደው ፕሮግራም የሚከናወነው በነጋታው ስለነበረና የሚጠበቅብኝን ስላሟላሁ መንፈሱም ስላልተመቸኝ ጥዬ በጠዋት ለመመለስ ቃጣኝ፡፡ ይሉኝታ አንዳንዴ መልካም ነው፡፡ አክብረውኝ የሚያስተናግዱኝን እናቷንና እህቷን ሌሎች እንደቤተሰበ የነበሩ ጐረቤቶች የፕሮግራሙ ባለቤት አድርገው የሚመለከቱኝ ሁሉ ምን ይላሉ ብዬ አውጥቼ አውርጄ ብድግ ብሎ መሄዱን አለፍኩት። የታሰበው ፕሮግራም በጥሩ ተጠናቀቀ።





ባለወቅሁት ነገር እንደተኰረፍኩ ጉዳዩ ተጠናቅቆ ተነስተን በአውቶቢሳችን ተሳፍረን እማማ "የዘመድ አውራ ያርግህ" ብለው መርቀውኝ ጐረቤቶቹም ደስ ብሏቸው በዚሁ መልክ መርቀውኝ ተሰነባብተን በተሳፈርነው አውቶቢስ ተጉዘን ሻሸመኔ ደረስን። መኪናችን በቀለ ሞላ ሆቴል ቆማ ነበር የጠበቀችንና አስነስተን ወደ ናዝሬታችን ተመለስን። በዚህ ጊዜ ሁሉ ችግሩን ለማወቅ ያልተደረገ ነገር አልነበረም ግን መልሱ ዝም ነበር። ሳምንቱ አለቀና ሁለተኛው ሳምንት ሲመጣ እሁዱን ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ነበረብኝና አቶ በየነን እና አቶ ገመዳን ሁለቱን ሽማግሌዎቼ ሄጄ ችግሩን ነግሬ ለማስተማር እንደምቸገር ሳጫውታቸው "እኛ እንጠይቃታለን" ብለው እነርሱ ወደ ቤታችን እኔም ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄድኩ። አፌ እንደ ኩበት ደርቆ ከዚያ የባሰ ደረቅ መልእክት አቅርቤ በችኮላ ወደ ቤት ስመለስ በክብረ መንግሥት ጀምሮ ናዝሬት ድረስ የተከተለኝና ግራ ያጋባኝ ግርዶሽ ተገለጠ።

ለዚያ የሁለት ሳምንት ጽልመት የደረገን ያ "ለእናቴ ስጥ" ያለችው ገንዘብ ሲሆን የተነጋገርነው ሁለታችን ነበርን። አሁን በነገሩ ውስጥ አራት ሆነናል። እኔና ባለቤቴ እማማና እህቷ ወይኒቱ። ወይኒቱ እኔና ባለቤቴ ስንነጋገር አልነበረችም ስለተነጋገርነውም ነገር የሰማችው ባለቤቴ ከመጣች በኋላ ነበር። እኔን ወይም እማማን እንደመጠየቅ ወይኒቱን "ገንዘብ ሰጠ ወይ" ብላ ስትጠይቅ "እኔ እንጃ አልመሰለኝም" ትላታለች። እስከአሁን በሆነው ክፉት የለውም። ክፋቱ እኔ መልዕክተኛው እያለሁና መልእክቱ የተባለላቸው እማማ እያሉ በአላወቀችው አራተኛ ሰው ነገሩን መደምደሙ ላይ ነው። እኔ እንደ ደረስኩ እማማን ነገሩን ነግሬ ገንዘቡን ልሰጥ ሳወጣ "ምነው ልጄ ምን አስቸኰለህ ይደርሳል የሚያስፈልገኝ ሁሉ በእጄ አለ" ሲሉኝ አልጋፋም ብዬ መተዌን የምናውቀው እኔና እማማ ብቻ ስንሆን፣ እኔም እርሳቸውም ሳንጠየቅ ውሳኔ መደረሱ ሊኖረን የሚገባውን የደስታ፣ የሣቅና የሰላም ጊዜአችንን ወሰደብን። ይህ ሊሆን የቻለው የተለያየን ሰዎች በመሆናችን ነው። ስለዚህም አቀራረባችን ይለያያል። በሁለቱ የትዳር ባልደረቦች መካከል የሚሆነውን ጉዳይ በሁለቱ መካከል መጨረስ እንጂ መካካድ ሳይኖር ምስክር መቁጠርና ማስመስከሩ ገበናን ከመዘርገፍ በተቀር ጥሩ አማራጭ አይደለም፤


እንዲያውም ያሳስታል። ጥሩ ማኅበረሰብን ለመገንባት ምርጥና ብቸኛው ግብአ
ቤተሰብ ነው።

ጥሩ ቤተሰብ ለመገንባት የትዳር ባልደረቦች ከራሳቸው ግለኛ ፍላጎት ወጣ ማለት
ራቅ አድርጎ ማሰብን ይጠይቃል። ለዚህ ታላቅ ዓላማ ሁለቱ የትዳር ባልደረቦ
መሰጠትና መሥራት አለባቸው። ጥሩ ልጆች ተወልደው በጥሩ ሞራል፣ ባሕል
እምነትና ባሕሪ ተቀርጸው ሲያድጉ ጥሩና ኃላፊነት የሚሰማው ማኅበረሰ
ይወጣዋል። እያንዳንዱ ዜጋ ይህንን ለማድረግ ቢታደል ለአገር ዕድገትና ልማ
"ምን አስተዋፅዖ አደረግኩ" ብሎ ማሰብ የለበትም።

ይህን ጽሑፍ በማዘጋጅበት ወቅት አግብቶ ወልዶ አያቶች ያደረገን ያ ልጃችን መና ብቻ ነው:: እርሱና ባለቤቱ ወይዘሮ ሰላም አሰፋ እንደ አውሮፖውያን አቆጣጠር 2006 ተጋብተው ውብ የሆኑ ሁለት ወንዶች ልጆች (ብሩክ እና ካሌብ) ወልደዋል:: መና በሙያው ጠበቃ ነው::


ብሩክ (የልጅ ልጃችን) መና (ልጃችን) ወ/ሮ ሰላም አሰፋ ካሌብ (የልጅ ልጃችን)

የመጀመሪያው ልጃችን ዋቤቶ የተሰማራው በሆቴል ሙያ ሲሆን የሥነ ጥበ
ዝንባሌ ይታይበታል:: በቅርብ ጊዜ ትዳር ይመሠረታል ብለን በተስፋ እንጠብቃለን
: ማኀሌት የአንድ ድርጅት የሰው ኃይል አስተዳደር መምሪያ ድሬክተር ሆ
እያገለገለች ነዉ፤ እሷም አያት እንደምታደርገን ተስፋ እናደርጋለን::



ብሩክ (የልጅ ልጃችን) መና (ልጃችን) ወ/ሮ ሰላም አሰፋ ካሌብ (የልጅ ልጃችን)